# አማርኛ

እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

የተማሪ መጽሐፍ

(፯) 7ኛ ክፍል

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የትምህርት ሚኒስቴር**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለከተማ ዐውድ ተስማምቶ የቀረበ**


**አስማምቶ አዘጋጆች**

ሳሙኤል አየለ ገብረኪዳን

ታሪኳ መላኩ ወንድሙ

**ጥራት ተቆጣጣሪ**

ፍሬህይወት አሥፋ ከበደ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለማዓቀፍ የልማት ድርጅት (United States Agency for International Development (USAID)) በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮና በREAD - TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም (General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II) ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ናቸው።

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

ISBN: 978-99944-2-545-7

# የይዘት ማውጫ


መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ) ........ iv

ምዕራፍ 1

ተፈጥሮን ማድነቅ ........ 1

ምዕራፍ 2

የቤተሰብ ምጣኔ ........ 21

ምዕራፍ 3

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ማህበራዊ ቀውሶች ........ 40

ምዕራፍ 4

ታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች ........ 63

ምዕራፍ 5

ውሃና ጥቅሙ ........ 87

ምዕራፍ 6

ማህበራዊ ግንኙነት ........ 109

ምዕራፍ 7

ሱስ ........ 134

ምዕራፍ 8

አርበኝነት ........ 156

ምዕራፍ 9

ተላላፊ በሽታዎች ........ 181

ምዕራፍ 10

ቃላዊ ግጥም ........ 208

ሙዳየቃላት ........ 231

ዋቢዎች ........ 235

# መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ)

ይህ መጽሐፍ ከ5ኛ እስከ8ኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት አካል ነው። የመጽሐፍ ዝግጅቱም፣ ተማሪዎች እንዴት ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር ፈጠራዊና አስደሳች እንዴት እንደሚሆን፣ የትምህርትቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለነዚህ የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## የሥርዓተትምህርቱ መሠረታዊ መርሖች፤

1. ተማሪዎች በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ (እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ የምንባብ ይዘትና የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል።)
2. ተማሪዎች ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡና ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመሥረት ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም።
3. ሁሉም የቋንቋ ትምህርት ከእነዚህ የምንባብ ይዘቶች፣ ርዕሰጉዳዮችና ምንባቦች ጋር የተያያዘ ነው።
4. ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በትክክል ለመግለጽ አይቸገሩም፤
5. ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ይማራሉ።
6. ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ጽሑፎችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

1. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ።
2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይኼንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ።
3. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
   - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
   - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
   - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
   - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
   - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን?
4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሟችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤
   - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
   - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
   - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?
5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።

7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ።
8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።
    - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
    - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
    - ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
    - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?
9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋልወይ? በዓርፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋልወይ? ወዘተ.
10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።
11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

## የመጽሐፍ ይዘቶች አደረጃጀት

### ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በምዕራፍ ተደራጅተው ቀርበዋል። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት፣ እያንዳንዱም የምንባብ ይዘት ሦስት ርዕሰጉዳዮችና አራት አራት ምንባቦች አሉት። የምንባብ ይዘቶቹና ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋቸው እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ እንደመነሻ ያገለግሏቸዋል።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር ተወያዩ።

## የቃላት ጥናት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን፣ የቃላቱን የተለያዩ የመዋቅር አካላት፣ ለተለያዩ አጠቃቀሞች የሚያሳዩትን የቅርጽ ለውጦች ይማራሉ።

## አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥረተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንበብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን ሰጥቶ እንዲከውኑ ማድረግ።

## ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡-

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

## መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነፃፃሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሃሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱ (እንዲያርሙ) እና ለኅትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተላያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ጽሑፎችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት ያነባሉ።

## ቃላዊ ክሂሎች፣ ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ጽሑፍ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቁልፍ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በማዳመጥ ምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሀሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

## ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።



# ተፈጥሮን ማድነቅ

# ምዕራፍ 1

## ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ ነገሮች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ማስታወሻ**

**መነጠል፣** በአንድ ቃል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች ተነጣጥለው ቀርበው የሚነበቡበት ሂደት ነው። ምሣሌ ቤተ-ሰብ

**ማጣመር፣** በአንድ ቃል ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች በአንድ ላይ የሚነበቡበት ሂደት ነው። ምሣሌ ቤተሰብ

### ተግባር

«መስህቦቻችን» ከሚለው ምንባብ ውስጥ የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

ምሣሌ፡- ቤተ-መንግሥት → ቤተመንግሥት የ-ነገሥት-አት-ን → የነገሥታትን

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እሳተ-ገሞራ | እሳተገሞራ |
| ለ | ቀስተ-ደመና | ቀስተደመና |
| ሐ | ቤተ-ክርስቲያን | ቤተክርስቲያን |
| መ | ተፈጥሮ-ኣዊ | ተፈጥሯዊ |
| ሠ | ነጎድጓድ-ኣዊ | ነጎድጓዳዊ |
| ረ | የ-ሀገር-ኣችን | የሀገራችን |
| ሰ | መስህብ-ኦች-ኣችን | መስህቦቻችን |
| ሸ | አል-አስተዋልኩ-ም | አላስተዋልኩም |
| ቀ | መልክዓ-ምድር-ኣዊ | መልክዓምድራዊ |

# ማንበብ

## መስህቦቻችን

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. መስህብ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. «መስህቦቻችን» ከሚለው ርዕስ በታች ከቀረበው ሥዕል ምን ተረዳችሁ? ምክንያት መስጠት ትችላላችሁ?


### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«መስህቦቻችን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ገላጭ ጽሑፍ፣ ለዋናዋና ሀሳቦች ትኩረት በመስጠት ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ።

## መስህቦቻችን






ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ሊያስገኙ የሚችሉ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ መስህቦች ባለፀጋ

ናት። ከተፈጥሯዊ መስህቦቿ መካከል ተራሮች፣ ፏፏቴዎች፣ ሐይቆች ብርቅዬ እንስሳት፣ የአእዋፍ ዝርያዎችና ዕፅዋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በ12ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመሬት በታች ከአንድ ወጥ አለት ተፈልፍለው የተሰሩ ዕፁብድንቅ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን መጥቀስ ይቻላል። እንዲሁም የ17ኛውና የ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የታሪክ ውጤቶች የሆኑት የጎንደር አብያተ መንግስታት ሰውሰራሽ መስህቦች ናቸው፤ በተጨማሪም የሀረር ግንብ የጥያ ትክል ድንጋይ፣ የኮንሶ መልክዓ ምድር፣ የነገስታት ታሪክ የሚያሣዩ ሀውልቶች፣ በተለያዩ ዘመናት የተሰሩ ቤተክርስቲያናት፣ ገዳማትና መስጊዶች ይጠቀሣሉ።

ኢትዮጵያ ከባህር ወለል በላይ 4620 ሜትር ከፍታ ካለው የራስ ዳሽን ተራራ ጀምሮ ከባህር ወለል በታች 116 ሜትር ዝቅታ እስካለው የዳሎል ረባዳ ቦታ ድረስ የተለያዩ መልከዓምድራዊ ገፅታዎች አሏት። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ፏፏቴዎች፣ዋሻዎችና ሰውሰራሽ ግንቦች የሀገሪቱ ድንቅ መለያዎች ናቸው። ከነዚህም መካከል የጢስ አባይ ፏፏቴ፣ ሶፍዑመር ዋሻና የሀረር ግንብ የመሣሰሉት ሁሉም የጎብኚዎችን ቀልብ የመሣብ ኃይል አላቸው።

> **ኢትዮጵያ ከራስ ዳሽን ከፍታ እስከ ዳሎል ዝቅታ ድረስ ያሏት የተፈጥሮ ገፅታዎች ውበት ሰጥተዋታል።**

የጢስ አባይ ፏፏቴ ከባህርዳር ከተማ በስተምስራቅ ይገኛል። ፏፏቴው ወደ ገደል ሲወረወር እጅግ አስገራሚና አስደሳች ስሜት ይፈጥራል። እየተጥመለመለ ወደ ገደሉ ከሚወርደው ውኃ የሚፈጠረው የውኃ ፍንጥቅጣቂ ጢስ የተባዘተ ጥጥ ይመስላል። የፏፏቴው ድምፅ የአካባቢው ልምላሜና የውሀው ጢስ የሚፈጥረው ቀስተደመና ለመንፈስ ደስታ ይሰጣል።

የጣና ሐይቅ የተፈጠረው ከብዙ ዓመታት በፊት በአንድ ወቅት በተከሰተ የእሣተገሞራ ፍንዳታ ነው። ሐይቁ 3600 ካሬ ኪሎ ሜትር ከፍታ አለው። የጣና ሐይቅ በውስጡ በሚገኙ ደሴቶች ብዙ ታሪካዊ ገዳማትን የያዘ በመሆኑ በርካታ ቱሪስቶች ይጎበኙታል። ከቱሪስቶች የሚገኘው ገቢም ለሀገራችን ምጣኔ ሀብትና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው።

የሀረር ጀጎል ግንብ የኢትዮጵያ የጥንታዊ ከተሞች ታሪክና ዕድገት ፈር ቀዳጆች አንዱ ነው። ጥንታዊቷ የሀረር ከተማ በምስራቅ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ በ525 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ስትሆን የተቆረቆረችው ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 9ኛው መቶ

> **ዋልያ፣ጭላዳ ዝንደጀሮ ቀይ ቀበሮ ብርቅዬ የሀገራችን የዱር እንስሳት ናቸው።**
>
> **ሌሎችስ ...?**

ክፍለ ዘመን እንደሆነ የታሪክ ፅሁፎች ይናገራሉ። የሀረር ከተማ ዙሪያ ግንብ አምስት በሮች ያሉት ሲሆን በውስጡም በጥንታዊ ሰዎች የተገነቡ መስጊዶች መኖሪያ ቤቶችና የዋሻ ውስጥ ስዕሎች ይገኙባቸዋል። የከተማዋ አጥር ግንብ ከ13ኛው እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተገነባ የሚነገር ነው። በመሆኑም ከተማዋ በኢትዮጵያ አንጋፋዋ የቱሪስት መዳረሻ ሆና ታገለግላለች።

የጣና ሐይቅ በውስጡ በሚገኙ ደሴቶች ብዙ ታሪካዊ ገዳማትን የያዘ በመሆኑ በርካታ ቱሪስቶች ይጎበኙታል።

በኢትዮጵያ በርካታ ብሔራዊ ፓርኮችና መስህቦች አሉ። ከነዚህም መካከል አዋሽ፣አብያታ፣ ሻላ፣ የባሌ ተራሮች፣ የሰሜን ተራሮች፣ ነጭሣር፣ ማጎ፣ ኦሞ፣ ጋምቤላ፣ አርባምንጭ የአዞ እርባታ ጣቢያ፣ ባቦሌ የዝሆን መጠለያ፣ ሰንቀሌ የቆርኪዎች መጠለያና ማዜ ብሔራዊ ፓርኮች ይጠቀሳሉ። እነዚህ መስህቦች ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣የአዕዋፍ ዝርያዎችና ሌሎችም የተፈጥሮ ብዝኃህይወት መገኛዎች ናቸው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊና ሰውሰራሽ መስህቦች ባለቤት በመሆኗ በቱሪዝም ሀብቷ ተጠቃሚ ናት። ስለዚህ እነዚህ ሀብቶች ልንጠብቃቸውና ልንከባከባቸው ይገባል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በፅሁፍ መልሱ።

ሀ. መስህቦች በስንት ይከፈላሉ? ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?

ለ. የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት አሠራር እንዴት ነው?

ሐ. የራስ ዳሸን ተራራ ከባህር ወለል በላይ ስንት ሜትር ከፍታ አለው?

መ. በኢትዮጵያ በከፍተኛው ቦታና በዝቅተኛው ቦታ መካከል ያለው ልዩነት በአህዝ ሲገለጽ ምን ያህል ነው?

ሠ. የሀገራችንን ጎብኚዎች የሚያስተናግዱ ተፈጥሯዊ መስህቦችን ጥቀሱ።

ረ. የሀረር ከተማ ከአዲስ አበባ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?

ሰ. ከምንባቡ የአድናቆት መግለጫ ቃላትን ለይታችሁ አውጡ።

ሸ. የጣና ሐይቅ በአፍሪካ ካሉት ሐይቆች ጋር በስፋቱ ሲወዳደር በስንተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል?

ቀ. ኢትዮጵያ ካሏት ሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ መስህቦች መካከል በሰፊው የተገለፀው የትኛው ነው?

በ. ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ሀብቷ ተጠቃሚ የምትሆነው እንዴት ነው?

ተ. ከራስ ዳሽንና ከዳሎል የትኛው ሞቃታማ ነው? እንዴት ይታወቃል?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሁለንተናዊ | መ. ወለል | ሰ. ብዝኃሕይወት |
| ለ. ይወረወራል | ሠ. እሳተገሞራ | ሸ. ባለፀጋ |
| ሐ. ደሴት | ረ. መስህብ | ቀ. ክፍለዘመን |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ


### በገላጭ ስልት አንቀጽ መጻፍ

**ማስታወሻ**

ገላጭ ጽሑፍ ማለት ስለ አንድ ነገር ወይም ሁኔታ ምንነት፣ አሠራር፣ አተገባበር ወዘተ. የሚገልጽ ጽሑፍ ነው።

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ማደራጃ ሠንጠረዥ በመጠቀም በገላጭ የአጻጻፍ ስልት ስለወፎች አመጋገብ አንድ አንቀጽ ጻፉ።




### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት አዳምጣችሁ ፊደላትን ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**መስህቦቻችን**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. አቀላጠፎ ማንበብ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. የማንበብ ፍጥነትን የሚያደናቅፉ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

### ማንበብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ተግባራት አከናውኑ።

ሀ. መምህራችሁ «መስህቦቻችን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አቀላጥፈው ሲያነቡላችሁ በትኩረት ተከታተሉ።

ለ. የመምህራችሁን አነባበብ በማስመሰል «መስህቦቻችን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጻችሁን እያሰማችሁ በማንበብ ተለማመዱ።

## ማዳመጥ

## የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

«የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ የሠንጠረዡን ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ።

| የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ | | |
|---|---|---|
| ስለፓርኩ የማውቀው | ስለፓርኩ ማወቅ የምፈልገው | ስለፓርኩ ያወቅሁት |
| •<br>•<br>•<br>• | •<br>•<br>•<br>• | •<br>•<br>•<br>• |

### የማዳመጥ ሂደት

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በማዳመጥ ስለፓርኩ ያገኛችኋቸውን አዳዲስ መረጃዎች «ስለፓርኩ ያወቅሁት» በሚለው ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

### አዳምጦ መረዳት

#### ተግባር

«ስለፓርኩ ያወቅሁት» በሚል የያዛችሁትን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ሀሳባችሁን በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### አያያዦች

ማስታወሻ፦

አያያዦች በሁለት ነጠላ ዓረፍተነገሮች መካከል እየገቡ ዓረፍተነገሮችን ወደድርብ ዓረፍተነገር መለወጥ የሚያስችሉ ናቸው። እነርሱም፣ እና፣ ግን፣ ነገር ግን፣ እንጂ ወዘተ. ናቸው።

### ተግባር

ቀጥሎ በተሰጡት ድርብ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን አያያዦች አስምሩባቸው።

ሀ. ደመናው ዳመነ እንጂ፣ ዝናቡ አልዘነበም።

ለ. ከድጃ ትምህርት ቤት መጣች፣ ግን ክፍል ውስጥ አልገባችም ።

ሐ. ብሩክታይት ሀኪም ናት እንጂ፣ ፖሊስ አይደለችም።

መ. ጅብሪል ድርሰት ጻፈና ለህትመት አበቃ።

ሠ. የአባይ ግድብ ሰውሠራሽ ነው እንጂ፣ ተፈጥሯዊ አይደለም።

ረ. ሮቤል የተፈጥሮ አካባቢን ማድነቅ ይወዳል፤ ኤደን ግን ልቦለድ ጽሑፎችን ማንበብ ትወዳለች።

## ማንበብ

### ጉዞ ወደሐዋሳ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

«ጉዞ ወደሐዋሳ» የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ሥዕሉን አስተውሉና ከሥዕሉ የተረዳችሁትን በቃላችሁ ግለጹ?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«ጉዞ ወደሐዋሳ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በእያንዳንዱ የጉዞ መዳረሻ ሊታዩ የሚችሉ ነገሮችን ቀድማችሁ በመተንበይ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ጉዞ ወደሐዋሳ



ዛሬ ወደሐዋሳ ይዣችሁ እጓዛለሁ። በጉዟችን የገጠሙኝን አይነግብ ክስተቶች በምናባችሁ እንድታዩዋቸው አደርጋለሁ።

የጉዞ መነሻችን ያደረግነው ከመዲናችን አዲስ አበባ ነበር። እኔና የስራ ባልደረቦቼ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ጉዟችንን ጀመርን። ከአዲስ አበባ በምስራቁ ክፍል ለቀን ለመውጣት በመስቀል አደባባይ በሳሪስ አድርገን ወደ ቃሊቲ የሚወስደውን መንገድ ይዘን ተጓዝን። ጎን ለጎን ለባቡር ተብሎ የተዘረጋው መንገድ ምን ያህል እየተጠናቀቀ እንዳለና ምን ያህል ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ላይ እንደሆነ እየተወያየን በአዲሱ ከአዲስ አበባ አዳማ (ቢሾፍቱ) በሚወሰደው የፈጣን መንገድ ወደ ቢሾፍቱ መኪናችን አየሩን እየሰነጠቀ ተጓዘ። እኛ ደግሞ የመንገዱን መመቻቸትና ከመንገዱ ባሻገር የሚዘናፈለውን የጤፍ አዝመራ በአድናቆት ተመለከትን።

የጠዋትዋ ፀሐይ በአረንጓዴው መስክ ላይ ጨረሯን በመፈንጠቋ አካባቢውን ልዩ ውበት አላብሶታል። ዱከም አካባቢ ባህር ዛፍና የግራር ዛፎች በብዛት ይታያል። አልፎ አልፎ የሚታዩት የግራር ዛፎች ልምላሜያቸውና ውበታቸው ድንቅ ነው። የየረር ተራራ በርቀት ሆኖ ሲታይ ለአካባቢው ድምቀት ሰጥቶታል። የመሬቱ ልምላሜ ቀልብ ይስባል። እዚህ አካባቢ በበጋ ረፋድ ላይ ፀሐይ ስትወጣ የተቀላቀለ ነፋሻማ አየር ስላለ ይበርዳል። እየተጓዝንም በምናየው ነገር ተገረምን።

የዱከም አካባቢ በፈጣን ሁኔታ ጨርሰን ቢሾፍቱ ደረስን። ጎራ ብለንም ቁርስ በልተን  ለቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎችን በአጭር ሰዓት ለመጎብኘት ገባን። በርካታ መሬቷ በሐይቆች የተከበበ ነው። ባለሃብቶች ሐይቆቹን ተንተርሰው ሪዞርትና ሆቴሎች በመገንባት የገቢ ምንጫቸውን አሳድገውበታል። ለአብነት ያህል ቢሾፍቱ ሪዞርት፣ ባቦጋያ ሪዞርት፣ ኩሪፍቱ ሪዞርት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እንዲሁም በርካታ አለም አቀፍ ሆቴሎች እንደሚገኙ ተመለከትን።

በመቀጠል ይህችን ውብ የቱሪስት ከተማ ለቀን ሞጆ ደረስን። በአንፃሩ ሞጆ ሞቅ ደመቅ ያለች ከተማ ናት። በግንባታ ላይ ያሉ በርካታ ተቋማት፣ ደረቅ ወደብ እና ዘመናዊ ሆቴሎችን በጉያዋ ይዛለች። የተለያዩ አረንጓዴ ተክሎች የሚታዩባት በመሆኑ «የበረሃ ገነት» አስመስሏታል።

ሞጆ ብዙም አልቆየንም ወዳሰብነው ቦታ በጊዜ ለመድረስ ጉዟችንን በፍጥነት ለማቅናት ሽምጥ ከነፍን በዚህ መሃል የሙቀቱ መጠን እየጨመረ ስለሄደ የመኪናችንን መስኮት መክፈት አስገድዶን ነበር። በመንገዳችንም የቆቃን ግድብ፣ የአዋሽ ወንዝ በሰፊው ተንሰራፍቶ ሲንከላወስ እያየን እንዲሁም በወንዙ ዳር ላይ በሚያምር ቅርፅና ሁኔታ የተደረደረውን የቲማቲም፣ የድንች፣ የሽንኩርት፣ የሃባብ፣ የወይን የመሣሠሉትን ፍራፍሬና የጓሮ አትክልቶችን እየተመለከትን ደማቋን መቂ ከተማን ተሻግረን (ባቱ) ዝዋይ ከተማ ደረስን። ለምሳም ወረድን።

(ባቱ) ዝዋይ በስሟ የሚጠራ ዝዋይ የሚባል ሐይቅ አላት። ይህ ሐይቋም ከፍተኛ የሆነ የአሣ ምርት ያስገኝላታል። በተጨማሪም እንደ ሽንኩርት፣ጥቅልጎመን፣ቆስጣ በመስኖ ይመረትበታል። በከተማዋ የአበባ ምርት እንዳለም ተመለከተናል። ይህንን ሁሉ ዓይተን ትንንሽ ከተማዎችን እንደ አርሲነገሌ፣ኩየራ፣ሻሸመኔን ጥቁር ውሃን ተሻግረን ወደ ውቢቷ ከተማ ሐዋሳ አመሻሽ ላይ ደረስን።

ሐዋሳ ሙቀቷ ከፍተኛ ቢሆንም በአረንጓዴ ተክሎች ተሸፍናለች። ከተማዋ በአስደናቂ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህቦቿ ተሞልታለች፣ የተለያዩ ብሔር ብሔረሠቦች በአንድነት በፍቅር ይኖሩባታል። በከተማዋ ዳር ላይ ተንጣሎ የሚታየው የሐዋሳ ሐይቅ በተለምዶ የፍቅር ሐይቅ እየተባለ የሚጠራው ለከተማዋ ግርማ ሞገስን ሰጥቷታል። በሐይቁዋ ዙሪያ የተለያዩ የሃገር ውስጥና የውጪ ሃገር ጎብኝዎች ይዝናኑበታል ሐይቁን ተያይዞ የአሞራ ገደል መናፈሻም አለ በዚህ መናፈሻ ደስ የሚል ትዕይንት ይታያል። ጎብኝው የአሣ ምርትን በጥሬው፣ በቅቅል፣ በጥብስ፣ በሾርባ መልክ ሲመገበው፣ የተለያዩ የዱር እንስሳት እንደ ጉሬዛ፣ ጦጣ፣ ዝንጀሮ ከጎብኝዎች እጅ ምግብ ሲቀበሉ፣ አብረው ፎቶ ሲነሱ፣ መላመዳቸውን እያዩ ወደሀይቁ እንደከፈሉትና እንደሚችሉት መጠን በመርከብ ወደ ሃይቋ ውስጥ በመጓዝ በመሽራሽር ትልቅ ደስታን ተችረውና ተዝናንተውበት የሚወጡበት የተፈጥሮ ምድረ ግቢ ነው።

በአጠቃላይ ወደሐዋሳ ባደረግነው ጉዟችን የተመለከትነው መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ድንቅ ነው። በዚህ የተነሣ ነዋሪዎቿ «ውበቷ ሐዋሳ» በማለት ይጠሯታል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ጻፉ።

ሀ. ትረካው ወደሐዋሳ ይዞን የሄደው በምንድን ነው?

ለ. ሙቀቱ የጨመረው ከየት ጀምሮ ነው?

ሐ. የሞጆ ከተማ «የበረሃዋ ገነት» የተባለችበት ምክንያት ምንድን ነው?

መ. ጎብኚዎች ዘዋይ ከተማ እንደደረሱ ምን ምን ዓይነት እፅዋትና የጓሮ አትክልቶችን ተመልከቱ?

ሠ. ከፈጣኑ መንገድ ላይ ሆኖ የሚታየው ተራራ ስሙ ማን ይባላል?

ረ. ከምንባቡ ውስጥ ያሉ የአድናቆት ቃላትን ወይም ሐረጋትን ለይታችሁ አውጡ።

## ተግባር 2

«ጉዞ ወደሐዋሳ» የሚለውን ምንባብ በአንድ አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

# 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

## ተግባር

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ዐውዱን መሠረት በማድረግ ተመሳሳይ ፍቺ በ«ለ» ረድፍ ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ድንቅ | ሀ. በራ |
| 2. ዓይነገብ | ለ. ወደጎን |
| 3. ፈነጠቀ | ሐ. የሚወዛወዝ |
| 4. ምናብ | መ. ምቹ |
| 5. መስህብ | ሠ. ማራኪ |
| 6. ገነት | ረ. ሳቢ |
| 7. ባልደረባ | ሰ. ሀሳብ |
| 8. የሚዘናፈል | ሸ. ውብ |
| | ቀ. ጓደኛ |
| | በ. ከፍተኛ ብርሃን |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በገላጭ ስልት አንቀጽ መጻፍ

## ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም፣ «ስለወፎች አኗኗርና አረባብ» በገላጭ የአጻጻፍ ስልት ሁለት አንቀጾችን ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

መምህራችሁ በቃል የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች ፊደላትን ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

### ጉዞ ወደሐዋሳ

## ቅድመንባብ

«ጉዞ ወደሐዋሳ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንቀጽ ሁለትን መምህራችሁ በሁለት ዓይነት መንገድ ያነቡላችኋል፤ ተከታተሉ።

## ማንበብ

### ተግባር

ካዳመጣችኋቸው አነባበቦች መካከል በተሻለው መንገድ አንቀጽ ሁለትን አንብቡ።

# መናገር

## አካባቢን በማድነቅ መናገር

እስካሁን በተለያዩ አጋጣሚዎች አይታችሁ ስላደነቃችኋቸው አካባቢዎች ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

# ሰዋስው

## ድርብ ዓረፍተነገሮችን መነጠል

### ተግባር

አያያዦችን በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮች ተመሥርተዋል። እነዚህን ድርብ ዓረፍተነገሮች በመነጣጠል የተለያዩ ነጠላ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

ምሣሌ

«ድሬዳዋ ከተማ ሞቃት የአየር ፀባይ አላት፤ ነገር ግን ከሰዓት በኋላ ነፋሻ አየር ይነፍስባታል» የሚለው ዓረፍተነገር «ድሬዳዋ ከተማ ሞቃት የአየር ፀባይ አላት»ና «ድሬዳዋ ከተማ ከሰዓት በኋላ ነፋሻ አየር ይነፍስባታል» የሚሉ ሁለት ነጠላ ዓረፍተነገሮችን ይዟል።

ሀ. አዲስ አበባ ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ አላት፤ ይሁን እንጂ የአየር ፀባይዋ ለኑሮ ተስማሚ ነው።

ለ. ልጁ ልብሱን አጥቧል፤ ነገርግን ልብሱ በሚገባ አልፀዳለትም።

ሐ. አፈርና ውኃ ለኑሯችን አስፈላጊዎች ናቸው፤ ስለዚህ ለአፈርና ውኃ አስፈላጊውን እንክብካቤ እናድርግላቸው።

መ. የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ሰፊ ነው፤ እንዲሁም አስደሳች ነው።

ሠ. አባትየው ልጁን ወደሽርሽር ቦታ ወሰደው፤ ልጁ ደግሞ የጎበኘውን ቦታ አደነቀ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እንደ-አይወሰድ-ና | እንዳይወሰድና |
| ለ | እንደ-ሚያሳይ-ኡ-ት | እንደሚያሳዩት |
| ሐ | እንደ-አይ-ሸረሸር-ና | እንዳይሸረሸርና |
| መ | ንጥረ-ነገር-ኦች | ንጥረነገሮች |
| ሠ | የሚያመርት-ኡ-ት | የሚያመርቱት |
| ረ | ቅጠል-ኣ-ቅጠል-ኦች | ቅጠላቅጠሎች |
| ሰ | የሚንደረደር-ኧ-ው-ን | የሚንደረደርውን |

## ማንበብ

### የአፈር እንክብካቤ

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. «የአፈር እንክብካቤ» ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ከሥዕሉ የተገነዘባችሁት ሀሳብ ምንድን ነው?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**


«የአፈር እንክብካቤ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በማንበብ በየአንቀጹ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦችን በደብተራችሁ ጻፉ።

## የአፈር እንክብካቤ

የተፈጥሮ ሀብቶች ከሚባሉት መካከል አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። አፈር የሰብል ምርት ለማምረት፣ የካርቦን ልቀትን ለመምጠጥ፣ ንጥረነገሮችንና ውኃን ጠብቆ ለመያዝ ይጠቅማል። አፈር ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ፍጥረታት ጠቀሜታው የጎላ ነው። ኑሮን ለማሻሻል ከፍተኛ ድርሻ አለው። ስለሆነም አፈር እንደሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ውስን ሀብት በመሆኑ በእንክብካቤ ሊያዝ ይገባል።

በኢትዮጵያ፣ በተለይም ደጋማ በሆኑ ከፍተኛ ቦታዎች፣ አፈሩ በሰዎች አያያዝ ጉድለት እየተራቆተ ነው። በመራቆቱም አፈሩ ውኃ የማከማቸት አቅሙ ውስን ሆኗል። የአፈር ክምችቱ ስስ፣ መሬቱ አለታማና ለካልሲየም ካርቦኔት እጥረት የተጋለጠ ነው። በዚህ ምክንያት በደጋማው ከፍተኛ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ሰብል የሚያመርቱት ሰውሠራሽ በሆኑ የማዳበሪያ ውጤቶች በመጠቀም ነው። ማዳበሪያ የማይጠቀሙት ግን የሚያመርቱት የምርት መጠን ዝቅተኛ ነው።

የአፈር ለምነትን ለመጨመር ረጅም ጊዜ ይወስዳል። አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሣዩት አንድ ሳንቲ ሜትር ለም አፈር ለመጨመር አንድ ሺህ ዓመት ሊፈጅ ይችላል። የአፈር ለምነትን መጨመር የሚቻለው ደግሞ አፈርን ለመሥራት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።



አፈር በጎርፍና በነፋስ እንዳይወሰድና ለምነቱን እንዳያጣ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል። አንዱና የመጀመሪያው አማራጭ ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን ነው። በዚህም ዛፎች አፈር በጎርፍ እንዳይሸረሸርና

በነፋስ እንዳይጠረግ መከላከል ይችላሉ። ዛፎች በሥራቸው አማካይነት አፈሩን ቆንጥጠው መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር ያደርጋሉ። ለምሣሌ ከፍተኛ ዝናብ በሚጥልበት ወቅት ሀይሉን በመቆጣጠር አፈሩ እንዳይታጠብ ይከላከላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ዛፎች የአፈርን ለምነትና ውፍረት በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። የዛፎች መኖር፣ አፈር በንጥረነገሮች እንዲዳብር ያደርጋል። ከዛፎች የሚረግፉት ቅጠላቅጠሎች ወደብስባሽ ስለሚለወጡ የአፈር ለምነትን ይጨምራሉ። ስለዚህ ተራራማ ቦታዎችን በደን በመሸፈን የአፈር መከላትን በመከላከል ለምነትን መጨመር ይቻላል።

በተጨማሪም በዳገታማ ቦታዎች ላይ እርከንና ክትር በመሥራት አፈርን ከመከላት ማዳን ይቻላል። ዳገታማ መሬቶችን አግድም በማረስ፣ በድንጋይና በአፈር እርከን በመሥራት፣ አፈሩ በጎርፍ ታጥቦ እንዳይሄድ ማድረግ ይቻላል። ይህም ከከፍተኛ ቦታ የሚንደረደረውን ጎርፍ እርከኑ ላይ እንዲያርፍና ደለል እንዲሠራ ያደርጋል። እርከኑ ላይ ያረፈው አፈርም ውኃ መቋጠር ስለሚችል ለምነት ይኖረዋል። እርከኑ አፈሩ ተረጋግቶ እንዲቀመጥ ያደርጋል። ለረዥም ጊዜ በጎርፍ ምክንያት ገደላማ በሆኑ ቦታዎች ላይ ደግሞ ክትር በመስራት የጎርፍ ፍጥነትን መግታትና አፈር ታጥቦ ወደሌላ ቦታ እንዳይሄድ መከላከል ይቻላል።

የጥራጥሬ እህሎችን (አተር፣ ባቄላ፣ ጓያ፣ ሽንብራና የመሳሰሉትን) አፈራርቆ በመዝራትም የአፈር ለምነትን መጠበቅ ይቻላል። እነዚህን የጥራጥሬ እህሎች በሌሎች ሰብሎች መካከል በየዓመቱ አፈራርቆ መዝራት አፈሩ በተለያዩ ንጥረነገሮች እንዲበለፅግ በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣል።

ከዚህም ሌላ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ የመሬት አጠቃቀምና አያያዝ ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል። መሬትን ለእርሻ፣ ለደን ልማት፣ ለግጦሽ በማለት ከፋፍሎ በሥርዓት መጠቀም የመሬት ለምነትን ይጨምራል። ይህ ሲሆን አፈር ያለአግባብ አይባክንም።

በአጠቃላይ አፈር ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ የሆነ ውስን ሀብት ስለሆነ በእንክብካቤና በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።

(መብራቱ ይበልሀ። 2006። *ኢ.ዜ.አ. ድረገጽ።* መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለትና ምክንያት በመስጠት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አፈር ውስን የተፈጥሮ ሀብት ነው።

ለ. ደጋማ አካባቢ ያለው አፈር ለም ስለሆነ ለሰብል ምርት ምቹ ነው።

ሐ. ተራራማ ቦታዎችን በደን መሸፈን አፈር እንዳይሸረሸር ያደርጋል።

### ተግባር 2

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ጻፉ።

ሀ. አፈር ሕይወትን ለማስቀጠል የሚያስችል የተፈጥሮ ሀብት የተባለው ለምንድን ነው? አብራርታችሁ ጻፉ።

ለ. የአፈር ለምነትን ከምንጠብቅባቸው ዘዴዎች መካከል ሁለቱን መርጣችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ማብራሪያ ስጡ።

ሐ. ከምንባቡ ከተጠቀሰው በተጨማሪ የአፈር ለምነትን ሊጨምሩ የሚችሉ ነገሮችን አብራርታችሁ ግለጹ።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ቀጥሎ በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በ«ለ» ረድፍ ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ለም | ሀ. የተፈጥሮ ማዳበሪያ |
| 2. ብስባሽ | ለ. ለማስተካከል |
| 3. እርከን | ሐ. ይዘው |
| 4. ክትር | መ. የመጀመሪያ |
| 5. መራቆት | ሠ. የተሸረሸረ |
| 6. ቀዳሚ | ረ. ካብ |
| 7. ለማሻሻል | ሰ. መጠረግ |
| 8. ቆንጥጠው | ሸ. የዳበረ |
| | ቀ. ግድብ |
| | በ. አላቂ ሀብት |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በገላጭ ስልት አንቀጽ መጻፍ

**ተግባር**

1ኛ ሳምንት በ2ኛው ቀንና በ2ኛው ሳምንት 5ኛው ቀን የጻፋችኋቸውን ሦስት አንቀጾች ከልሳችሁ እንደገና ጻፏቸው።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች፣ ፊደላትን ሳትገድፉና ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን ሳታጓድሉ በትክክል ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የአፈር እንክብካቤ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

አፈርን መንከባከብ ለምን እንደሚያስፈልግ የምታስታውሱትን ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«የአፈር እንክብካቤ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያውን አንቀጽ አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ በማዳመጥ በሚከተለው ቅፅ ላይ ይህን «✓» ምልክት በማድረግ እርስበርስ ተገማገሙ።

| ቃላትን ያለአግባብ መደጋገም | | | | አገላለጽ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የአንባቢ ስም | ከ1-2 ቃል ስህተት ዝቅተኛ | ከ3-4 ቃል ስህተት መካከለኛ | ከ4 በላይ ቃላት ስህተት ከፍተኛ | ጥሩ | በጣም ጥሩ | እጅግ በጣም ጥሩ |
| | | | | | | |

## መናገር

### በመረጃ የተደገፈ ንግግር

#### ተግባር

የአፈር ለምነትን ለመጨመር ከሰውሠራሽ ማዳበሪያና ከተፈጥሮ ማዳበሪያ የተሻለው የትኛው እንደሆነና ለምን እንደተሻለ ከግብርና ባለሙያ ጠይቃችሁ በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ድርብ ዓረፍተነገሮችን መመሥረት

#### ተግባር

ቀጣዮቹን አያያገሮች በትክክል በመጠቀም ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረቡትን ነጠላ ዓረፍተነገሮች ወደድርብ ዓረፍተነገር ለውጡ።

| እና | ይሁንእንጂ | ነገርግን | ግን |
|---|---|---|---|

ሀ. አፈር ሕይወት የለውም።

አፈር ሕይወትን ያለመልማል።

ለ. አስቴር ወንድም አላት።

አስቴር እህት የላትም።

ሐ. ሀሰን እግርኳስ ተጫወተ።


አበራ ወደገበያ ሄደ።

መ. ሀዋ ደብተሯን አዘጋጀች።

ጋሻው ወደትምህርትቤት ሄደ።

ሠ. ሀሊማ በጥሩ ሁኔታ አጠናች።

ሀሊማ ፈተናውን አለፈች።



# የቤተሰብ ምጣኔ

ምዕራፍ 2

## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ. | የሚ-ያስፈልግ-ኣቸው-ን | የሚያስፈልጋቸውን |
| ለ. | ዳያ-ፍራም | ዳያፍራም |
| ሐ. | ኖር-ፕላንት | ኖርፕላንት |
| መ. | ኢ.ም-ፕላንት | ኢ.ምፕላንት |
| ሠ. | ኤክስ-ቴን-ሽን | ኤክስቴንሽን |
| ረ. | ኮንትራ-ሴፕ-ቲቭ | ኮንትራሴፕቲቭ |
| ሰ. | ዳይፖ-ፕሮ-ቤራ | ዳይፖፕሮቤራ |

## ማንበብ

### የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. በምንባቡ ከቀረቡት ሥዕሎች ምን እንደተገነዘባችሁ በቃላችሁ ግለጹ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በዋናና በዝርዝር ሀሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማስተዋል ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት


እንደምንናችሁ ውድ እናቶችና አባቶች? ደህና ሰነበታችሁ? ኧ … ምህረት የሺጥላ እባላለሁ! በዚህ ወረዳ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያ ነኝ። ኧ … በጥሪያችን መሠረት ሰዓቱን አክብራችሁ በመገኘታችሁ ከልብ አመሰግናለሁ። በጋራ የተገናኘነው ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደል? መቼም ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እንዳደረጋችሁ እገምታለሁ። እሺ! እናቶቼና አባቶቼ! ዛሬ ደግሞ ጤና ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሃሳቦችን አቀርብላችኋለሁ።



የቤተሰብ ምጣኔ ማለት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር የመመጠን ልምድና በውልደት መካከል ያለውን የጊዜ ርዝመት የመወሰን ጉዳይ ማለት ነው። ለማብራራት ያህል በቤተሰብ ውስጥ የልጆች ቁጥር መመጠን ማለት ወላጆች በእንክብካቤ ማሣደግ የሚችሏቸውን ልጆች ብቻ ወስነው መውለድ ማለት ነው። አይደለም እንዴ? ኧ…ብልህ የሆኑ ባልና ሚስት እኮ ስለኑሯቸው ይወስናሉ። እንዲያውም ሰዎች በህይወታቸው ከሚወስኗቸው ጠቃሚ ውሣኔዎች መካከል ስንት ልጆች መውለድ እንዳለባቸው መወሰን አንዱና ዋነኛው ነው። እናንተስ? ኧ… በየቤታችሁ የልጆቻችሁን ቁጥር ወስናችሁ ታውቃላችሁ? እንዳልኳችሁ ይህ እኮ ትልቅ ነገር ነው። እስቲ በጥሞና ተከታተሉኝ።

ኃላፊነት የሚሰማቸው ወላጆች እኮ… ለሚወልዷቸው ልጆች የሚያስፈልጓቸውን እንክብካቤ፣ ፍቅርና ድጋፍ መስጠት ይፈልጋሉ። እናንተስ? እናንተም ኃላፊነት እንደሚሰማችሁ እተማመናለሁ። ለማንኛውም የልጆችን ቁጥር ለመወሰን ስለሚያስችሉ ዘዴዎች እንነጋገራለን።

እንግዲህ ስለቤተሰብ ምጣኔ ስናነሳ የልጆችን ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለድ የሚያስችሉ ሁለት ዘዴዎች እንዳሉ ማወቅ ይኖርብናል። እነሱም ተፈጥሯዊና ዘመናዊ ዘዴዎች ይባላሉ። ሁለቱም እርግዝናን ይከላከላሉ። ተፈጥሯዊ ዘዴዎች የሚባሉት ከግንኙነት መታቀብ፣ ቀን መቁጠርና ጡት ማጥባት ናቸው። ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎች ደግሞ ኮንዶም (የወንድና የሴት)፣ ዳያፍራም (ብራንፊ)፣ እንክብል፣ ሉፕ፣ በመርፌ የሚሰጥ መከላከያ (ዳይፖፕሮቤራ) እና በክንድ የሚቀበር (ኖርፕላንት ኮንትራሴፕቲቭ ኢምፕላንት) እና የመመሳሰሉት ናቸው። አያችሁ? እንግዲህ እናንተም ከነዚህ ዘዴዎች አንዱን መርጣችሁ እንደምትጠቀሙ ተስፋ አደርጋለሁ።



እንግዲህ ሀሳቤን ላጠቃል። እናንተ መገንዘብ የሚገባችሁ ዋናው ጉዳይ ኧ… የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ኧ… ወላጆች መቼ ልጅ ይ…ኑረን? እና ኧ… ስንት ልጅ ይኑረን? ብለው ምላሽ የሚሰጡበት ዕቅድ መሆኑ ነው። ይህንንም ተረድታችሁ ከዛሬ ጀምሮ ከባለቤታችሁ ጋር ተወያዩና ወደጤና ጣቢያ በመምጣት ኧ… አገልግሎቱን በሕክምና ባለሙያ ድጋፍ መጠቀም ትችላላችሁ። በተረፈ ዛሬ በውይይቱ ላልተካፈሉ ለምታውቋቸው እናቶች ሁሉ ፍሬነገሩን ባገኛችሁት አጋጣሚ እንድታስረዱ ኧ… አደራ እያልኩ ለዛሬ ገለፃዬን በዚሁ አበቃሁ። ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ። በሌላ ጊዜ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ተናጋሪዋ ስለቤተሰብ ምጣኔ ምንነት ምን በማለት ገለፁ?

ለ. የልጆችን ቁጥር መመጠን ለምን አስፈለገ?

ሐ. የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ተፈጥሯዊና ዘመናዊ የተባሉት በምን ምክንያት ነው?

መ. ተናጋሪዋ «ይህ እኮ ትልቅ ነገር ነው» ሲሉ «ይህ» የሚለው ምንን ያሳያል።

ሠ. ወላጆች የወሊድ መቆጣጠሪያን ለመጠቀም ማንን ማማከር አለባቸው?

ረ. ተናጋሪዋ የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላችኋል?

ሰ. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በሦስት ዓረፍተነገሮች ግለጹ።

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዓውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

እንክብል → በአፍ የሚወሰድ የወሊድ መከላከያ

ሀ. የቤተሰብ ምጣኔ (አንቀጽ 2)

ለ. መመጠን (አንቀጽ 2)

ሐ. ጥሞና (አንቀጽ 2)

መ. ዘመናዊ ዘዴዎች (አንቀጽ 4)

ሠ. ቀን መቁጠር (አንቀጽ 4)

ረ. ዕቅድ (አንቀጽ 5)

ሰ. መገንዘብ (አንቀጽ 5)

ሸ. ላልተካፈሉ (አንቀጽ 5)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን ቢጋር ማዘጋጀት

**ተግባር**

«የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት» የሚለውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ አሟሉ።

**የቤተሰብ ምጣኔ**

| ምንነት | አለመጠቀም |
| --- | --- |
| • በአንድ ቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው ልጆች መጠን<br>•<br>• | • ሕጻናት እንክብካቤ ማጣት<br>•<br>• |
| **የሚያገለግሉ ዘዴዎች** | **ጠቀሜታ** |
| • ተፈጥሯዊ ዘዴ<br>•<br>• | • ልጆች በእንክብካቤ ያድጋሉ<br>• |

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችና አገልግሎታቸው

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ያሉትን ሥርዓተነጥቦች በስም ከለያችሁ በኋላ አገልግሎታቸውን በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ሀሎ! እንደምን አለሽ? እኔ ደህና ነኝ።

ለ. ከፊቴ ጥፉ!

ሐ. «የተማረ ሰው ወድቆ አይወድቅም» አሉ አቶ ሃምዛ።

መ. እሰይ! ደግ አደረግህ!

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

«የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት» ከሚለው ምንባብ የምታስታውሱትን ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

«የቤተሰብ ምጣኔ ምንነት» የሚለውን ምንባብ ከአንቀጽ አንድ ጀምራችሁ ለአንድ ደቂቃ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡና ምን ያህል ቃላት እንዳነበባችሁ በመቁጠር ለመምህራችሁ ንገሩ።

# ማዳመጥ

## ሥነተዋልዶና ጤና

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

ለሚከተለው ጥያቄ በቃላችሁ መልስ ስጡ።

«ሥነተዋልዶና ጤና» ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

«ሥነተዋልዶና ጤና» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በትኩረት አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።

ሀ. «ሥነተዋልዶና ጤና» በሚል ርዕስ ያዳመጣችሁትን የማዳመጥ ምንባብ ፍሬሃሳቦች በቃላችሁ ግለጹ።

ለ. ለእናቶችና ለህፃናት ጤንነት ሲባል የተወለዱ ህፃናት ሁለት ዓመት ሳይሞላቸው ወላጆች ሌላ ልጅ መውለድ የለባቸውም የተባለው ለምንድን ነው?

ሐ. ሕፃናት በእንክብካቤ እንዲያድጉ ከህብረተሰቡ ምን የሚጠበቅ ይመስላችኋል?

## ሰዋስው

### ጥገኛ መስተፃምር

ማስታወሻ፦

ጥገኛ መስተፃምር አንድን ዓረፍተነገር ግሱ እንዳያሥር አድርጎ ከሌላ ዓረፍተነገር ጋር እንዲጠጋ የሚያደርግ ነው። ከእነዚህም መካከል ስለ- እንደ- ከ- ለ- ይገኙበታል።

### ተግባር

በጥንድ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በጥገኛ መስተፃምር በማጣመር ድብልቅ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሣሌ፦

አህመድ ቶሎ መጣ።
አህመድ ደብተሩን አገኘ።
→ አህመድ ቶሎ <u>ስለመጣ</u> ደብተሩን አገኘ።

ሀ. ጋሻው በሰዓቱ ሥራውን አጠናቀቀ።

ጋሻው በጊዜ ወደቤቱ አመራ

ለ. ፋጡማ ከጓደኞቿ ጋር ተባበረች።

ፋጡማ ሥራዋን በጥሩ ሁኔታ ታከናውናለች።

ሐ. አቶ አለማየሁ የወረዳችን እናቶችና ሕጻናት ባለሙያ ሆነ።

አቶ አለማየሁን ስለቤተሰብ ምጣኔ እጠይቀዋለሁ።

## ማንበብ

### ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች

**ቅድመንባብ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ**

**ተግባር**

ከዚህ በታች በቀረቡት አባባሎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. ልጅ ሀብት ነው ።

ለ. ልጅ በዕድሉ ያድጋል።

**የማንበብ ሂደት**

**ተግባር**

ቀጥሎ «ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በማንበብ ተናጋሪው ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት ተገንዘቡ።

### ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች

ውድ የስብሰባው ተሣታፊዎች! እንደምናችሁ? እ… ሰሚራ መሐመድ እባላለሁ። የእናቶችና የሕፃናት ሀኪም ነኝ። ዛሬ በዚህ ቦታ ለተገኛችሁ ጎልማሶች ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች ትምህርት እንድሰጥ በጎልማሶች ትምህርት አስተባባሪ በመጋበዜ አመሰግናለሁ። እናንተም ትምህርቱን ለመከታተል እዚህ በመገኘታችሁ ኧ… ከልብ አመሰግናችኋለሁ።

አያችሁ! የቤተሰብ ምጣኔ በቤት ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸውን የልጆች ቁጥር ለመመጠንና አራርቆ ለመውለድ ያስችላል። በተጨማሪም ልጆችን በእንክብካቤ ለማሣደግና የእናቶችን ጤንነት ለመጠበቅ ይረዳል። እ…ኑሮንም በአግባቡ ለመምራት ጠቀሜታ አለው። ይሁን እንጂ ስለቤተሰብ ምጣኔ ሰዎች የተለያዩ አመለካከቶች አሏቸው።

እ… አንዳንድ ሰዎች ስለቤተሰብ ምጣኔ በጎ አመለካከት የላቸውም። በተለይ እንደእኛ ባሉ ታዳጊ ሀገሮች አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ብዙ ሊሆኑ

ይችላሉ። ይህንን በስፋት ከሚነገሩት አስተያየቶች መረዳት ትችላላችሁ። ከእነዚህ አስተያየቶች መካከል እ... «የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም መሃን ያደርጋል» የሚለው አንዱ ነው። በዚህ አባባል ትስማማላችሁ? እንዴት መሰላችሁ እ... የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት መጠቀም ልጅ መውለድ በማይፈለግበት ጊዜ ብቻ ላለመውለድ የሚያገለግል ዘዴ ነው። መውለድ ሲፈለግ ደግሞ ከጤና ባለሞያ ጋር ተነጋግሮ አገልግሎቱን በማቋረጥ ልጅ መውለድ ይቻላል። የቤተሰብ ምጣኔ ከመሃንነት ጋር የሚያያዝ አይደለም። መሃንነትንም አያስከትልም። ግልፅ ነው? በጣም ጥሩ።

ሌላው አመለካከት ደግሞ የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም «ልጆችን እንደመግደል ስለሚቆጠር ኃጢያት ነው» የሚል ነው። ይህንን አባባል ስንቶቻችሁ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እ ... የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ልጅ ከመፀነሱ በፊት የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ስለዚህ ፅንስን እንደመግደል ተቆጥሮ እንደጨካኝና እንደኃጢያተኛ የሚያስቆጥር አይደለም።

ሦስተኛው አመለካከት ምን መሰላችሁ? እ ... «ልጅ በዕድሉ ያድጋል» የሚለው ነው። ይሁን እንጂ ልጆች ከተወለዱ በኋላ የቤተሰብ ድጋፍና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው ከሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርሱ አይችሉም። እ ... ስለዚህ ልጆችን መጥኖ መውለድ በእንክብካቤ ለማሣደግ ጠቃሚ ነው። ኧረ ስንቱ... አንድ ልጨምር።

በገጠሩ አካባቢ የሚኖሩ ወላጆች ልጆችን እንደ ... ገቢ ምንጭ በመቁጠር የቤተሰብ ምጣኔን ሲያጣጥሉት ይታያል። እ ... ልጆችን እንደገቢ ምንጭ መቁጠር ማለት ወሊድን ከመቆጣጠር ይልቅ በብዛት በመውለድ ጉልበታቸውን ለመጠቀም መፈለግ ነው። ይህ እኮ በጣም የሚገርም ነው! ይህ አመለካከት ልጆች ያለዕድሜያቸው በሥራ እንዲጠመዱና ከወላጆቻቸው ማግኘት የሚገባቸውን ድጋፍና እንክብካቤ እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል። ለእንግልትም ይዳርጋቸዋል።መቼም ዘርዝሬ አልጨርሰውም። አንድ ልጨምርና ላብቃ።

እም ... አንዳንድ ቤተሰቦች ደግሞ ልጆቻቸውን እንደጧሪ ቀባሪ በመቁጠር፣ «ዘር ማብዛት ይገባል» ይላሉ፤ በተጨማሪም ሁለቱን ጾታዎች ለማግኘት፣ ማለትም ሴት ያላቸው ወንድ ለማግኘት፣ ወንድ ያላቸው ደግሞ ሴት ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፉም።

በአጠቃላይ ቀደም ብዬ እንደነገርኳችሁ የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያዩ አመለካከቶች ምክንያት የቤተሰብ ምጣኔን አይደግፉም። እንደዚህ ዓይነት አመለካከት ካላቸው ሰዎች የሚወለዱ ልጆች በዕድሜያቸው ማግኘት የሚገባቸውን ነገር ስለማያገኙ ለበርካታ ችግሮች ይዳረጋሉ። ራሳቸውም ተጠቃሚና ደስተኛ አይሆኑም። ግልፅ ነው? እ ... ደህና ዛሬ በቤተሰብ ምጣኔ አጠቃቀም ረገድ ስላሉ የተለያዩ አመለካከቶች ተወያይተናል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በተመሳሳይ

ትምህርት እንድሰጥ ከተጋበዝኩ ልንገናኝ እንችላለን። ለዛሬው ተሳትፏችሁ በጣም አመሰግናለሁ! ደህና ሁኑ!

(አብክመ ትምህርት ቢሮ። 2002። *ሥነህዝብና የቤተሰብ ሕይወት።* ገጽ190-194 መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት ምክንያት በመስጠት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የቤተሰብ ምጣኔ መጠቀም ልጆችን መጥኖ ለመውለድ ይረዳል።

ለ. ብዙ ሰዎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በአሉታ ይመለከቱታል።

ሐ. «የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን መጠቀም ለመሃንነት ይዳርጋል» በሚለው ሀሳብ ብዙ ሰዎች ይስማማሉ።

መ. ልጆችን እንደገቢ ምንጭ የሚቆጥሩ በገጠር የሚኖሩ ወላጆች ናቸው።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «አንዳንድ ወላጆች ሁለቱንም ጾታ ለማግኘት ሲሉ የቤተሰብ ምጣኔ አይደግፉም» ከሚለው አገላለጽ ምን ተገነዘባችሁ?

ለ. ስለቤተሰብ ምጣኔ በአሉታዊነት ከተዘረዘሩት አመለካከቶች መካከል ምናልባት እናንተ በአዎንታ የምትመለከቱት ካለ ግለጹ።

ሐ. የቤተሰብ ምጣኔ ለወላጆችና ለልጆች የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

መ. የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ የማኅበረሰቡ አመለካከቶች ምን ምን ናቸው?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቻቸውን ጻፉ።

ምሣሌ፡- ዘር ⟶ ልጅ

ሀ. የገቢ ምንጭ
መ. መቁጠር
ሰ. መጠቀም
ለ. እንግልት
ሠ. እንክብካቤ
ሐ. ጧሪ
ረ. መሃንነት

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና ዝርዝር ሀሳቦች የተዋቀረ አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

1ኛ ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን በቢጋር ሠንጠረዡ ያሰፈራችኋቸውን ሀሳቦች በዋናና ዝርዝር ሀሳቦች ስልት አንቀጽ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ወሊድን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። እነዚህን ዘዴዎች በአጠቃላይ በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን። ዘዴዎቹ በሁለት የሚከፈሉት ከመከላከያ የጊዜ ርዝማኔያቸው አንጻር ነው። በመሆኑም የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች በመባል ይከፈላሉ። የአጭር ጊዜ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች የሚባሉት ኮንዶምና ዲያፍራም ሲሆኑ፣ የረዥም ጊዜ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎች የሚባሉት በክንድ ላይ የሚቀበርና በማህፀን የሚቀመጥ እንዲሁም የሚዋጡ እንክብሎችን ያጠቃልላሉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

#### ተግባር

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. መማር መማር አሁንም መማር ብሏል ሌኒን

ለ. ውይ ለምን ሳታንኳኳ ገባህ

ሐ. ሱቁ ጧት ከ2፡30-4፡45 ክፍት ነው

መ. ትርፍ አንጀት ስላመመው ኦፕራሲዮን ሆነ

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

**ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች**

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን «ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሱትን ፍሬ ሐሳቦች ባጭሩ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«ስለቤተሰብ ምጣኔ የተለያዩ አመለካከቶች» ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንቀጽ አንድን አንዳችሁ አንባቢ አንዳችሁ አድማጭ በመሆን በየተራ አቀላጥፋችሁ በማንበብ ስለንባብ ፍጥነታችሁና በትክክል ስለማንበባችሁ አስተያየት ስጡ።

# መናገር

### የተገነዘቡትን በራስ አባባል መግለጽ

**ተግባር**

ስለቤተሰብ ምጣኔ ያሉ አሉታዊ አመለካከቶች ከምን የተነሳ ሊመነጩ እንደቻሉ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በማቅረብ ተናገሩ።

# ሰዋስው

### አያያዦችን መጠቀም

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች በክፍት ቦታው በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟሉ።

እና፣ ግን፣ ነገርግን፣ እንጂ፣ ይሁንእንጂ፣ ስለዚህ

ምሳሌ፡-

1. ፋጡማ ጎበዝ ናት፤ _ነገርግን_ ፈተናውን አላለፈችም።

2. ዳዊት ንቁ አዕምሮ አለው፤ *ስለዚህ* ነገሮችን ቶሎ ይገነዘባል ።

ሀ. ዮናስ በጣም ጥሩ ውጤት አመጣ፤ __________ ተሸለመ።

ለ. ትምህርቱ ጠቃሚ ነበር፤ __________ ብዙ ሰው በተገቢው አልተከታተለውም።

ሐ. ስለቤተሰብ ምጣኔ ሁልጊዜ በሬዲዮ ይነገራል፤ __________ ብዙ ሰዎች ወሊድን በመመጠን በኩል ግንዛቤን አግኝተዋል።

መ. ብዙ እናቶች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው፤ ጥቂቶች __________ ተጠቃሚ አይደሉም።

ሠ. የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ እኔና እሱ ያለን ግንዛቤ ተቀራራቢ ነው፤ __________ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ልዩነት ይታይብናል።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | የሚ-ያደርስ-ኣቸው-ን | የሚያደርሳቸውን |
| ለ | ተ-ደንግገው-ኣል | ተደንግገዋል |
| ሐ | የሚ-ያገለግል-ኡ-ት | የሚያገለግሉት |
| መ | አ-ይጠበቅ-ባቸው-ም | አይጠበቅባቸውም |
| ሠ | ይኖር-ብ-ኣቸው-ኣል | ይኖርባቸዋል |
| ረ | ዓለም-አቀፍ-ኣዊ | ዓለማቀፋዊ |

## ማንበብ

## የሕፃናት እንክብካቤ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በያዙት ሀሳብ ላይ ተወያዩ።

ሀ. የሕፃናት እንክብካቤ
ለ. ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች
ሐ. ሰውሠራሽ አደጋዎች
መ. ሥነልቦና
ሠ. መብት

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የሕፃናት እንክብካቤ» የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

# የሕፃናት እንክብካቤ

ውድ እንግዶች! እንደምን ሰነበታችሁ? ... አቶ ኢማም አብዶ እባላለሁ፤ የሥነዜጋና ሥነምግባር መምህር ነኝ። ዘወትር በየሣምንቱ በዚህ ሰዓት እየተገናኛችሁ የማህበረሰብ ውይይት እንደምታደርጉ ስለሰማሁ ነው ዛሬ ... ከእናንተ ጋር ስለሕፃናት እንክብካቤ ... ለመወያየት የተገኘሁት። በመጀመሪያ ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ሀሳብ ልስጣችሁ። እም... በዚህም መነሻነት ውይይት እናደርጋለን።

እም... የሕፃናት እንክብካቤ ሲባል የሕፃናትን ጤንነት <u>በመጠበቅ</u> ለሞት የሚያደርሳቸውን አደጋ መቀነስን ይመለከታል። ሀገራችን <u>ከፈረመቻቸው</u> ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች መካከል አንዱ የሕፃናትን ሞት መቀነስና ጤንነታቸውን መንከባከብ የሚል ይገኝበታል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ... በትኩረት እየተሠራ ነው።

በአካባቢያችሁ የጤና ተቋማት በመስፋፋት ላይ እንዳሉ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? የጤና ባለሙያዎች ቁጥር እያደገ መምጣቱንስ? ኧ... እንደሚታወቀው የጤና ባለሙያዎች እናቶችንና ሕፃናትን በመንከባከብ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ <u>ያላሰለሰ</u> ጥረት ያደርጋሉ።

የሕፃናትን ጤንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ... መብቶቻቸው ተከብረውላቸው እንዲያድጉ የሚያስችሉ <u>መብቶች</u> ተደንግገዋል። ከእነዚህ መብቶች መካከል ዋናዋናዎቹ ሕጻናት በሕይወት የመኖር፣ ጤንነታቸው የመጠበቅ፣ ከአካላዊ ጥቃት የመጠበቅ፣ ከጉልበት ብዝበዛ ነጻ የመሆን፣ ትምህርት የማግኘትና የወላጆችን ፍቅር የማግኘት መብት አላቸው የሚሉት ይጠቀሳሉ። ኧ... ግን የመብቶች መውጣት ብቻ ሕፃናትን ተጠቃሚ ሊያደርግ... አይችልም። እነዚህ መብቶች ለሕፃናት የሚያገለግሉት የእናንተ ድጋፍ ሲታከልበት ነው። አይመስላችሁም? እስኪ ልጠይቃችሁ እናንተ በአካባቢያችሁ ላሉ ሕጻናት ምን ምን እንክብካቤ እያደረጋችሁ ነው? ... ሕፃናትን በእንክብካቤ ለማሣደግ ከእኛ ምን ይጠበቃል ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ህፃናት ለተላላፊ በሽታዎችና ለሰውሠራሽ አደጋዎች እንዳይጋለጡ አካባቢያችንን ለሕፃናት ምቹ የማድረግና ከጥቃት የመከላከል ኃላፊነት አለብን።

ኧ ... ቀደም ብዬ እንደገለፅኩላችሁ ወላጆች ልጆቻቸውን በእንክብካቤ ለማሣደግ የጎላ ኃላፊነት አለባቸው። በተለይም በህጻንነታቸው ጊዜ ክትባት የማስከተብ፣ የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ፣ የወላጅ ፍቅር የማሣየት ኃላፊነት የወላጆች ነው። እነዚህ ካልተሟሉ ሕጻናት ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ። ዕድገታቸውም ይቀጭጫል፤ በሥነልቦናቸውም የተጎዱ ይሆናሉ።

እንዲሁም ወላጆች ልጆቻቸውን በሥነምግባር አንፀው የማሣደግ ኃላፊነት አለባቸው። ኧረ እስቲ... የታዘብኩትን ልንገራችሁ ኧ... በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው ነፃነት የሰጡ እየመሰላቸው ልቅ በመተው በነገ ህይወታቸው ላይ እንቅፋት ሲፈጥሩ ይታያል። ... ወላጆች ልጆችን ለማዝናናት ሲፈልጉ ገንዘብ

ብቻ ከመስጠት የሚዝናኑበትን ቦታና የመዝናኛ ዓይነቶችን ትኩረት ሰጥተው መምረጥ ... ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን በልጆቻቸው ሥነምግባር ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሣደሩ አይቀርም።

ኧ... ወላጆች ልጆቻቸውን ማዝናናት ሲፈልጉ የግድ ወደመዝናኛ ቦታ መውሰድ ብቻ አይጠበቅባቸውም። ኧ... ተረት እንዲያዳምጡ፣ ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲመለከቱ፣ ወጎችን እንዲሰሙ ቢያደርጉ ከማዝናናት በተጨማሪ የሀገራቸውን ታሪክና ባህል እንዲያውቁና እንዲወዱ ያደርጓቸዋል። በተጨማሪም የተለያዩ ጨዋታዎችን ከእኩያ ጓደኞቻቸው ጋር እንዲጫወቱ ኧ... ዕድል ቢሰጧቸው ይመረጣል። ኧ... ምክንያቱም ጨዋታዎች ከማዝናናት አልፈው <u>ለፈጠራና</u> ለምርምር ስለሚያነሳሱ ነው።

ህፃናት ከመዝናናት በተጨማሪ ሰላም በሰፈነበት ቤተሰብና አካባቢ ማደግ ይኖርባቸዋል። በቤታቸውም ሆነ በውጭ ጭቅጭቅ፣ ጠብና ግጭትን እያዩና እየሰሙ ማደግ የለባቸውም። ህፃናት ሰላም ካላገኙ በሥነልቦናቸው ይጎዳሉ። በወደፊት ህይወታቸው ላይም አሉታዊ <u>ተፅዕኖ</u> ሊያደርስባቸው ይችላል።

እንግዲህ ሃሳቤን ለማጠቃለል፣ ኧ... ልጆችን በእንክብካቤ ለማሣደግ ሁላችንም ኃላፊነት አለብን። በሉ በጥሞና ስላዳመጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ። በሌላ ጊዜ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ።

(ፍቅር ለይኩን። 2013። *የኢትዮጵያ ሪፖርተር ድረገጽ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ።

1. ወላጆች ለልጆቻቸው ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ የማይደገፈው የትኛው ነው?

   ሀ. ሕፃናትን በወቅቱ ማስከተብ  
   ሐ. የወላጅ ፍቅር መስጠት  
   ለ. መብቶቻቸውን ማክበር  
   መ. ህፃናትን ልቅ መተው

2. ሕጻናት በስነልቦና የሚጎዱበት ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ. እቤት ውስጥ ሠላም ማግኘት  
   ሐ. የወላጅ ፍቅር ማግኘት  
   ለ. ጭቅጭቅ ባለበት አካባቢ ማደግ  
   መ. ለሚጠየቁት ጥያቄ ተገቢ መልስ መስጠት

3. ሀገራችን ከፈረመቻቸው ዓለማቀፋዊ ስምምነቶች መካከል አንዱ የትኛው ነው?

   ሀ. ለሕፃናት የሀገራቸውን ታሪክ ማሣወቅ  
   ለ. ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲወዱ ማድረግ

ሐ. የሕፃናትን ሞት መቀነስ

መ. የሕፃናትን መዝናኛ ቦታ መገንባት

### ተግባር 2

በዓረፍተነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. ወላጆች ለልጆቻቸው ከሚያደርጉት እንክብካቤ አንዱ የወላጅ ፍቅር ማሣየት ነው።

ለ. ወላጆች ለሕፃናት በጨቅላነት ዕድሜያቸው ልዩ ልዩ እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ሐ. ወላጆች የሕፃናት ጤንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በጥሩ ሥነምግባር አንፀው የማሣደግ ኃላፊነት አለባቸው።

መ. ሕፃናትን ተረት እንዲያዳምጡ፣ ባህላዊ ጨዋታዎችን እንዲመለከቱና ወጎችን እንዲሰሙ ማድረግ ከማዝናናት በተጨማሪ የሀገራቸውን ታሪክ ባህል እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ምንባቡን መሠረት በማድረግ በ«ሀ» ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት በ«ለ» ሥር ካሉት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ያላሰለሰ | ሀ. መስማማት |
| 2. መጠበቅ | ለ. ጫና |
| 3. ፈጠራ | ሐ. አዕምሮን ማደስ |
| 4. መፈራረም | መ. ምርምር |
| 5. መብት | ሠ. ያልተቋረጠ |
| 6. ተጽዕኖ | ረ. መንከባከብ |
| 7. መዝናናት | ሰ. አዲስ ግኝት |
| | ሸ. በሕይወት መኖር |
| | ቀ. መጠጣት |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና ዝርዝር ሀሳቦች የተዋቀረ አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር 1

በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን ሁለት አንቀጾችን መጻፋችሁ ይታወቃል። አሁን ደግሞ እነዚህን አንቀጾች እንደገና አሻሽላችሁ ጻፏቸው።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

#### ተግባር

የሚከተሉትን ሥርዓተነጥቦች በጽሁፉ ውስጥ በተገቢው ቦታ አስቀምጡ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፣ | « » | ! | ። | ፤ |

የመድረኩ መሪ ለተወሰኑ ወራት በሕክምና ላይ ቆይቶ የነበረውና ዛሬ በመካከላችን በድንገት የተገኘው አንጋፋው ተወዳጁና ተናፋቂው ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ መድረክ ላይ ቀርቧል ሲል አዳራሹ በጭብጨባ በእልልታና በፉጨት አስተጋባ ተመልካች መጠራጠሩን አላቆመም ጥላሁን መድረክ ላይ ወጣ ማይክ ጨበጠ እዩዋት ስትናፍቀኝ... አለ በረጂሙ ትንፋሽ ይሄኔ ነው ጩኸትና ለቅሶ የተጀመረው።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሕፃናት እንክብካቤ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

አቀላጥፎ ማንበብ ሲባል ምንምን ነገሮችን የሚያካትት ይመስላችኋል?

## ማንበብ

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን የንባብ መከታተያ ቅጽ በመጠቀም አለ ለምትሉት ድክመት ወይም ጥንካሬ ይህን (✓) ምልክት በመሙላት «የሕፃናት እንክብካቤ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንቀጽ አንድና ሁለትን አንብቡ።

### የንባብ መከታተያ ቅፅ

| አድማጭ ተማሪ | አንባቢ ተማሪ | ቃላትን መሳሳት/ መድገም | የአነባበብ ሥርዓት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተማሪ አንድ | ተማሪ ሁለት | በቁጥር | በጣም ጥሩ | ጥሩ | ችግር ያለበት |
| ተማሪ ሁለት | ተማሪ አንድ | | | | |

## መናገር

### የተገነዘቡትን ሀሳብ መናገር

### ተግባር 1


በ3ኛው ሳምንት በ7ኛው ቀን «የሕፃናት እንክብካቤ» የሚል ፅሁፍ ማንበባችሁ ይታወቃል። አሁን ደግሞ በዚያ ጽሑፍ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### አያያዦችን መጠቀም

### ተግባር 1

አያያዦችን በመጠቀም አምስት አምስት ድርብ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።



# ምዕራፍ 3 ኤች.አይ.ቪ./ኤድስና ማህበራዊ ቀውስ

## ኤች አይ ቪ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-ኢትዮጵያ-ም | በኢትዮጵያም |
| ለ | ከ-ሚተላለፍ-ብ-ኣቸው | ከሚተላለፍባቸው |
| ሐ | ሊቋቋም-ኡ-ኣቸው | ሊቋቋሚቸው |
| መ | በ-ምታጠባ-ብ-ኧት-ም | በምታጠባበትም |
| ሠ | የሚታወቅ-ኧው-ን | የሚታወቀውን |
| ረ | እየ-አንዳንድ-ኣችን | እያንዳንዳችን |
| ሰ | የሚችል-ኡ-ኣቸው-ን | የሚችሏቸውን |

## ማንበብ

## ኤች አይ ቪ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስለ ኤች.አይ.ቪ. የምታውቁትን ተናገሩ።

ለ. «ኤች.አይ.ቪ.» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«ኤች.አይ.ቪ.» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የነገሮችን ምክንያትና ውጤት በመመርመር ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ኤች.አይ.ቪ.



ኤች አይ ቪ፣ ለኤድስ በሽታ የሚያጋልጥ ቫይረስ ነው። ቫይረሱ ለመጀመሪያ ጊዜ መኖሩ የታወቀው በአሜሪካ ነው። ጊዜውም እ.አ.አ. በ1981 ዓ.ም. ነው። በወቅቱ ባለመታወቁ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የችግሩ ሰለባ ሆነዋል። እ.አ.አ. በ2009 ዓ.ም. ተጽፎ በተገኘው መረጃ መሠረት በዓለማችን 34 ሚሊዮን ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ለማወቅ ተችሏል። በርካታ ሰዎችም ለሞት ተዳርገዋል፤ እየተዳረጉም ነው። በኢትዮጵያም የቫይረሱ መኖር ከታወቀበት እ.አ.አ. ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ዘር፣ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ ወዘተ. ልዩነት ሣያደርግ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች እያጠቃ ይገኛል።

የሰውነት የመከላከያ ኃይልን ማዳከሙ ቫይረሱን ከሌሎች ቫይረሶች ልዩ ያደርገዋል። ኤች.አይ.ቪ. ነጭ የደም ህዋስን በማጥቃት የሰውነትን የበሽታ መከላከል አቅም ያዳክማል። የሲዲ ፎር ህዋስ ተብሎ የሚታወቀውን ነጭ የደም ክፍል ቁጥር በመቀነስ፣ የቫይረሱ መጠን በደም ውስጥ እንዲሠራጭ ያደርጋል። ከዚያም ለተለያዩ በሽታዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ከኤድስ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ሰዎች ጤነኛ በነበሩበት ጊዜ ሊቋቋሟቸው የሚችሏቸውን በሽታዎች መቋቋም አይችሉም። በዚህ ምክንያት እስከሞት ሊደርሱ ይችላሉ።

ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ሰዎች የበሽታው ምልክት ሳይታይባቸው ለተወሰኑ ዓመታት ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት በዓለም ላይም ይሁን በሀገራችን በርካታ ሰዎች ለበሽታው ተጋላጭ ሆነዋል።

> **ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ሰዎች የበሽታው ምልክት ሳይታይባቸው የተወሰኑ ዓመታት ሊኖሩ ይችላሉ።**

ጥንቃቄ የጎደለው የግብረሥጋ ግንኙነት ቫይረሱ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች በቀዳሚነት ይጠቀሳል። የቫይረሱ ተጠቂዎች የተጠቀሙበትን መርፌ ሌሎች ሰዎች ሲጠቀሙበት ቫይረሱ ሊተላለፍ ይችላል። ኤች.አይ.ቪ. ካለባቸው እናቶች በእርግዝና ጊዜም ይሁን በወሊድ ጊዜ በቂ ሕክምና ካልተደረገ ከእናት ወደልጅ ሊተላለፍ ይችላል። እናት ጡት በምታጠባበትም ጊዜ ወደልጇ ሊተላለፍ ይችላል። ኤች.አይ.ቪ. ሊተላለፍባቸው የሚችልባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም አሉ። ከነዚህም መካከል ግርዛት፣ ዕንጥል ማስቆረጥ፣ ጥርስ መነቀስ የመሳሰሉት ድርጊቶች በተመሳሳይ መሣሪያዎች ሲከናወኑ ለቫይረሱ መዛመት ምክንያቶች ይሆናሉ።

በኤች.አይ.ቪ. ላለመያዝና ቫይረሱ ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ለመከላከል የ«መ» ህጎችን ማክበር አለብን። እነዚህም መታቀብ፣ መወሰን፣ መጠቀምና መመርመር ናቸው።

«መታቀብ» ከማንኛውም ዓይነት የግብረሥጋ ግንኙነት መቆጠብ ሲሆን፣ «መወሰን» ደግሞ ለፍቅረኛ ወይም ለትዳር ጓደኛ ታማኝ መሆንን ያመለክታል። «መጠቀም» በግብረሥጋ ግንኙነት ጊዜ ፍቅረኛሞች ኮንዶም መጠቀማቸውን ያሳያል። «መመርመር» ደግሞ ከግንኙነት በፊት ራስን ማወቅ የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

> **ራስን ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ለመጠበቅ የ«መ» ህጎችን ማክበር አስፈላጊ ነው።**

በመሆኑም አንደኛ እያንዳንዳችን በደማችን ቫይረሱ እንዳይኖር፣ ሁለተኛ ቫይረሱ ከተገኘብን ለሌሎች እንዳናስተላልፍ የ«መ» ህጎችን ማክበር ከሁላችንም የሚጠበቅ ነው። የሰማ ላልሰማ፣ ያወቀ ላላወቀ መልዕክቱን ማስተላለፍና የባህርይ ለውጥ ማምጣት የዘወትር ተግባር ሊሆን ይገባል።

(አበሻ ኬር ድረገጽ። 2009። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)


## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ከዚህ በታች በክቡ ውስጥ የሰፈሩትን ሀሳቦች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማዋቀር በደብተራችሁ ላይ ጻፏቸው።

ምሣሌ

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| የሰውነት የበሽታ መከላከል አቅም ሲዳከም | ለተለያዩ በሽታዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። |
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |




## ተግባር 2

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በኤች አይ ቪና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. ኤች.አይ.ቪ. ከሚተላለፍባቸው መንገዶች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ምክንያት ምንድን ነው?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

በ «ሀ» ክፍል ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት የሚስማማቸውን ከ «ለ» ክፍል በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. መቆጠብ | ሀ. ማከማቸት |
| 2. ነጭ የደም ህዋስ | ለ. አቅም ነሳ |
| 3. ጎጂ ልማድ | ሐ. ውሣኔ መስጠት |
| 4. መወሰን | መ. ሲዲ ፎር |
| 5. ሰለባ | ሠ. ራስን ማወቅ |
| 6. ጥንቃቄ የጎደለው | ረ. ጥርስ መነቀስ |
| 7. አዳከመ | ሰ. ተጠቂ |
| 8. መመርመር | ሸ. ልቅ |
| | ቀ. መታቀብ |
| | በ. ታማኝ መሆን |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

በምክንያትና ውጤት አወቃቀር ስልት አንቀጽ መጻፍ


> ማስታወሻ፡- የአንድ ነገር ውጤት ከሱ በፊት በሚኖሩ ምክንያቶች ወይም መንስኤዎች ሊመሠረት ይችላል። «ምን ተከሰተ?» ወይም «ምን ሆነ?» ብለን ስንጠይቅ ውጤት እናገኛለን። እንዲሁም «በምን ምክንያት?» ወይም «በምን ሰበብ?» ብለን ስንጠይቅ «መነሻውን» ወይም «ምክንያቱን» እናገኛለን።

## ተግባር

ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት ስለኤችአይቪ በቢጋር ሠንጠረዡ የቀረቡትን ሀሳቦች በምክንያትና ውጤት ስልት በማስፋፋት አንድ አንቀጽ ጻፉ።


ምሣሌ፡

ምክንያት ውጤት




የደን መጨፍጨፍና ከኢንዱስሪዎች የሚወጣ ጪስ ለአየር ንብረት መዛባት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ሰዎች ደንን በመጨፍጨፍ ለማገዶ፣ ለግንባታና ለተለያዩ ቁሳቁሶች መሥሪያ ስለሚጠቀሙ የአየር ንብረት መዛባት ይከሰታል። በከተሞች አካባቢም ከተለያዩ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች የሚለቀቀው ጪስ ለአየር ንብረት መዛባት ምክንያት ይሆናል።

ምክንያት ውጤት



### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የፊደላት ግድፈት (ስህተት) ያለባቸውን ቃላት በማረም አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ሕመምተኛው ሽማግሌ እየተንቆጠቆጠ ወደሃኪም ቤት ሄዱ።

ሕመምተኛው ሽማግሌ እየተንቀጠቀጡ ወደሃኪም ቤት ሄዱ።

ሀ. ንጉሥ ሆይ! «አልቀጣሽም ብለህ ማለልኝና እነግርሃለሁ»አለችው።

ለ. መጻሕፍት መንደርደሪያ ላይ ከመደርደራቸው በፊት የካርድ ቁጥር ይሰጣቸዋል።

ሐ. ቃላት ላይ ቅጥያዎች በመቀጠል ሌሎች ቃላትን ስንመሠርት ድምጾች በሚያደርሱት ቅንጅት የሆሂያቱ ቅርፅ ለወጥ ይችላል።

መ. ያነጋገረው ባለሙያ ወጣት ስለሆነ ለመግባባት ጊዜ አልወሰደባትም።

ሠ. ታታሪ ስለሆኑ ገበሬዎች ውጤትማነት ሲሰማ ተደሰተ።

ረ. ማንኛውም የተማረ ሰው ከልዩ ልዩ ምሎች መረጃን አንብቦ መረዳት ይጠብቅበታል።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ኤች አይ ቪ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«ኤች.አይ.ቪ.» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሱትን ሀሳብ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «ኤች.አይ.ቪ.» በሚል የቀረበውን ምንባብ አንብቡ።

## ማዳመጥ

# ሴቶችና ኤች.አይ.ቪ.

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ኤች.አይ.ቪ. ከሴቶችና ከወንዶች በይበልጥ ማንን የሚያጠቃ ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

«ሴቶችና ኤች.አይ.ቪ.» በሚል ርዕስ የሚቀርብላችሁን ምንባብ በማዳመጥ ምክንያቱንና ውጤቱን በሠንጠረዡ መሠረት በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

### አዳምጦ መረዳት

**ተግባር**

በደብተራችሁ ላይ የጻፋችሁትን ምክንያትና ውጤት በመጠቀም የተገነዘባችሁትን ሀሳብ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ጠቋሚ መስተኣምር

ማስታወሻ፡- ጠቋሚ መስተኣምራን የሚባሉት፣ ይህ፣ ያ፣ ይቺ፣ ያቺ፣ እነዚህ፣ እነዚያና የመሳሰሉት ናቸው። በዓረፍተነገር ውስጥ ከስም በፊት ሲገቡ ከተናጋሪው ጋር ካላቸው ርቀት አንጻር የመጠቆም አገልግሎት የሚሰጡ ቃላት ናቸው።

## ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ያሉትን ጠቋሚ መስተኣምራን ለይታችሁ ጻፉ።

ምሣሌ፦ እነዚያ ልጆች የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የደም ምርመራ አደረጉ። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ «እነዚያ» የሚለው ጠቋሚ መስተኣምር ነው።

ሀ. ያቺ ልጅ በህጻንነቷ፣ ለስድስት ወራት ያህል ጡት ብቻ ስለጠባች ጤነኛ ናት።

ለ. እነዚያ ሰዎች፣ ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በቂ ግንዛቤ አላቸው።

ሐ. ይህ ልጅ ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች እያስተማረ ነው።

መ. እነዚህ ተማሪዎች፣ የፀረኤድስ ክበብን እያጠናከሩ ይገኛሉ።

## ማንበብ

### ወይ አለማወቅ!

#### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ለተለያዩ ሱሶች ተገዢ መሆን ምን ምን ጉዳቶችን ያመጣሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? መልሶቻችሁን በቃላችሁ አቅርቡ።

#### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«ወይ አለማወቅ?!» የሚለውን ምንባብ ምክንያትና ውጤት ለመለየት ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ።

### ወይ አለማወቅ!

የተወለድኩት አዲስ አበባ ከተማ ነው። ረዳት አልነበረኝም። በዚህም ምክንያት የገበያ እንቅስቃሴ በሚደረግበት በአንድ ሱቅ ውስጥ በሻጭነት ተቀጠርኩ። ግማሽ ቀን እየሠራሁ ግማሽ ቀን ደግሞ ትምህርቴን እማር ነበር። በምሠራው ሥራ የተሻለ ገንዘብ በማግኘቴ ገንዘብን ይበልጥ እየተላመድኩ ሄድኩና ሰባተኛ ክፍል እንደደረስኩ ትምህርቴን አቋረጥኩት። ቀስ በቀስ ሥራው በፈጠረልኝ አጋጣሚ ከተለያዩ የንግድ ሰዎች ጋር ተዋወቅሁ። ተፈላጊ ዕቃዎችንም መለየት ቻልኩ። በዚህም አዳዲስ ዕቃዎችን እየተረከብኩ ለሌሎች ባለሱቆች መሸጥ ጀመርኩ። በዚህም ጠቀም ያለ ትርፍ ወደማግኘቱ ስሸጋገር የሻጭነት ሥራዬን ተውኩና በድለላ ሥራ ላይ ተሰማራሁ።

በሱቅ ውስጥ በምሠራበት ጊዜ ምንም ዓይነት ትርፍ ጊዜ አልነበረኝም። በአዲሱ ሥራዬ ግን፣ ትርፍ ጊዜ በማግኘቴ የሱስ ተገዥ መሆን ጀመርኩ። ጫት ቃሚ ጓደኞች ስላፈራሁ፣ ሁልጊዜ ከምሳ ሰዓት በኋላ የምውለው በጫት መቃሚያ ቤት ሆነ። ከጫት በኋላ ደግሞ ወደመጠጥ ቤት እሄዳለሁ። ከአንድ ቤት መጠጣት እጀምርና በሞቅታ የተለያዩ መጠጥቤቶችን በማዳረስ ስጠጣ አመሻለሁ። በስካር መንፈስ ብዙ ሴተኛ አዳሪዎች እየጋበዝኩና ከእነሱ ጋር እየተዳራሁ አመሽና ከአንዷ ደንበኛዬ ጋር አድራለሁ።

በዚህ ምክንያት በርካታ የቡናቤት ሴቶች ያውቁኝ ነበር። ሁኔታዬ ያላማራቸው ብዙ ሰዎች የባህርይ ለውጥ እንዳመጣ ይመክሩኝ ጀመር። በዚህም የመጠጡን ነገር በመጠኑም ቢሆን ልቆጣጠረው ሞከርኩ። ከዚህ በፊት ከነበሩኝ የቡና ቤት ሴት ደንበኞቼ ጋር የነበረኝን ግንኙነት ግን ማቆም አልቻልኩም። በዚህ ሁኔታ ረዥም ጊዜ አሳለፍኩ። በሂደትም ብርድብርድ የሚልና እንደሳል ያሉ የህመም ስሜቶች ይሰሙኝ ጀመር።

ስሜቶቹ ሲደጋገሙብኝ በአካባቢዬ በሚገኘው አንድ ጤና ጣቢያ ሔጄ ተመረመርኩና የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳለብኝ ተነገረኝ። ሕክምናውን መከታተል ጀመርኩ። ጤንነቴ ለውጥ አሳየ። ነገርግን እንደበፊቱ ተሯሩጬ መሥራት አልቻልኩም። ከሳንባዬ ሕመም ባገግምም የሌሎች በሽታዎች ስሜቶች ይታዩብኝ ጀመር። ሰውነቴ አለቀ። ይህንን ያስተዋሉ የቅርብ ጓደኞቼ ምናልባት ኤች.አይ.ቪ. ሊሆን ይችላል በሚል የደም ምርመራ እንዳደርግ መከሩኝ። እኔም ምክራቸውን ተቀብዬ ወደህኪም ቤት ሄጄ ተመረመርኩ። ከምርመራው በኋላ በደሜ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. መኖሩ ተነገረኝ። ውጤቱን ስሰማ ያለሁበትን አላውቅም ነበር። ዶክተሩ፣ መከረውና አረጋግተው እንደማንኛውም ሰው መኖር እንደምችል ከነገሩኝ በኋላ ቀጠሮ ሰጥተው ሸኙኝ።

በልጅነት ዕድሜዬ ኑሮዬን ለመምራት ሠርቼ ገንዘብ ማግኘት ብችልም ገንዘቤን በአግባቡ መጠቀም አልቻልኩም። በዚህ ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተጋላጭና ሕመምተኛ ሆንኩ። አሁን የሀኪሜን ምክር እየተከታተልኩና ለኤድስ ህሙማን የሚሰጠውን መድሀኒት እየወሰድኩ ነው። ባለማወቄ በሽታውን ለበርካታ ሴቶች ማስተላለፌ ስለሚፀፅተኝ የእኔ ዕጣ ፈንታ በሌሎች እንዳይደርስ እየመከርኩ እገኛለሁ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ባለታሪኩ ትምህርቱን ዳር ሳያደርስ የቀረበት ምክንያት ምንድን ነው?

ለ. ባለታሪኩን ለኤች.አይ.ቪ. ኤድስ እንዲጋለጥ ያደረጉትን ምክንያቶች ዘርዝሩ?

ሐ. በልጅነት ዕድሜ ገንዘብ ከተገኘ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይገባል?

መ. ባለታሪኩ የተለያዩ የሕመም ስሜቶች ሲሰሙትና የሰውነት ክብደቱ ሲቀንስ ምን አደረገ?

ሠ. በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ የተያዙ ሰዎች በሽታውን ወደ ጤነኞች እንዳያስተላልፉ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ረ. ከባለታሪኩ ምን ተማራችሁ? ባለታሪኩን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ጠቃሚ
ለ. ትርፍ
ሐ. ምክር
መ. ግማሽ
ሠ. አገገመ
ረ. ሻጭ
ሰ. ማቋረጥ
ሸ. መረጋጋት
ቀ. ጓደኛ
በ. ተቀጠረ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን የሠንጠረዥ መረጃዎች መሠረት በማድረግ በምክንያትና ውጤት ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

ምክንያት

በሥራ አለመጠመድ

ውጤት

ጊዜን በከንቱ ማሳለፍ።

ጠቃሚ ካልሆኑ ሰዎች ጋር መጎዳኘት።

ለተለያዩ ሱሶች ተገዥ መሆን።

ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን ማከናወን።

ማስታወሻ፦ አሕፅሮተ ቃል አንድ የተለመደ ቃል ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት የሚጠራን ስያሜ በተወሰኑ ፊደላት ውክልና አሳጥሮ መጻፍ ማለት ነው። ከአንድ ነጥብ (ይዘት) አገልግሎቶች ውስጥ በአብዛኛው የተለመደውም ይኸው አሕፅሮተ ቃልን ወይም ቃላትን ለመመሥረት ተግባር መዋል ነው። በተለይ ከሁለት በላይ በሆኑ ቃላት ህብረት የተመሰረቱ ስሞችን ወይም መጠሪያዎችን የየቃላቱን የመጀመሪያ ፊደላት ብቻ በመጻፍ አሳጥሮ ለመግለጽ ያገለግላል።

ምሣሌ፦ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አሳጥሮ ሲጻፍ ኢ.ዜ.አ. ይሆናል።

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸውን ስሞች ወይም መጠሪያዎች በአሕፅሮተቃላት ጻፉ።

ሀ. <u>የትግራይ ልማት ማህበር</u> በገጠር ቀበሌዎች ብዙ ትምህርትቤቶችን ገነባ።

ለ. የባህር ዳር <u>ከተማ ነዋሪዎች ማህበር</u> የእግር ኳስ ቡድን ዛሬ ውድድር አለው።

ሐ. <u>የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት</u> ተጨማሪ ቤቶች ሠራ።

መ. የትምህርት ቤታችን <u>ወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት</u> ዛሬ ተሰበሰቡ።

ሠ. <u>የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት</u> መቼ ተመሰረተ?

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ወይ አለማወቅ!

### ቅድመንባብ

### ተግባር

«ወይ አለማወቅ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ አንቀጽ አንድን መምህራችሁ በተለያዩ መንገዶች ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል። እናንተ ደግሞ አዳምጣችሁ ከፍጥነትና ከአገላለጽ አንጻር የተሻለውን አነባበብ ምረጡ።

## ማንበብ

### ተግባር

«ወይ አለማወቅ» የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንቀጽ አንድና ሁለትን ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

### ውይይት

ማስታወሻ

የውይይት አቀራረብ መመሪያ

- ርዕሱን መገንዘብና መረጃ መሰብሰብ፣
- የውይይቱን ርዕስና ዓላማ ለአድማጭ ማስተዋወቅ፣
- በማዳመጥ ዋናውን ሀሳብ በግልፅና በቅደምተከተል ማቅረብ፣
- ጎላ ባለ ድምፅና ሥርዓት ባለው መንገድ መናገር፣
- ሀሳባችን ተቀባይነትን እንዲያገኝ በቂ ምክንያት ማቅረብ፣
- በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሀሳብን ማጠናቀቅ።

### ተግባር

ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ ተወያዩ።

ሀ. ወጣቶችን ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተጋላጭ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. ወጣቶች ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ራሳቸውን ለመከላከል ምን ማድረግ አለባቸው?

## ሰዋስው

### ጠቋሚ መስተአምርና የመሆን ግስ

ማስታወሻ

የመሆን ግሶች የሚባሉት ስምን በመሙያነት ሊወስዱ የሚችሉ ናቸው። ጠቋሚ መስተአምሮች ደግሞ በመሙያነት ከሚገባው ስም ቀድመው በመምጣት የመጠቆም ተግባርን ያከናውናሉ።

ምሣሌ፦ «እነዚያ ዋልያዎች ናቸው» በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ «ናቸው» የሚለው የመሆን ግስ ሲሆን፣ «ዋልያዎች» የሚለው ስም ደግሞ ለመሆን ግሱ መሙያ ነው። እነዚያ የሚለው መስተኣምር ስሙን ይጠቁማል።

## ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች የጠቋሚ መስተኣምሩንና የመሆን ግሱን ቦታ በመጠበቅ አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. እነዚያ ናቸው በጎች።

ለ. ግመል ነው ይህ።

ሐ. ተራራ ያ ነው።

መ. ተያቢ ናት ይቺ።

ሠ. ሀውልቶች ናቸው እነዚያ።

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በህብረተሰብ ጤናና ምጣኔሀብታዊ ላይ ያለው ተፅዕኖ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ህፃን-ኣት-ና | ህፃናትና |
| ለ | ለ-እንግል-ት-ና | ለእንግልትና |
| ሐ | ውጤት-ኣማ-ነት-ም | ውጤታማነትም |
| መ | አድርግ-ኡ-ኣቸው-ኣል | አድርጓቸዋል |
| ሠ | ያደረሰ-ብ-ኣቸው | ያደረሰባቸው |
| ረ | የ-ሚ-ደግፍ-ኡ-ት-ም | የሚደገፉትም |
| ሰ | ወንድም-ኦች-ኣቸው-ን-ና | ወንድሞቻቸውንና |

## ማንበብ


### የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተፅዕኖ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተለውን ቢጋር አሟሉ።




## የማንበብ ሂደት

«የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተፅዕኖ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምጻችሁን ሳታሰሙ የምክንያትና የውጤትን ትሥሥር እየለያችሁ አንብቡ።

## የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተፅዕኖ

የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ምጣኔሀብታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል። በማህበረሰቡ ጤናና ምጣኔሀብታዊ ላይ የሚያሳድረውም ተፅዕኖ ቀላል አይደለም። በተለይም በወጣቶችና በጎልማሶች ላይ ያለው ሥርጭት የጎላ ነው። የተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በበሽታው እየተጠቁ በሚመጡበት ወቅት በሀገር ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ያጋጥማል። በዚህም በሀገር ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል።

**የኤድስ መስፋፋት የምጣኔሀብታዊና የጤና ችግር ከማስከተሉ በተጨማሪ የሀገርን የህዝብ ስብጥር ያዛባል።**

የኤድስ መስፋፋት የምጣኔሀብታዊና የጤና ችግር ከማስከተሉ በተጨማሪ የሀገርን የሕዝብ ስብጥር ያዛባል። በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ኤድስ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ከ15-49 የዕድሜ ክልል ያሉት ናቸው። በዚህ የዕድሜ ክልል የሚገኙት ደግሞ አምራች

ዜጎች ናቸው። ማምረት የማይችሉት ሕጻናትና አረጋውያን የሚደገፉትም በነዚህ አምራች ክፍሎች ነው። ወጣቶችና ጎልማሶች በቫይረሱ እየተጠቁ ከሄዱ ደግሞ ሕጻናትና አረጋውያን ያለደጋፊና ጧሪ ይቀራሉ። በዚህም በሀገርም ሆነ በሕዝብ ምጣኔሀብት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ይስከትላል።

በተጨማሪም የቫይረሱ ሥርጭት መስፋፋት ሆስፒታሎች በኤድስ ህሙማን እንዲጨናነቁ በማድረግ የጤና አገልግሎት ችግር ፈጥሯል። በዚህ ምክንያት በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በሚመለከት ለሚያዙ መርሀግብሮች እንደሚወጣ መረጃዎች ያሣያሉ። ይህ ገንዘብ ለሌሎች የልማት ሥራዎች ቢውል በሕዝብ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ ይችል ነበር።

ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ዜጎችን ለእንግልትና ለስቃይ ዳርጓል። በሺ የሚቆጠሩ ሕጻናት ያለወላጅ ቀርተዋል። ይህም ለመንግሥትና ለማህበረሰቡ አስቸጋሪ ፈተና ሆኗል። ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ወጣት ሴቶች ራሳቸውን፣ ታናናሽ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ለጎዳና ሕይወትና ሴተኛአዳሪነት ተዳርገዋል። ወንዶችም የጎዳና ተዳዳሪ ሆነዋል። በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሰዎችም በተለያዩ በሽታዎች ስለሚጠቁና ቶሎም ስለማይድኑ ከሥራ ይቀራሉ። በሥራ ላይ ያላቸው ውጤታማነት ከዕለት ወደ ዕለት  እየቀነሰ ይሄዳል። ይህ ደግሞ በግለሰብ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ምጣኔሀብታዊያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ያስከትላል።

ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ያለባቸው ሰዎች ከጤናቸው መታወክ በተጨማሪ የሚደርስባቸው የሥነልቦና ጫና ቀላል አይደለም። ዛሬም ቢሆን በበሽታው የተያዙ ሰዎችን የማግለሉ ችግር ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ በመሆኑ ህሙማን ቫይረሱ በደማቸው መኖሩ ከተረጋገጠ ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንደወትሮው ላይቀጥል ይችላል። በዚህም ምክንያት የኤድስ ህሙማን የሥነልቦና ችግር ያጋጥማቸዋል። በተለይም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በሌላ በሽታ ለተያዙ ሰዎች የሚያደርጉት ድጋፍና ክትትል ዓይነት ለኤድስ ህሙማንም ስለማያደርጉ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ህሙማንን ችግር እጥፍ ድርብ ነው። ይህ በራሱ በሽታውን ሊያባብሰው ይችላል።

በአጠቃላይ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በሀገር፣ በማህበረሰብና በግለሰብ ዘንድ ከፍተኛ ምጣኔሀብታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ያስከትላል። ስለዚህ በበሽታው ከመያዝ በፊት ራስን መጠበቅ፣ ከተያዙ በኋላም ወደሌሎች እንዳይተላለፍ የድርሻን መወጣት ያስፈልጋል።

**ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ራሳችንን በመጠበቅ ኃላፊነታችንን እንወጣ።**

(ሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ.። 1995። *የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ትምህርት።* ገጽ 29-31 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ምክንያቶቹ የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች በትክክል አስፍሩ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. የወጣቶችና የጎለማሶች በቫይረሱ መጠቃት | → | • |
| ለ. የኤች.አይ.ቪ. መስፋፋት | → | • |
| ሐ.ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሰዎች ላይ መኖር | → | • |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን በሚመለከት ለሚያዙ መርሀግብሮች እንደሚወጣ መረጃዎች ያሳያሉ» በሚለው ዓረፍተነገር የተላለፈው ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

ለ. በአንዲት ሀገር ትክክለኛ የሆነ የሕዝብ ስብጥር አለ ለማለት የሚቻለው ምን ሲሆን ነው?

ሐ. ሰዎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳይያዙ ምን ትመክራላችሁ?

መ. ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የሚኖሩ ሰዎች በሌሎች ሰዎች መገለል እንዳይደርስባቸው ለማድረግ መፍትሄው ምን ይመስላችኋል?

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መጠበቅ ለ. ሰለጠነ ሐ. ጎዳና መ. መታወክ

### ተግባር 2

ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ቀውስ ለ. ማባዛት ሐ. እንግልት መ. መስፋፋት

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት አንቀጽ መጻፍ

### ተግባር

በ1ኛ ሳምንት፣ 2ኛ ቀንና በ2ኛ ሳምንት 5ኛ ቀን ሁለት አንቀጾችን ፅፋችኋል። እነዚህን አንቀጾች በምክንያትና ውጤት ስልት በተገቢው አደራጅታችሁ ጻፏቸው።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር 1

ቀጥሎ በተሰጡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የፊደላት ግድፈት የሚታይባቸውን ቃላትና ሐረጋት አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. በደሮው ጊዜ የነበረውን የአገራችንን የትምህርት ሥርዓት አብርታችሁ ግለጹ።

ለ. አገራችን ምጣኔሀብታዊዋን ለማሣደግ የሚያስችሉ የተለዩ የማዕድን አይኖች አሏት።

ሐ. ተማሪ በምን ዓይነት ሁኔታ ሊሳተፍ እንዲችል ተናገሩ።

መ. ውኃን በግብ አጠራቅሞ ማቆየት፣ ማጣራትና ማራጨት ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል።

### ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የተሠመረባቸውን ሐረጋት በአጽሕሮተ ቃል ጻፉ።

ሀ. <u>የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር</u> መቼ ተመሰረተ?

ለ. <u>የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር</u> ዓመታዊ ስብሰባ አካሄደ።

ሐ. <u>የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር</u> ዓመታዊ በአሉን አከበረ።

መ. <u>የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር</u> ትምህርት ቢሮ በየ6 ወሩ መጽሔት ያሳትማል።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተፅዕኖ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

ምንባብን በጥሩ አገላለጽ ማንበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቃል ግለጹ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተፅዕኖ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ ከመጀመሪያው አንቀጽ በመጀመር መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንብቡ።

# መናገር

### ክርክር

ማስታወሻ

በክርክር ጊዜ ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች

- በሚቀርቡ መከራከሪያዎች ላይ በመረጃ የተደገፈ ዝግጅት ማድረግ
- የሌላውን ተከራካሪ ሀሳብ አለማንቋሸሽ
- ለተከራካሪ ሀሳብ ምክንያታዊ መልስ መስጠት
- ተራን ጠብቆ መናገር

**ተግባር**

በሚከተለው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተዘጋጅታችሁ ክርክር አቅርቡ።

የኤች.አይ.ቪ.. ምርመራ ማድረግ መብት ነው ወይስ ግዴታ?

## ሰዋስው

### ጠቋሚ መስተኣምር ከመሙያ ጋር

### ተግባር

ጠቋሚ መስተኣምርንና ስምን እንደመሙያ የያዙ ስድስት ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።



# ታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች

## ምዕራፍ 4

## የታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች የሕይወት ታሪክ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ሲ-ዊ-ድ-ን | ስዊድን |
| ለ | አዘ-ጋጅ-ነት | አዘጋጅነት |
| ሐ | ፕሮፓ-ጋን-ዳ | ፕሮፓጋንዳ |
| መ | ተወዳጅ-ነት | ተወዳጅነት |
| ሠ | ሚ-ስ-ዮ-ን | ሚስዮን |

## ማንበብ

### የመጀመሪያዋ ጋዜጠኛና ደራሲ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሕይወት ታሪክ ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በጣም ታዋቂ የሚባሉትን ሴት የኪነ-ጥበብ ሰዎች ስም ጥቀሱ?

### የማንበብ ሂደት

«ሮማነወርቅ ካሳሁን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የታሪኩን ቅደም ተከተል በመገንዘብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የመጀመሪያዋ ጋዜጠኛና ደራሲ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን



### የልጅነት ጊዜ

ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን ከአባታቸው ከአቶ ካሳሁን እንግዳሸትና ከእናታቸው ከወ/ሮ አለሙሽ አንቺአለም በ1914 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። ዳዴ ብለው ወፌ ቆመች ተብለው በእናትና በአባታቸው እቅፍ አደጉ። ወ/ሮ ሮማነወርቅ ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ አዲስ አበባ ከተማ ከሚገኘው ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብተው ማንበብና መፃፍ ተማሩ። ከዚያም ከሲዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በመግባት በጊዜው የነበረውን ዘመናዊ ትምህርት ተማሩ። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲማሩ በተደጋጋሚ የአንደኝነት ደረጃ በማግኘት የምስክር ወረቀት ይሸለሙ ነበር። ወ/ሮ ሮማነወርቅ ገና የ16 ዓመት ልጃገረድ ሆነው ለትዳር ታጩ። በለጋው ዕድሜያቸው ወደትዳር አለም ተቀላቀሉና በጠዋቱ የአንዲት ሴት ልጅ እናት ለመሆን በቁ።

## የጋዜጠኝነት ህይወት

በሲዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት ከአውሮፓውያን መምህራን ያገኙት ዘመናዊ ትምህርት ከተፈጥሮ ችሎታቸው ጋር ተዳምሮ በጥናትና በንባብ ያዳበሩትን እውቀታቸውን ወደ አደባባይ ለማውጣት ስለፈለጉ በጥር 20 ቀን 1939 ዓ.ም በማስታወቂያ ሚኒስቴር (ያን ጊዜ ማስታወቂያና ፕሮፓጋንዳ መስሪያ ቤት) ተብሎ ይጠራ በነበረው ድርጅት የመጀመሪያዋ ሴት ጋዜጠኛ በመሆን ተቀጠሩ።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በተሰጣቸው በሬድዮ ጋዜጠኝነት ስራቸው የተለያዩ ፅሑፎችንና ዜናዎችን በማዘጋጀት በማራኪ አንደበታቸው ሲያንቆረቁሩት በዜና አቀራረባቸውና በፕሮግራም ዝግጅታቸው ከህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነትንና አድናቆትን ለማግኘት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም ነበር።

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ባገለገሉባቸው ጊዜያት በሬድዮ ዜና አጠናቃሪነት፣ በዜና አንባቢነት ፣ በሴቶች ፕሮግራም አዘጋጅነት ያገለግሉ ነበር። በዚህም መስሪያ ቤት ውስጥ ከአንደበታቸው ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ በየጊዜውና በየቀኑ ለአድማጭ አዲስ ነገር ይዞ በመቅረብ ለ25 አመታት ያህል ለሙያቸው በመታመን ያገለገሉት ወይዘሮ ሮማነወርቅ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ጋዜጠኞች አርአያ ሆነዋል። በወቅቱም በዝግጅቶቻቸው ላይ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ስራዎች በንባብና ጥናት በማካሄድ ጎንለጎን የአንዳንድ ወንዶችን የበላይነት ስሜት ተቋቁመው በነበራቸው ንቃተህሊና መጠን ለህዝቡ አገልግሎት ሲሰጡና ገና በትምህርት ገበታ ላይ ለነበሩት ሴቶች ልጆች እንደብርቅዬና የበጎ አርአያ ተምሳሌ በመሆን ይታዩ ነበር። ከአድማጩም ለሚደርሳቸው ማበረታታትና አድናቆትም በመታገዝ በስራቸው ላይ ከፍተኛ ትኩረት አደረጉ። በዝግጅቶቻቸው የተለያዩ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በወቅቱ ለሴቶች ይሰጥ የነበረውን የዝቅተኝነት ደረጃ ለመፋቅ በሚዲያ የራሳቸውንና የብዙ ሴቶችን ድምፅ አሰምተዋል። ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን የመጀመሪያ የሴት ጋዜጠኛም ብቻ አልነበሩም። ለሀገራቸው ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሰልፈው በመስራት ምሳሌና አርአያ የመሆን ቅድሚያ ነበራቸው።

## የስነፅሑፍ ህይወት

ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን የተለያዩ ፁሑፎችን በመፃፍ ለህዝቡ አቅርበዋል። ካቀረቧቸው ስራዎች የመጀመሪያው ለአንባቢያን ያበረከቱት «ትዳር በዘዴ» የሚል ነበር። የመጀመሪያ ስራቸው የባላገር ትዳርና የከተማ ኑሮ በማነጻጸር ያተኮረ ነበር። መፃሃፉ ለህትመት የበቃው 1942 ዓ.ም ነው። ከዚህ በመቀጠል ሁለተኛው ስራችን በ1943 ዓ.ም «ማህቶተ ጥበብ» የሚል ስራቸውን በትያትር መልክ አቅርበዋል። ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ፅሑፎችን በተለያዩ ጋዜጦችና መፅሄቶች

ላይ በማሳተም በህትመት ሚዲያ የፋናወጊነት ሚና ተጫውተዋል። ለመነን መፅሔት በአዘጋጅነት ሰርተዋል።

ለሕትመት ካበቁት ባሻገር ወ/ሮ ሮማነወርቅ ያልታተሙ ፅሑፎችን በመፃህፍ መልክ ለማዘጋጀት ችለዋል። ለአብነት ያህል «ሂዋን፣ መልካም እመቤት፣ ጋብቻና ወጣት ወዘተ» የሚሉ መፃህፍትን ቢፅፉም በተለያዩ ምክንያቶች ለህትመት ሳይበቁ ቀርተዋል። በአጠቃላይ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን ታዋቂ ጋዜጠኛ፣ ደራሲ፣ የሴቶች መብት ተሟጋች ታታሪና ትጉህ የጥበብ ሰው በመሆን ሀገራቸውን ሲያገለግሉ ቆይተው ጥር 25 ቀን 1964 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።


> **ሮማነወርቅ ካሳሁን የመጀመሪያ ሴት ጋዜጠኛ ብቻ ሳይሆኑ ደራሲም ናቸው።**

(ፍፁም ወልደማርያም። 2006። ያልተዘመረላቸው ከገፅ 141-147 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ ዋና ዋና ሀሳቦችን አስፍሩ።



## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

በሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተመሳሳይ ፍቺዎችን ጻፉ።

> በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ባገለገሉባቸው ጊዜያት በሬድዮ ዜና አጠናቃሪነት በዜና አንባቢነት ፣በሴቶች ፕሮግራም አዘጋጅነት ያገለግሉ ነበር። በዚህም መስሪያ ቤት ውስጥ ከአንደበታቸው ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ በየጊዜውና በየቀኑ ለአድማጭ አዲስ ነገር ይዞ በመቅረብ ለ25 ዓመት ያህል ለሙያቸው በመታመን ያገለገሉት ወይዘሮ ሮማነወርቅ ለሴቶች ብቻ ሣይሆን ለአጠቃላይ ጋዜጠኞች አርአያ ሆነዋል። በወቅቱም በዝግጅቶቻቸው ላይ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዩችን የሚዳስሱ ስራዎችን በንባብና ጥናት በማካሄድ ጎንለጎን የአንዳንድ ወንዶችን የበላይነት ስሜት ተቋቁመው በነበራቸው ንቃተህሊና መጠን ለሕዝቡ አገልግሎት ሲሰጡና ገና በትምህርት ገበታ ላይ ለነበሩት ሴቶች ልጆች እንደብርቅዬና የበጎ አርአያ ምሳሌ በመሆን ይተዩ ነበር። ከአድማጩም በሚደርሳቸው ማበረታታትና አድናቆትም በመታገዝ በስራቸው ላይ ከፍተኛ ትኩርት አደረጉ። በዝግጅቶቻቸው የተለያዩ ወቅታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት በወቅቱ ለሴቶች ይሰጥ የነበረውን የዝቅተኝነት ደረጃ ለመፋቅ በሚዲያ የራሳቸውንና የብዙ ሴቶችን ድምፅ አሰምተዋል። ወይዘሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን የመጀመሪያ የሴት ጋዜጠኛም ብቻ አልነበሩም። ለሀገራቸው ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሰልፎ በመስራት ምሣሌና አርአያ ቅድሚያ ነበራቸው።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የሕይወት ታሪክ መጻፍ

ማስታወሻ

- የግለሰብ የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ መመሪያ
- ታሪኩ ስለሚጻፍለት(ላት) ግለሰብ የተጻፉ ጽሑፎች ካሉ ማሰባሰብ፣

- ግለሰቡን(ቧን) የሚያውቁ ሰዎች ካሉ በመጠየቅ፣ የግለሰቡን/ቧን ትክክለኛ ታሪክ ወይም ማስረጃ ማሰባሰብ፣
- ማስረጃውን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣
- ግለሰቡ(ቧ) የተወለደበትን(ችበትን) ቦታ፣ ዘመን፣ እንዲሁም በሕይወት የሌለ(የሌለች) ከሆነ(ነች) የሞተበትን(ችበትን) ዘመን መግለጽ፣
- ስለአስተዳደግ፣ ስለትምህርት ደረጃ ስላበረከታቸው(ቻቸው) አስተዋጽኦዎች ማተት፣ ዋናዋናዎቹ ናቸው።

### ተግባር

በ1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን በአንብቦ መረዳት ሥር የቀረበውን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም ሁለት አንቀጾችን ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚታዩትን ግድፈቶችና የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ።

በዚህ ዘመን ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምንነት ከሚነሱ ጥያቄዎች ባሻገር ድህነት ለሽታው ስለሚያደርገው አስተጽኦ ማለትም «የበሽታው ማህበራዊና ምጣኔህብታዊያዊ ደረጃ ምን ነው ። የህብታሞች፡ የድሆች ወይስ የሁሉም በሽታ ነው?» የሚል ጥያቄም እየተነሳ ነው።

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የመጀመሪያዋ ጋዜጠኛና ደራሲ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን

## ቅድመንባብ

### ተግባር

ስለወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን ጋዜጠኛነትና ደራሲነት ሕይወት የምታስታውሱትን ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

«የመጀመሪያዋ ጋዜጠኛና ደራሲ ወ/ሮ ሮማነወርቅ ካሳሁን» የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### የሙዚቃ ጠቢቡ…

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

ሀ. የምታውቋቸውን የሙዚቃ ጠቢቦች ስም ዘርዝሩ።

ለ. በፎቶግራፉ የምታዩአቸው ሰው ማን ናቸው?



### የማዳመጥ ሂደት

«የሙዚቃ ጠቢቡ …» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እናንተ ደግሞ በሚከተለው የሕይወት ታሪክ መጻፊያ ሠንጠረዥ ማስታወሻ በመያዝ አዳምጡ።

| የሕይወት ታሪክ መጻፊያ ሠንጠረዥ | |
|---|---|
| የባለታሪኩ ስም | |
| የትውልድ ዘመን | |
| የትውልድ ቦታ | |
| የትምህርት ሁኔታ | |
| ባለታሪኩ በሙዚቃ ሥራው ያገኘው ዕውቅና | |
| የተለያዩ ተሰጥኦዎቹ | |

### አዳምጦ መረዳት

ማስታወሻችሁን በመጠቀም ስለሙዚቃ ጠቢቡ የሕይወት ታሪክ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ተውሳከግስ

ማስታወሻ

ተውሳከ ግስ ማለት የግስ ጭማሪ ወይም ግስን የሚገልጽ ማለት ነው። ግሱን የሚገልጸው ደግሞ ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ ወዘተ. አንጻር ነው።

ምሣሌ፣ ኃይሉ እዚህ ነበር። (ቦታን)
ጽጌረዳ ነገ ትመጣለች። (ጊዜን)

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ተገቢውን ተውሳከ ግስ በመጻፍ አገልግሎቱን ግለጹ።

ሀ. ሁለቱ ልጆች _______ መጥተዋል።

ለ. አበራ ዛሬ _______ ነበር።

ሐ. ከድጃ ሰፊ ቦታ _______ ገዛች።

መ. አሊ _______ ሄደ።

ሠ. ልጆቹ _______ ናቸው።

ረ. እሷ _______ ነበረች።

ሰ. ቀዩ ልጅ _______ መጣ።

ሸ. ጎበዙ ሯጭ _______ አሸነፈ።

## ማንበብ

### የውሎ ማስታወሻ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

ለሚከተለው ጥያቄ የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

በጣም ተወዳጅ ከሆኑት አንጋፋ ኢትዮጵያዊ ድምፃውያን መካከል ማንን ታውቃላችሁ? ለምን ተወዳጅ የሆኑ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በማንበብ የምንባቡን መልዕክት በድርጊት ቅደምተከተል ለመረዳት ሞክሩ።

### የውሎ ማስታወሻ

«ዓሣ ጎርጓሪ ...» እንዲሉ ... የግል ማስታወሻ ደብተሬን እንዳጋጣሚ አገኘሁና ያኔ የሞነጫጨርኩትን ዳግም ሳነበው አስደነቀኝ። አሁን አሁን የግል ማስታወሻ ወይም «ዳያሪ» መጻፍ ትቻለሁ። የሚጻፍ ጠፍቶ ሳይሆን እያስጠላኝ ስለመጣ ነው። መጥላትም ላይሆን ይችላል፤ ስንፍና ተጨምሮ ሳያዳክመኝ አልቀረም። በሌላ በኩል ሳስበው ደግሞ አለመጻፍ ትልቅ ስህተት ይመስለኛል። ምክንያቱም ነገሮች ተመዝግበው ሲቀመጡና ጊዜያቸው ካለፈ በኋላ ሲያነቧቸው ከአስተማሪነታቸው በተጨማሪ አዝናኝም ናቸውና። ምን ያህል እንደተለወጥን ወይም እንዳልተለወጥን ለማወቅ ጥሩ ማስረጃዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ራስን መታዘቢያም ናቸውና።

> **ሙያዬ ጋዜጠኝነት በመሆኑ ብዙ ማስታወሻዎች አሉኝ።**

ሙያዬ ጋዜጠኝነት በመሆኑ ብዙ ማስታወሻዎች አሉኝ። እስኪ ለማንኛውም ለቅምሻ ያህል በ1986 ዓ.ም. የጻፍኩትን ላካፍላችሁ።

**እሁድ ሚያዝያ 14 ቀን 1986 ዓ.ም.**

በአንድ የሙዚቃ ምሽት ላይ ያልተጠበቀ እንግዳ እንደሚመጣ ሹክሹክታ ተሰማ። ወሬው የደረሰው ሁሉ፣ ጉዞው ወደ«ሂልተን ሆቴል» ሆነ። እኔም ካሜራዬን ይዤ ወደዚያው ቀጠልኩ።

ከሆቴሉ እንደደረስኩ እንግዳ ተቀባዩን የራት ምሽት ላይ እንድገኝ መጠራቴን ገለጽኩለት። መዝገቡን አገላበጠ። ምናልባት ሰዓቱን ብነግረው ሊረዳኝ እንደሚችል ገለፀልኝ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት እንደሚካሄድ ነገርኩት። እንግዳ ተቀባዩም የነገርኩት ትክክል መሆኑን አረጋግጦና እንድገባ ፈቀደልኝ። «አመሰግናለሁ!» ብዬ ቀጥታ ወደሙዚቃ ጥበብ መቋደሻ አዳራሹ አመራሁ። ታዋቂ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር እንግዶች አዳራሹን ሞልተውታል። ወንበር አጥተውም የቆሙ ነበሩ።

ሁሉም እንግዶች ይንሾካሾካሉ። «በእርግጥ ሙሉ በሙሉ ድኖ መዝፈን ይችል ይሆን?» ጎንለጎን ይጠያየቃሉ። ታዋቂ አርቲስቶች እንኳን ሳይቀሩ በጉጉት የሚጠብቁት ነው። ምክንያቱም «ጥላሁን ምናልባት ከአሜሪካ በድንገት ሊመጣና ሊገኝ ይችል ይሆናል» የሚል ሀሳብ ነበር። በዚያን ጊዜ ጥላሁን እንግሊዝ አገር ሲታከም ቆይቶ ለተጨማሪ ሕክምና አሜሪካ ሂዶ ነበር።

መርሃግብሩ ተጀመረ። የባህል ሙዚቃ ቡድኑ ተጋባዦችን እያዝናና፣ በመሐል የተለያዩ ሽልማቶች ለተለያዩ ግለሰቦች ተሰጡ። በመቀጠልም አርቲስት ንዋይ ደበበ፣ አርቲስት ፀሐዬ ዮሐንስ፣ አርቲስት ኤሊያስ ተባባል ተጋባዦችን በመረዋ ድምጻቸው በየተራ እየተነሱ ታዳሚውን አዝናኑ። ይህ ሁሉ ቢከናወንም ተጋባዦች ልባቸው ሙሉ በሙሉ አላረፈም። አንድ ነገር ጎድሎታል፣ ስለጥላሁን ማወቅ።

የመድረኩ መሪ፣ «ለተወሰኑ ወራት በሕክምና ላይ ቆይቶ የነበረውና ዛሬ በመካከላችን በድንገት የተገኘው አንጋፋው፣ ተወዳጁና ተናፋቂው ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ! መድረክ ላይ ቀርቧል!» ሲል አዳራሹ በጭብጨባ፣ በእልልታና በፉጨት አስተጋባ። ተመልካች መጠራጠሩን አላቆመም። ጥላሁን መድረክ ላይ ወጣ። መነጋገሪያውን ጨበጠ። «እዩዋት ስትናፍቀኝ...» አለ በረጅም ትንፋሽ። ይሄኔ ነው ጩኸትና ለቅሶ የተጀመረው። ማመን ያቃታቸው ሰዎች ዓይናቸውን ማሸት ጀመሩ። ግማሾቹ ወደላይ ይዘላሉ። የተቀሩት በሰው ላይ እየተራመዱና ሰው እየረገጡ ወደመድረኩ ይሄዳሉ። በጥላሁን ጉሮሮ ላይ በትልቁ የተገዘገዘ ጠባሳ ይታያል። መዝፈን ግን አልተሳነውም። እሱም ቢሆን የታዳሚዎችን ሁኔታ ሲያይ አይኖቹ እንባ አቀረሩ።

በጥላሁን ጉሮሮ ላይ በትልቁ የተገዘገዘ ጠባሳ ይታያል። መዝፈን ግን አልተሳነውም።

አርቲስቶች ራሳቸው መጮህ ጀመሩ። «ጋሼ ጥላሁን!... ጋሼ !... ጋሼ !...» ማመን አቃታቸው። ምን ያድርጉ? እንኳን የድምጻዊ ጉሮሮ ተሸርክቶ ቀርቶ ጉንፉን ሲይዝ እንዴት እንደሚቸግር የሚያውቁት እነሱ አይደሉ!? ጋሼ ጥሌ! አሁን ፊቱ በላብ ተጠመቀ።

…ገላጋይ ገባ። «ጥላሁን በቃ! ይብቃህ!» ይሉ ጀመር። አንድ አንጋፋ የጥበብ አድናቂ «እባካችሁ ሙሉ በሙሉ አልተሻለውም፤ ለእናንተ ብሎ ነው ከስምንት ሰዓት በረራ በኋላ ረፍት ሳያደርግ በቀጥታ እዚህ አዳራሽ የመጣው» አሉ። የሰማቸው አልነበረም። «በጭራሽ!» አለ ተመልካች። «ጥላሁን፣ የዘንባባ ማርነሽ…. ሞናሊዛ …» እያለ ሲያዜም ሕዝቡ ይጮህል። እንዲዘፈንለት ይፈልጋል።

…ጋሼ ጥሌ ግን ከድካም ሌላ ምንም አልተሰማውም ነበር። ድምፁ ምንም አልተነካም። ይልቁንም ቀርቦ ላየው ሰው የመደንገጥና የመጠራጠር ሁኔታ ከፊቱ ይነበባል። ምክንያቱም ጥላሁን በአንገቱ፣ በእጁና በሆዱ ላይ የደረሰበት ጉዳት የስለት ውጊያ ይመስል ነበር። ከሞት በኋላ ሕይወት ዘርቶ፣ ስለደረሰበት አደጋ ሲጠየቅ፣ «ሁሉንም <u>ሆድ ይፍጀው</u>» የሚለው ተወዳጁና ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጅ ጥላሁን በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅና ተናፋቂ እንደነበር መረዳት የቻልኩት ያኔ ነበር፤ ዛሬም ደግሜ ሳነበው ተገረምሁ። አበቃሁ።

(ሙስጠፋ አህመድ። 1986። *ጦቢያ*። ቅጽ 2፣ ቁ. 10፣ ገጽ 38-39 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት የሚከተለውን የትረካ ቅደምተከተል ቢጋር በማሟላት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

የታሪኩ ጊዜና ቦታ

↓

______

ጽሑፉ ስለማን ይተርካል

↓

______

በታዳሚዎች መካከል የታየ የህሳብ ልዩነት

↓

______

የህሳብ ልዩነቱ የመጨረሻ ውጤት

↓

______

## ተግባር 2

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. «ያልተጠበቀ እንግዳ እንደሚመጣ ሹክሹክታ ተሰማ» ከሚለው ሀሳብ ምን ተረዳችሁ?

ለ. በአንቀጽ ሦስት የተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው?

# 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

## ተግባር

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረግ ተመሳሳይ ፍቻቸውን በምንባቡ መሠረት ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጥበብ | መ. መድረክ | ሰ. ተጋባኘ |
| ለ. መረዋ | ሠ. ሆድ ይፍጀው | ሸ. ቅምሻ |
| ሐ. መነጋገሪያ | ረ. ድምጻዊ | ቀ. አንጋፋ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የውሎ ማስታወሻ መጻፍ

## ተግባር

የሚከተለውን የውሎ ማስታወሻ አጻጻፍ ቅደምተከተል መሠረት በማድረግ የራሳችሁን የአንድ ቀን ውሎ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

ጧት በመኖሪያቤት አካባቢ

↓

[ ]

ከቤት ወደትምህርትቤት በነበረ ጉዞ

↓

[ ]

በትምህርትቤት ውስጥ የነበረ እንቅስቃሴ

↓

ከትምህርትቤት መልስ

↓

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን የውሎ ማስታወሻ አንቀጽ ሥርዓተነጥቡን በማስተካከልና የሀሳብ ቅደምተከተሉን በማደራጀት እንደገና ጻፉ።

ዛሬ ጧት ከመኝታዬ ተነስቼ ጥርት ያለውን የፀሐይ ብርሃን ለ10 ደቂቃ ያህል ሞቅሁ። ከጥዋቱ 1፡30 ሰዓት ቁርስ በላሁ። በመንገድ አቡዬን አገኘሁት። አቡዬ የክፍል ጓደኛዬ ነው። ከዚያ ደብተሬንና መጽሐፌን አዘጋጀሁና ወደትምህርትቤት ሄድኩ። ከአቡዬ ጋር ትምህርትቤት ደረስን። ከዚያም ክፍል ውስጥ ገብተን የመጀመሪያውን ክፍለጊዜ ትምህርት ተማርን። ትምህርትቤት እንደደረስን የሰንደቅ ዓላማ ሥርዓት አከበርን። እስከ አምስተኛው ክፍለጊዜ ያሉትን የትምህርት ዓይነቶች ከተማርን በኋላ እኔ ከአቡዬ ጋር ሣይሆን ብቻዬን ወደቤት ተመለስኩ። ለከሰዓት ትምህርቴ ጉዞ ጀመርኩ። እኔም ምሣ በላሁና አረፍ አልኩ። እማዬ ደብተሬን ተቀብላ ምሣ አቀረበችልኝ።

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የውሎ ማስታወሻ

## ቅድመንባብ

### ተግባር

የሚከተሉትን አንቀጾች ከማንበባችሁ በፊት ትዕምርተጥቅስ፣ ትዕምርተአንክሮ (ቃለ አጋኖ)፣ ነጠብጣብና ትዕምርተጥያቄ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት ግለጹ።

## ማንበብ

### ተግባር

«የውሎ ማስታወሻ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ አንቀጽ 7 ና 8ን የሥርዓተነጥቦችን አጠቃቀም መሠረት በማድረግ አንብቡ።

## መናገር

### ተግባር

«የውሎ ማስታወሻ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው የሀሳብ ቅደምተከተል መሠረት ንግግር አቅርቡ።

የውሎ ማስታወሻ አቅራቢው በመጀመሪያ ወደየት ተጓዘ?

↓

ከዚያስ ምን አጋጠመው?

↓

ቀጥሎስ ምን አየ?

↓

ከዚያ በኋላስ?

↓

ከዚያስ?

↓

በመጨረሻስ?

## ሰዋስው

ማስታወሻ

በአማርኛ ቋንቋ መደብ በሦስት ይከፈላል። እነዚህ መደቦች የሚገለጹባቸው ተውላጠ ስሞችም የሚከተሉት ናቸው።

| መደብ | ተውላጠ ስሞች በቁጥር | |
|---|---|---|
| | ነጠላ | ብዙ |
| 1ኛ. | እኔ | እኛ |
| 2ኛ. ተባእታይ | አንተ | እናንተ |
| አንስታይ | አንቺ | እናንተ |
| 3ኛ. ተባእታይ | እሱ | እነሱ |
| አንስታይ | እሷ | እነሱ |

## ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተውላጠስሞችን፣ ጾታን፣ መደብንና ቁጥርን ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ

| ዓረፍተነገር | ተውላጠ ስም | መደብ | ፆታ | ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| እኔ ነገ መጽሐፍ አነባለሁ። | እኔ | 1ኛ | (አይለይም) | ነጠላ |

| ዓረፍተነገር | ተውላጠ ስም | መደብ | ፆታ | ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. እናንተ ዛሬ እዚህ ተጫወቱ። | | | | |
| ለ. እነሱ ነገ እዚያ ይሰበሰባሉ። | | | | |
| ሐ. እሱ እዚያ መጽሐፍ አነበበ።. | | | | |
| መ. እሷ ትናንት እዚያ ልብሷን አጠበች። | | | | |
| ሠ. እኔ ቀድም እዚያ ነበርኩ። | | | | |

# የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አ-በረታ-ች-ነት | አበረታችነት |
| ለ | ባለሙ-ያ-ነት-ኣቸው | ባለሙያነታቸው |
| ሐ | የ-ብሔር-ኧ-ሰብ-ኦች-ን | የብሔረሰቦችን |
| መ | አስ-ተዋው-ቀው-ኣል | አስተዋውቀዋል |
| ሠ | ተሰጥኦ-ኣቸው-ን | ተሰጧቸውን |
| ረ | አ-ር-ኪ-ቴ-ክ-ቸ-ር | አርኪቴክቸር |

# ማንበብ

## እጅግ የተከበሩ፣ የዓለም ሎሬት፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሥዕሉን በትክክል አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ለ. ከዚህ በታች በሥዕሉ የምታዩአቸው ሰው ዕውቅና ያገኙባቸው ሥራዎች ምን ምን ይመስሏችኋል?

### የማንበብ ሂደት

«እጅግ የተከበሩ፣ የዓለም ሎሬት፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ» የሚለውን ተራኪ ምንባብ በጊዜ ቅደምተከተል የተከናወኑ ድርጊቶችን በመለየት ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ።

## እጅግ የተከበሩ፣ የዓለም ሎሬት፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ



በዓለም የታወቁና እጅግ የተከበሩ ኢትዮጵያዊ ሠዓሊ አፈወርቅ ተክሌ በሰሜን ሸዋ በአንኮበር ከተማ ጥቅምት 13 ቀን 1924 ዓ.ም. ተወለዱ። በህፃንነት ዕድሜያቸው ኢትዮጵያ በጣልያን ተወርራ ነበር። የጣሊያን የግፍ ወረራና ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን የሰው፣ የንብረትና የባህል ጥፋት በሕጻንነት ዕድሜያቸው ተመልክተዋል። በዚህ ምክንያት አፈወርቅ የሚያስቡት የግፍ ወረራው ያስከተለውን ጥፋት እንደገና ስለመገንባት ነበር።

> **መምህራን የተማሪዎችን ተሰጥኦ ጠቋሚና መሪ ናቸው።**

አፈወርቅ በወቅቱ ለሀገር ግንባታ አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት ማግኘት ፈለጉ። ለማጥናት የፈለጉትም የማዕድን ምህንድስና ነበር። የአፈወርቅ ቤተሰቦች ግን የኪነጥበብ ስጦታ

እንዳላቸው ስለሚያውቁ ኪነጥበብ እንዲማሩ ይፈልጉ ነበር። ምክንያቱም በጊዜው በቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚሥሏቸው ሥዕሎች የኪነጥበብ ተሰጥኦቸውን የሚያሣዩ ነበሩ። ነገርግን ያሰቡትን ትምህርት ለመማር ይፈልጉ ስለነበር ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በተገቢው እንዲማሩ ምክር ተቀብለው በእንግሊዝ አዳሪ ትምህርትቤት የምህንድስና ትምህርታቸውን ተከታተሉ። በሒሳብ፣ በኬሚስትሪና በታሪክ ጥሩ ውጤት አስመዝግበው የምህንድስና ትምህርታቸውን አጠናቀቁ። ሆኖም አስተማሪዎቻቸው የተፈጥሮ ተሰጥያዋቸው ኪነጥበብ እንደሆነ ነግረዋቸው ስለነበር በኪነጥበብ ስጦታቸው ላይ የበለጠ ለማተኮር ወሰኑ። ከዚያም በለንደን የኪነጥበብ ማዕከላዊ ትምህርትቤት ገብተው ተማሩ።

## የኪነጥበብ ሕይወት

አፈወርቅ ለከፍተኛ የኪነጥበብ ጥናት በታዋቂው የለንደን ዩኒቨርስቲ በሥሌድ ኪነጥበብ ማዕከል የመጀመሪያ አፍሪካዊ ተማሪ ሆነው ተመዘገቡ። በዚህም በሥዕል፣ በቅርፅና አርኪቴክቸር ጥናቶች ላይ አትኩረው በመማር ተመረቁ። ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የብሔረሰቦችን ባህልና ወግ ሲያጠኑ ቆዩ። በመጀመሪያ የተማሩትን የምህንድስና ሙያ ርግፍ አድርገው ትተው በኪነጥበብ ሙያቸው ላይ ለማትኮር ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ። በዚህም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያንፀባርቁ ሥራዎችን እያሳዩ ማገልገላቸውን ቀጠሉ።

አፈወርቅ በ22 ዓመታቸው የመጀመሪያ ሥራቸውን የሚያሣይ የኪነጥበብ ትርዒት በአዲስ አበባ ማዘጋጃቤት አቀረቡ። በወጣትነት ዕድሜያቸው ባቀረቡት ትርዒትም ጥሩ ገቢ አግኝተዋል። ከትርዒቱ ባገኙት ገቢም ተመልሰው ወደአውሮፓ በመሄድ ለሁለት ዓመት የኪነጥበብ ትምህርት ቀስመዋል። በዚህም በጣልያን፣ በፈረንሳይ፣ በእስፔን፣ በፖርቹጋል፣ በብሪታኒያና በግሪክ እየተዘዋወሩ የጠበቀ የኪነጥበብ ትምህርት ተምረዋል። ከኪነጥበብ ሥራዎች መካከል የመስታወት ሥዕልና የ«ሞዛይክ» አሠራር ጥበብን ተምረዋል። ከዚያም ወደሀገራቸው ተመልሰው የተለያዩ ሥራዎችን አከናውነዋል። ከሠሯቸው ሥራዎች መካከል የ«ቀዳማዊ ምፅዓት ፍርድ»፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የዘውድ ሥርዓትን የሚያሳየው ሥዕል፣ በሐረር ከተማ የሚገኘው የልዑል ራስ መኮንን ሐውልትና ሌሎችም ሥራዎች ይጠቀሳሉ።

> ባገኙት ዓለማቀፋዊ ዕውቅና በዓለም ላይ ከሚገኙ ስመጥርና ታላላቅ ከተሰኙ 200 ሰዎች ጋር የሕይወት ታሪካቸውና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በጨረቃ ላይ እንዲያርፍ አስደርገዋል።

እነዚህ የኪነጥበብ ውጤቶች ለሕዝብ እይታ የቀረቡና በ«ቴምብሮች» ላይ እየወጡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የኪነጥበብ ትርዒት ላይ ሲታዩ አርቲስቱ በጣም እየታወቁና እየገነኑ መጡ። በዓለምአቀፍ ደረጃ ታላቅ አድናቆትን አተረፉ። በዚህም ከ97 በላይ ሽልማቶችን በዓለምአቀፍ ደረጃ ከተለያዩ ተቋማት ለማግኘት ችለዋል።


በአጠቃላይ አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ አርአያነት ያላቸው የኪነጥበብ ሰው በመሆናቸው «እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት» የተባለውን እጅግ የተከበረ ማዕረግ ለማግኘት በቅተዋል። እኚህ የኪነጥበብ ባለሙያ፣ ኪነጥበብ የሰው ልጅን መንፈስ ለማዳበር፣ ሀገርን ለማሣደግ፣ ለማሳወቅና ለሕይወት ጥሩ ተስፋ ለመፍጠር የላቀ ሚና እንዳለው ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በዚህ ምክንያት ለሀገራቸው በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል። በኪነጥበብ ሥራቸው የሀገራቸውን ባህልና ወግ ለውጭው ዓለም አስተዋውቀዋል። ባገኙት ዓለማቀፋዊ ዕውቅና በዓለም ላይ ከሚገኙ ስመጥርና ታላላቅ ከተሰኙ 200 ሰዎች ጋር የሕይወት ታሪካቸውና የኢትዮጵያ ሰንደቅዓላማ በጨረቃ ላይ እንዲያርፉ አስደርገዋል። ሥራዎቻቸውንም ለአሁኑ ትውልድ አሻግረዋል። በሁሉም ዓርአያነት ባላቸው ተግባሮቻቸው ተጠቃሽ የኪነ ጥበብ ሰው ሆነዋል።

(ፍቅር ይምራን። *ከኢትዮጵያን ድረገጽ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በሥሩ ሊካተቱ የሚችሉትን ነጥቦች ጻፉ።




## 8ኛ ቀን

## ቃላት

## ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ የቃላቱን ዝርዝር ከመገለጫዎቻቸው ጋር ይህን (✓) ምልክት በማድረግ አዛምዱ፤ ከመሥራታችሁ በፊት ሠንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጁ።

| የቃላት መግለጫ | ቃላት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሠዓሊ | ባህል | አርቲስቶች | ሞዛይክ | አርኪዎ | ሎሬት | ቴምብር | ተሰጥኦ | ወግ |
| ተዋንያን፣ ሙዚቀኞች፣ ሠዓሊዎች፣ ደራሲዎች | | | | | | | | | |
| በሥራው ለሌሎች ምሣሌ የሆነ ሰው | | | | | | | | | |
| በዓለምአቀፍ ደረጃ ለታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች የሚሰጥ ከፍተኛ ማዕረግ | | | | | | | | | |
| እርሳስ፣ ቀለምና ሸራ የሚጠቀም የጥበብ ሰው | | | | | | | | | |
| የአንድ ማህበረሰብ አመጋገብ፣ አኗኗር፣ አለባበስ ወዘተ. | | | | | | | | | |
| የሥዕል ዓይነት | | | | | | | | | |
| ከጥንት ሲያያዝ የመጣ የማህበረሰቡ ሥርዓትና ደንብ | | | | | | | | | |
| በፖስታ፣ በደብዳቤና በንግድ ፈቃድ ላይ የሚለጠፍ | | | | | | | | | |
| ልዩ ተፈጥሯዊ ችሎታ | | | | | | | | | |


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በሕይወት ታሪክ ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ መሪ ወይም ዋና ዋና ሀሳቦችን ካሰፈራችሁ በኋላ አስፋፍታችሁ የሕይወት ታሪካችሁን በሦስት አንቀጽ ጻፉ።




## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

ከዚህ በታች በቀረበው አንድ አንቀጽ ውስጥ በተጓደሉ ሥርዓተነጥቦች ምትክ ቁጥሮች ገብተዋል። እያንዳንዱን ቁጥር በአስፈላጊው ሥርዓተነጥብ ተኩ።

ተማሪዎች በሦስት ቡድን ተቧደኑ 1 ከዚያም በየቡድናችሁ ቀጥሎ የተሰጧችሁን ተግባራት ያዙ 2 በመቀጠልም በመምህራችሁ አማካይነት በአቅራቢያችሁ ወደሚገኝ የማህበራዊ ጉዳይ መ 3 ቤት ሂዱ። ከዚያም ለኃላፊው 4 ለባለሙያዎችና ለሌሎችም ሠራተኞች ቃለመጠይቅ አድርጉ 5 በዚህ መንገድ ያሰባሰባችሁትን ሀሳብ ክፍል ውስጥ በማቅረብ ተወያዩበት።

## 9ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## እጅግ የተከበሩ፣ የዓለም ሎሬት፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

አንድን ምንባብ ስታነቡ ፍጥነታችሁን እንዴት ትለካላችሁ? አገላለጻችሁስ እንዴት ቢሆን ይመረጣል?

### ማንበብ

#### ተግባር

«እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ» የሚለውን ምንባብ በቅጹ አስፈላጊውን መረጃ እየሞላችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን አንብቡ።

| ተማሪ (በየተራ) | የማንበብ ፍጥነት በቃላት ብዛት | የቃላት ድግግሞሽ | አገላለጽ |
|---|---|---|---|
| የመጀመሪያው የማንበብ ሂደት | | | |
| ሁለተኛ ጊዜ የማንበብ ሂደት | | | |

ማብራሪያ፦

- በፍጥነት ከተነበበ ✓
- በፍጥነት ካልተነበበ ×
- ቃላት ካልተደገሙ ✓
- ቃላት ከተደገሙ ×
- ጥሩ አገላለጽ ከሆነ ✓
- ጥሩ አገላለጽ ካልሆነ ×

## መናገር

### ተግባር

በአካባቢያች ታዋቂ ስለሆኑ አንድ ሰው፣ ስለሰሯቸው ሥራዎች በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን የጋራ ሀሳብ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ተውሳከግስ፣ ተውላጠስምና መደብ

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ቃላት በተገቢ ቦታቸው መድቡ።

| ዓረፍተነገር | | በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያለው የተውሳከ ግስ ዓይነት | | | በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያለው ተውላጠ ስም | መደብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የጊዜ | የቦታ | የሁኔታ | | |
| ሀ | እሱ ትናንት እዚህ አልነበረም። | | | | | |
| ለ | እኔ ይህንን ጉዳይ በቀላሉ አላየውም። | | | | | |
| ሐ | አንቺ ነገ ወደወላጆችሽ ትሄጃለሽ። | | | | | |
| መ | አንተ ቅድም እዚህ አልመጣህም። | | | | | |
| ሠ | እነርሱ ጎበዞች ናቸው። | | | | | |





# ውኃና ጥቅሙ

ምዕራፍ 5

## የሚጠጣና የማይጠጣ ውኃ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጎች በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | መድሀኒት-ኦች-ን | መድሀኒቶችን |
| ለ | አሳስቦ-ኣት-ኣል | አሳስቧታል |
| ሐ | ነግረ-ዋ-ኣት-ኣል | ነግረዋታል |
| መ | የ-ሚ-ያሰቃይ-ኣቸው | የሚያሰቃያቸው |

## ማንበብ

### ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ሰዎች በተስቦ፣ በአንጀት ቁስለትና በጃርዲያ በሽታዎች የሚያዙት በምን ምክንያት ይመስሏችኋል?

ለ. በውኃ አማካይነት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎችን እንዴት መከላከል ይቻላል?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ» የሚለውን ምንባብ ስታነቡ ባለታሪኳ ለሚያጋጥሟት ችግሮች ቀድማችሁ መፍትሔውን በመገመት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ

በአዲስ አበባ ወጣ ባለው ገጠራማ አካባቢ ወይዘሮ ተዋበች የምትባል አንዲት እማወራ ትኖራለች። ይህች እናት ሰሞኑን እየተመላለሰ ቤተሰቧን የሚያሰቃያቸው የቁርጠት በሽታ ቋሚ መፍትሔ አለማግኘቱ በጣም አሳስቧታል። የቤተሰቦቿ አባላት በሽታው በተነሳባቸው ቁጥር ከሚሔዱባቸው ክሊኒኮች የተለያዩ መድሀኒቶችን እየያዙ መምጣትን ተላምደውታል። ተስቦ፣ የአንጀት ተስቦ፣የአንጀት ቁስለት፣ጃርዲያና የመሳሰሉት ለበሽታው ከሚሰጡ ስሞች ጥቂቶች ናቸው። የእነዚህ በሽታዎች መነሻ ደግሞ ንፅህናው ያልተጠበቀ ውኃና የተበከለ ምግብ እንደሆነ ሐኪሞች ደጋግመው ነግረዋታል፤ ቢሆንም ወይዘሮ ተዋበች በአካባቢዋ ንፁህ የቧንቧ ውኃ ባለመኖሩ ምክንያት ለምግብ ማብሰያና ለመጠጥ ከጉርጓድና ከወንዝ የምታመጣውን ውሃ በንፅህና ለመያዝ ብትሞክርም፣ የቤተሰቦቿ ህመም ሻል ያላቸው ቢመስልም ማገርሸቱ ግን አልቀረም።

በዚህ የተነሳ ይህች እናት ከወንዝና ከጉድጓድ ያመጣችውን ውኃ ሳታፈላ ለመጠጥ መጠቀሟን ቆም ብላ አስተዋለች። በመቀጠልም ይህ ውኃ ንፁህ እንዳልሆነ ሲገባት እጅጉን አሳሰባት። የአራትና የአምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆቿ ጤናቸው የታወከውም በዚህ ምክንያት ይሆናል ብላም ገመተች፤ ከዚያም የህፃናቱ ችግር ንፅህናው ያልተጠበቀ ምግብና ውኃ ሊሆን እንደሚችል ሐኪሞቹ ሲናገሩ የሰማችው ትዝ አላት። ለዚህ ችግር መንስኤው ደግሞ በመንግስት ድጋፍና በማህበረሰብ ትብብር በእነወይዘሮ ተዋበች ሰፈር የተገነባው የቧንቧ ውኃ ብረቱ በሌቦች ተነቅሎ መወሰዱ ነው።

ጥርጣሬዋ እየጨመረ ሲመጣ ውኃውን በብርጭቆ እየቀዳች ማስተዋል ጀመረች። በብርጭቆው ውስጥ ውኃውን ስትመለከተው ንፁህ አለመሆኑ የበለጠ አስጨነቃት ወይዘሮ ተዋበች ለሐኪሙ መንገር እንዳለባት ወሰነች፤ ከዚያም ወደ ጤና ተቋም ሄዳ ለመጠጥ የምትጠቀመው የወንዝና የጉድጓድ ውሃ ንፁህ እንዳልሆነ ለሀኪሙ ተናገረች። ሀኪሙም ውኃ በህይወት ለመኖር አስፈላጊ ቢሆንም ንፅህናው ካልተጠበቀ ግን ለከፍተኛ ሕመም እንደሚያጋልጥ አስረዳት። በመቀጠልም የሚጠጣና የማይጠጣ ውኃ ለይቶ ማወቅ ጠቃሚ ነው። የተገኘው ውኃ ሁሉ ለመጠጥ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ከኩሬ፣ ከወንዝ፣ ከሐይቅ፣ ከግድብና ከጉድጓድ የሚገኝ ውኃ እንዲሁ ከተጠጣ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል። ስለዚህ ከነዚህ ቦታዎች የሚገኝ ውኃ ተፈልቶ ለመጠጥ መዋል ይኖርበታል። የቧንቧ

ውኃም ቢሆን በአጋጣሚ ቧንቧው ተሰብሮ ወይም ተበላሽቶ ሊበከል ስለሚችል አፍልቶ መጠቀም ያስፈልጋል በማለት መከሯት።

ወይዘሮ ተዋበች ሐኪሙ የመከራትን በመቀበል በመጀመሪያ የሚጠጣና የማይጠጣ ውኃ መኖሩን ተገነዘበች። ከዚያም የተለያዩ የውሃ ማጣሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ጀመረች። በዚህም ምክንያት ከወንዝና ከጉድጓድ የቀዳችውን ውኃ አፍልታ መጠቀም ጀመረች። ከዛን ጊዜ ጀምሮ ውኃው እየተንተከተከ እንፋሎት እስኪወጣው ድረስ ታፈላዋለች ሲቀዘቅዝ በባልዲ ወይም በጀሪካን ትገለብጥና መልሶ እንዳይበከል ትከድነዋለች። ለመጠጣት ሲፈለግ በንፁኅ ኩባያ ወይም ብርጭቆ በመቅዳት ቤተሰቦቿ ለመጠጥ እንዲጠቀሙት ታደርጋለች። ይህንን ተግባር ለተከታታይ ሳምንታት ተጠቀመች።





ወይዘሮ ተዋበች ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ውኃን አፍልቶ ከመጠጣት በተጨማሪ ሌላ ዘዴ መጠቀም አሰበች ስለጉዳዩ የአካባቢ ሰዎችን ስታማክር የውኃ ማከሚያ መድሐኒቶችን መጠቀም አማራጭ እንደሆነ ነገሯት። የውኃ ማከሚያ መድሀኒት የሚጠጣ ውኃ ለማጣራት የሚያገለግል መሆኑን ተገንዝባ መጠቀም ጀምራለች።

በመጨረሻም ወይዘሮ ተዋበች የሐኪሙንና የአካባቢዋን ኗሪዎች ምክር ተቀብላ ንፁህ ውኃ መጠቀም ቻለች። ከወንዝና ከጉድጓድ የምትቀዳውንም ውኃ በማፍላት ወይም የውኃ ማከሚያ መድሀኒት በመጨመር መጠቀም የዘወትር ልምዷ አደረገች። የልጆቿም ጤንነት ቀስበቀስ መሻሻል አሣየ።

ምንጭ (ከአዲስ አድማስ ድረገፅ። መነሻነት የተዘጋጀ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ምንባቡን መሠረት በማድረግ በ«ለ» ረድፍ የተዘረዘሩትን ጥቅል ሀሳቦች በ«ሀ» ረድፍ ከተዘረዘሩት አንቀጾች ጋር በተስማሚው አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. ተዋበች የሀኪም ምክር አገኘች። |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. ውኃን ለማጣራት የተለያዩ ዘዴዎች ተጠቀመች። |
| 3. አንቀጽ ሦስት | ሐ. የተዋበች ልጆች የጤንነት ሁኔታ ተሻሻለ። |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. ተዋበች ቤተሰቦቿ በሕመም መሰቃየታቸው አሳሰባት። |
| 5. አንቀጽ አምስት | ሠ. ተዋበች ያገኘችውን ምክር ተግባራዊ አደረገች። |
| 6. አንቀጽ ስድስት | ረ. የተገነባው የቧንቧ ውኃ ብረቱ በመሰረቁ ተዋበች የወንዝና የጉድጓድ ውኃን ለመጠጥ ተጠቀመች። |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከሥዕሉ የተመለከታችሁትን ተግባር ወይዘሮ ተዋበች አከናወነች ብንል፣ የወይዘሮ ተዋበች ቤተሰቦች የወደፊት የጤና ሁኔታ ምን ሊሆን ይችላል?

ለ. ማጣራት የሚያስፈልገው ከየት የሚገኝን ውኃ ነው?

ሐ. ወይዘሮ ተዋበች በውኃ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን መከላከል የጀመረችው በምን መንገድ ነው?

መ. ንፁህ ውኃ በዘላቂነት ለማግኘት ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 2ኛ ቀን

# ቃላት

## የቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ምሣሌ

ደፈረሰ ⟶ ውኃው ደፈረሰ። (ቆሸሸ)

የሕዝቡ ሰላም ደፈረሰ። (ታወከ)

የጓደኛዬ ዓይን ደፈረሰ። (ቀላ)

ሀ. እሷ ለችግሯ ቋሚ መፍትሔ አገኘች።

ሰውዬው የሰርጉ ቋሚ ነበር።

ለ. ልጁ ከእንቅልፉ ተነሳ።

ከዚህ በፊት የነበረባቸው በሽታ ተነሳ።

ሐ. የውኃ ቧንቧ ብረት በሌቦች ተነቀለ።

ዛፉ ከሥሩ ተነቀለ።

መ. ተማሪዎች ያቀረቡት ሀሳብ ድጋፍ አገኘ።

የቧንቧው ውኃ በመንግሥት ድጋፍ ተሠራ።

ሠ. የምንጭ ውኃ ተጣርቶ ለመጠጥ ይውላል።

የነገሩ ምንጭ ታወቀ።

ረ. ውኃን ከመጠጣት በፊት ቆሻሻውን ማጣራት ያስፈልጋል።

ከመጣላት በፊት የነገሩን መነሻ ማጣራት ጥሩ ነው።

ሰ. በሂድክበት መዋል የለብህም።

የተጣራ ውኃ ለመጠጥ መዋል አለበት።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በተራኪ ስልት አንቀጽ መጻፍ

**ተግባር**

«ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ተከታዩን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በተራኪ የአጻጻፍ ስልት በሦስት አንቀጾች አሳጥራችሁ ጻፉ።

መግቢያ

↓

ሀተታ

↓

መደምደሚያ

### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

ቀጥሎ በቀረበው አንቀጽ ውስጥ የሚታዩትን የፊደላት ግድፈትና የሥርዓተነጥብ ስህተቶች በማስተካከል እንደገና ጻፉ።

> ውድ ተማሪዎች! በመቀጠል ደግሞ በቤተሰብ ውስጥ የልጆችን ቁጥር ለመጠንና አራርቆ ለመውለድ የሚያስችሉ ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ እገልፅላችኋለሁ፡ ወሊድን ለመቆጠርና ቤተሰብን ለመመጠን የሚያስችሉ የተለያዩ የፅንስ መከላከያ ዘዴዎች አሉ። ከነዚህ መካከል ኮዶም፡ በማህፀን የሚቀመጥ (ሉፕ)፡ በክንድ የሚቀበር (ኖርፕላንት)፡ ዲያፍራም፡ እንክብሎች የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ሰዎችም የመረጡትን በመጠቀም የልጆችን ቁጥር መመጠን ይችላሉ።

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በተሻለ ፍጥነትና በጥሩ አገላለጽ ለማንበብ የምንጠቀምባቸውን ብልሀቶች በቃላችሁ ዘርዝሩ?

### ማንበብ

**ተግባር**

«ተዋበችና የውኃ አጠቃቀሟ» የሚለውን ምንባብ በተሻለ ፍጥነትና በጥሩ አገላለጽ አንብቡ። ምንባቡን በምታነቡበት ጊዜ የአንዳችሁ ድምፅ ሌላችሁን በማይረብሽበት መልኩ ይሁን።

# ማዳመጥ

## ውኃ ያድናልም ይገድላልም

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**


በሚከተለው ጥያቄ ላይ በመወያየት መልሱን በቃላችሁ ግለጹ።

ውኃ ሊያድንም ሊገድልም የሚችለው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ በማዘጋጀት «ውኃ ያድናልም ይገድላልም» የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ያዙ።




## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

«ውኃ ያድናልም ይገድላልም» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ስታዳምጡ የጻፋችኋቸውን ቁልፍ ሀሳቦች በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮች

ማስታወሻ

አዎንታዊ ዓረፍተነገር ማለት ስለዓረፍተነገሩ ባለቤትና በግሱ ስለተጠቆመው ድርጊት ሳያፈርስ መናገርን የሚመለከት ነው። አሉታዊ ዓረፍተነገር ደግሞ መጀመሪያ የታወቀን ወይም የተነገረን ሀሳብ የሚያፈርስ አገላለጽ ነው። አዎንታዊ ዓረፍተነገር አዎንታዊነቱን የሚያሣይ ቅጥያ የለውም። አሉታዊ ዓረፍተነገር ላይ ግን ግሱ ላይ አል-(-ም) የሚሉ ቅጥያዎችን ይወስዳል።

## ተግባር

ከዚህ በታች የተሰጡትን ዓረፍተነገሮች አዎንታዊና አሉታዊ በማለት ለዩ።

ሀ. የወይንሐረግ የተሠራውን ሥራ አላየችም።

ለ. በስብሰባው ላይ ብዙ ሰው አልተገኘም።

ሐ. ለቃለመጠይቅ ያለፉ ተማሪዎች ዛሬ ይፈተናሉ።

መ. ወደቤታቸው የሄዱት ልጆች እንደገና መጡ።

ሠ. ራስን ከኤች.አይ.ቪ. መጠበቅ ብልህነት ነው።

ረ. ጠንክሮ መሥራት ለሀገር ልማት ይበጃል።

ሰ. አቶ ወርቁ ወደትግራይ አልሄደም።

ሸ. ትምህርትቤታችን ሥራውን በመስከረም ጀመረ።

ቀ. በሕይወት ለመኖር ውኃ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

በ. ልጁ ጎበዝ ተማሪ መሆኑን አላወቅሁም።

## ማንበብ

### ውኃና ሕይወት

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ውኃ ለምን ለምን እንደሚጠቅም በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተወያዩና በቃላችሁ ግለጹ።

#### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ፣ ምክንያቶቹ ሊያስከትሏቸው የሚችሉ ውጤቶችን በመገመት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ውኃና ሕይወት

> **ውኃ ከሌለ ሕይወት የለም፤ ስለዚህ ውኃን ልንከባከበው የሚገባ የተፈጥሮ ሀብት ነው።**

ሕይወት ላላቸው ነገሮች ከሚያስፈልጉ ንጥረነገሮች ዋነኛው ውኃ ነው። በዚህ ምክንያት ሰዎች፣ እንስሳትና ዕፅዋት በሕይወት ለመኖር ውኃ ያስፈልጋቸዋል። ሰዎች ውኃን ለመጠጥ፣ የግል ንፅህናን ለመጠበቅ፣ ምግብ ለማብሰልና፣ ቁሳቁሶችን ለማፅዳት ይገለገሉበታል። ከዚህም በተጨማሪ ውኃ ለኃይል ምንጭነት፣ ለመስኖ፣ ለደን ልማት፣ ለእርሻ ሰብልና ለመሳሰሉት በጣም ጠቃሚ ነው። በዚህ የተነሳ ውኃ ለሰው ልጆችና ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ እንደትልቅ ሀብት ይቆጠራል።

ውኃ በሰውነታችን ውስጥም በርካታ ተግባራትን ያከናውናል። ምግብና ማዕድናት በደም ውስጥ የሚዘዋወሩት በውኃ አማካይነት ነው። የተለያዩ ቆሻሻዎች ከሰውነታችን የሚወገዱት በውኃ አማካይነት ነው። የሰውነት ፈሳሽ ሚዛን የሚጠበቀው በውኃ ነው። በተጨማሪም ውኃ የአጥንት መገጣጠሚያዎች እንዲተጣጠፉ በማድረግ

ረገድ የራሱ ድርሻ አለው። በሰውነት ውስጥ የፕሮቲንና የካርቦሃይድሬት ዑደት ውጤቶች፣ ሰውነት በሚጠቀምበት መልኩ የሚቀየሩት በውኃ አማካይነት ነው። ውኃ የሰውነትን ሙቀት በመቆጣጠር ረገድም ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከተለያዩ ንጥረምግቦች እጥረት ይልቅ የውኃ እጥረት ካጋጠመ በሕይወት መኖር አይቻልም። ምክንያቱም ያለውኃ ከ10 ቀናት በላይ በሕይወት መቆየት እንደማይቻል የተለያዩ የምርምር ግኝቶች አረጋግጠዋል።

ውኃ ለመጠጥ ከመዋሉ በተጨማሪ ለኃይል ምንጭነትም ያገለግላል። ትላልቅ ወንዞችና ሐይቆች ተገድበው ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ይውላሉ። ሀገሮች ለዕድገታቸውና ለልማታቸው ተገቢና በቂ የሆነ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል። ኢትዮጵያም በዕድገት ጎዳና ለመገስገስ ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል የምታገኘው ከውኃ ነው። ለምሣሌ፦ ተከዜ፣ ግልገል ጊቤ፣ አባይ፣ ጣና፣ አዋሽ የመሳሰሉት ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት እየዋሉ ነው።

> **ውኃ ለመጠጥ ከመዋሉ በተጨማሪ ለኃይል ምንጭነትም ያገለግላል።**

ውኃን ለኃይል ምንጭነት መጠቀም ካልቻልን ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ያጋጥመናል። በዚህ ምክንያት በከፍተኛ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ፋብሪካዎች ይስተጓጎላሉ። የመብራት አገልግሎትም እንደልብ ማግኘት አይቻልም። በቂና አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌለ ደግሞ የሚፈለገው የሀገር ዕድገት ሊመጣ አይችልም።

> **ውኃ ከኃይል ምንጭነት በተጨማሪ ለመስኖ አገልግሎት ይውላል።**

ውኃ ከኃይል ምንጭነት በተጨማሪ ለመስኖ አገልግሎት ይውላል። የዝናብ ወቅትን ብቻ ጠብቆ በማምረት ገቢን ለማሳደግና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያስቸግራል። ለምሣሌ ውኃን ገድቦ ለመስኖ መጠቀም በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ለማምረት ያስችላል። በዚህ ሁኔታ በመስኖ በመጠቀም ለምግብ ፍጆታና ለገበያ የሚሆን ምርት በሰፊው ማምረት ይቻላል። በአጭር ጊዜ ምርት የሚሰጡ የጓሮ አትክልቶችንም አምርቶ ለመጠቀም ያስችላል።

ውኃ በቱሪዝም ሀብትነትም የሚሰጠው አገልግሎት ቀላል አይደለም። በአሁኑ ጊዜ የውኃ ቱሪዝም አዝናኝ ሆኖ ተገኝቷል። ባህር አቋራጭ ዋና፣ የጥልቅ ውኃ ውስጥ ሽርሽር፣ የውኃ ውስጥ እንስሳት ጉብኝትና የውኃ ዳርቻ ስፖርታዊ መዝናኛዎች

የውኃ ቱሪዝም ዘርፎች ናቸው። ለምሣሌ በኢትዮጵያ በባህር ዳር፣ በሀዋሳና በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚገኙት ሀይቆች ባሏቸው በርካታ መዝናኛዎች የጐብኚዎችን ቀልብ በመሣብ አገሪቱ የቱሪስት መናኸሪያ እንድትሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እንዲሁም በርካታ ሐይቆች የሚገኙበት የታላቁ ስምጥ ሸለቆም በጎብኚዎች ተወዳጅ ነው። የእንስሳት ቱሪዝምን በውኃ ላይ ይዞ የሚገኘው የጫሞ ሐይቅም በጎብኚዎች ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፏል።

በአጠቃላይ ውኃ በሕይወት ለመኖር ከማስቻሉም በላይ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስለሆነም የተፈጥሮ ስጦታ የሆነውን ውኃ በአግባቡ ከጥቅም ላይ እንዲውል በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል። ለዚህም ውኃ የሚገኝባቸው ወንዞችና ሐይቆች እንዳይደርቁ ደን በማልማት የአየር ሙቀትን መቀነስ ብሎም መቋቋም ያስፈልጋል። ሙቀት ከበዛ ዝናብ ሊኖር አይችልም። ዝናብ ከሌለ ደግሞ ውኃ ሊኖር አይችልም።

(*ከዌልነስ ኢትዮጵያ ድረገጽ። መነሻነት የተዘጋጀ*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በሠንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት ምክንያቶች ለእያንዳንዳቸው ቢያንስ ሁለት ውጤቶችን ጻፉ።

ምሣሌ፦


| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ወንዞችና ሐይቆችን በአግባቡ መያዝ | የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት በስፋት ማግኘት ይቻላል። |
| | በመስኖ እርሻ ምርታማነትን ማሣደግ ይቻላል። |

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ሀ. የውኃ ሀብትን በአግባቡ መያዝ ወይም መጠቀም | ሀ. |
| | ለ. |
| | ሐ. |
| ለ. ውኃን ለኃይል ምንጭነት አለመጠቀም | ሀ. |
| | ለ. |
| | ሐ. |

| | |
|---|---|
| ሐ. የውኃ አለመኖር | ሀ. |
| | ለ. |
| | ሐ. |

## ተግባር 2

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ሀሳቦች በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሑፍ ግለጿቸው።




## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### አያያዦችን በዓረፍተነገሮች ውስጥ መጠቀም

## ተግባር

የሚከተሉትን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት በተስማሚ ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለምሳሌ | ስለዚህ | እና | በተጨማሪም |
| ነገርግን | በአጠቃላይ | ምክንያቱም | በመሆኑም |

ሀ. ውኃ የሰውነት ሙቀትን ይቆጣጠራል፤ ________ የሰውነት ሙቀት ተገቢ በሆነ ልክ እንዲወሰን ያደርጋል።

ለ. ውኃ ለመጠጥ፣ የግል ንፅህናን ለመጠበቅና ምግብን ለማብሰል ይጠቅማል፤ ________ ለኃይል ምንጭነት፣ ለመስኖና ለደን ልማት ያገለግላል።

ሐ. የውኃ እጥረት ካጋጠመ ሕይወት አይኖርም፤ ________ ያለውኃ ከአሥር ቀናት በላይ መኖር አይቻልም።

መ. ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል የምታገኘው ከውኃ ነው፤ ________ ተከዜ፣ ግልገል ጊቤ፣ አባይና አዋሽ ተገድበው ለኃይል ምንጭነት እየዋሉ ነው።

ሠ. ________ ውኃ በሕይወት ለመኖር የሚያስችል የተፈጥሮ ሀብት ነው።

ረ. ውኃ ________ ሕይወት የማይለያዩ ነገሮች ናቸው።

ሰ. የዝናብ እጥረት ካለ ድርቅ ይከሰታል፤ ________ የዝናብ ዑደት እንዲፈጠር ውኃን መንከባከብ ያስፈልጋል።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

በ2ኛ ሳምንት፣ በ4ኛ ቀን በአንብቦ መረዳት ሥር በሠንጠረዥ ያሠፈራችኋቸውን የምክንያትና ውጤት ሀሳቦች መሠረት በማድረግ ሁለት አንቀጾች ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

#### ተግባር

በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ የሚታዩትን ግድፈቶችና የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች አስተካክላችሁ ጻፉ።

ግን ምን ነካን!? በራስ መኩራታችን የት ደረሰ። የሀገርና  የወገን ፍቅራችን ምን በላው? በሀገር ናፍቆት ትምህርታቸውን ምኞታቸውን ትተው የሚመጡ ልጆች የት ደረሰ? በሀገር ሠርቶም ተሹሞም ተንገላቶም ወዘተ. ከመኖር ይልቅ የሰው አገር ወራዳ ሥራ የሚያልም ትልድ ከየት መጣ? የማውቁት ሀገር አይናፍቅም ይባል ነበር። በማናውቀው አገር ናፍቆት ልንሞት ነው! የሆነውስ ሆነ፣ ማንናችን ነን ተጠያቂ!?

(ኢ.ብ.ክ.መ. ት.ም.ቢ.. 2004። *የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ።* ገጽ 18)

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ውኃና ሕይወት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

ውኃ ከሕይወት ጋር ያለው ተያያዥነት ምን እንደሆነ በቡድን ተወያይታችሁ በቃላችሁ ግለጹ።

### ማንበብ

#### ተግባር

«ውኃና ሕይወት» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን አንቀጽ ተራ በተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

# መናገር

## ሀሳብን በምክንያትና ውጤት መግለፅ

ማስታወሻ

ንግግር ስታቀርቡ የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውሉ፦

- ንግግርን በምክንያትና ውጤት ላይ መመሥረት፣
- የአድማጭን ስሜት መከታተል፣
- አካላዊ እንቅስቃሴና የተለያዩ የአገላለጽ ስልቶችን በመጠቀም አድማጮችን ማሳመን።

#### ተግባር

ውኃ ሰዎችን እንዴት ሊጎዳ ይችላል? በሚለው ጥያቄ ላይ በመወያየት የደረሳችሁበትን የጋራ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### መጠይቃዊ ቃላትና ዓረፍተነገሮች

ማስታወሻ

መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ምላሽ የሚሹ ዓረፍተነገሮች ናቸው። እነዚህ ዓረፍተነገሮች አብዛኛውን ጊዜ በመጠይቃዊ ቃላት አማካይነት ይመሠረታሉ። መጠይቃዊ ቃላት የሚባሉት፣ ማን? ምን? ለምን? እንዴት? መቼ? የት? የሚሉት ናቸው።

### ተግባር

ማን? ምን? ለምን? እንዴት? መቼ? የት? የሚሉትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም አምስት አምስት መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ምሣሌ፡- በትምህርትቤታችን የተሠራውን ቧንቧ ማን ሠበረው?

ንፁህ የመጠጥ ውኃ እንዴት ሊገኝ ይችላል?

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

በሠንጠረዡ ውስጥ ተነጣጥለውና ተጣምረው የተሰጧችሁን ቃላት አንብቧቸው።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ጠግር-ነት-ና | ጠግርነትና |
| ለ | አይ-ታሰብ-ም | አይታሰብም |
| ሐ | ከ-ሀ-ይ-ድ-ሮ-ጅ-ን-ና | ከሀይድሮጅንና |
| መ | የ-ተ-ለወጠ-ው | የተለወጠው |
| ሠ | ከ-ኦ-ክ-ስ-ጂ-ን | ከኦክስጂን |
| ረ | ተ-ሃዋሲ-ያን | ተሃዋስያን |

## ማንበብ

### የውኃ አጠቃቀም

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተለውን የቅድመንባብ ጥያቄ የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ?

ውኃ ለመጠጥ አገልግሎት ከመዋሉ በፊት በምን ዘዴ ሊጣራ ይችላል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የውኃ አጠቃቀም» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ዝርዝር ሀሳቦችን ከዋና ሀሳቦች ለይታችሁ በመረዳት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የውኃ አጠቃቀም

ውኃ፣ የፈሳሽነት፣ የጠጣርነትና የጋዝነት ባህርይ ያለው ውሁድ ነው። ይህ ከሀይድሮጅንና ከኦክስጅን የሚገኘው ውሁድ ውኃ፣ ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ይጠቅማል። ሕይወት ያለውኃ አይታሰብም። በመሆኑም የሕይወት ዋልታ የሆነውን ውኃ በቁጠባና በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል።

ውኃ፣ የውኃ አካላት ከሆኑት፣ ከወንዝ ፣ ከሐይቅ፣ ከባህር፣ ከውቅያኖስና ከመሳሰሉት በፀሐይ የሙቀት ኃይል ወደእንፋሎትነት ይለወጣል። ይህ ከፈሳሽነት ወደእንፋሎትነት የተለወጠው ውኃ በአየር ውስጥ ወደውኃ ጠብታዎች ይቀየራል። ጠብታዎቹ ተሰባስበው ዳመናን ይፈጥራሉ። ዳመናው ደግሞ ዝናብ ሆኖ ወደመሬት ይወርዳል። ተመራማሪዎች፣ የውኃ ወደላይ ወጥቶ የመመለስን ሂደት፣ የውኃ ዑደት በማለት ይጠሩታል።

> **ውኃ፤ በውኃ አስተዳደር ካልተመራ ይባክናል፤ እጥረት ያጋጥማል።**

### ውኃን ማጣራት


ውኃን ለመጠጥ አገልግሎት ለማዋል፣ ከፍተኛ ድካምና ወጭን ይጠይቃል። ውኃን እንዲሁ ሲያዩት ንፁህ ይመስላል። ይሁንእንጂ በውስጡ በዓይን የማይታዩ በሽታ አምጪ ተሃዋስያን ሊኖሩበት ይችላሉ። ስለዚህ ውኃን ለመጠጥ አገልግሎት ለማዋል ማጣራት ያስፈልጋል። ለዚህም በመጀመሪያ ከዝናብና ከወንዝ የሚገኘውን ውኃ በመገደብ ማጠራቀም ይገባል። ውኃውን በአሸዋ አማካይነት ማጣራት ቀጣዩ ተግባር ይሆናል። በመቀጠልም ውኃው ከጎጂ ተሃዋስያን እንዲፀዳ ክሎሪን መጨመር ይኖርበታል። ከዚያም ውኃው ከማጣሪያ ጣቢያው ተነስቶ ወደሚፈለግበት ቦታ እንዲደርስ የግፊት መስጫ መሣሪያ ያስፈልጋል። በግፊት ሰጪ መሣሪያው አማካይነት ውኃ በማጠራቀሚያ ጋን ውስጥ ይጠራቀማል። በመጨረሻም ለምግብነት የሚውለው የተጣራ ውኃ በቧንቧ አማካይነት ለኗሪዎች ይሠራጫል።

> **ውኃን ለመጠጥ አገልግሎት ለማዋል፤ ከፍተኛ ድካምና ወጪን ይጠይቃል።**

### ውኃን ማከፋፈል

ውኃን በግድብ አጠራቅሞ ማቆየት፣ ማጣራትና ማሠራጨት ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል። ለምሣሌ፣ አንድ ሜትር ኩብ ውኃ ለማምረት በአማካይ ብር 2.50

ይፈጃል። በተጨማሪም በውኃ ማከፋፍያ ጣቢያዎች ለሚሠሩ፣ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ገንዘብ ይከፈላል። ስለሆነም በከፍተኛ ወጪ ተጣርቶ የሚመጣን ውኃ ሳያባክኑ በቁጠባ መጠቀም ተገቢ ነው።




ውኃ ሊያልቅ የሚችል የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ የአጠቃቀም ሥርዓትን ማስተካከል ይገባል። አንድ የሚያንጠባጥብ የውኃ ቧንቧ በጊዜ ርዝማኔ ከፍተኛ የውኃ ብክነት ያመጣል። ይህ ክስተት ደግሞ ላልተፈለገ ወጪ ይዳርጋል። ከዚህ በተጨማሪ ለተለያዩ በሽታ አምጪ ተሃዋስያን መራባት ምክንያት ይሆናል። ስለሆነም ከቤት ውስጥ አገልግሎት አንስቶ ከፍተኛ የውኃ ፍጆታን እስከሚጠይቅ ተግባር ድረስ፣ ውኃን በቁጠባና በጥንቃቄ መጠቀም ያስፈልጋል።

(የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ። 2004። *አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ 6ኛ ክፍል።* መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሀሰት» በማለት ምክንያት እያቀረባችሁ በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ተመራማሪዎች የውኃ ወደላይ ወጥቶ የመመለስን ሂደት የውኃ ትነት ይሉታል።

ለ. በውኃ ውስጥ የበሽታ አምጭ ተሃዋስያን መኖር አለመኖራቸውን በአይን አይተን ማረጋገጥ እንችላለን።

ሐ. ውኃ ሊያልቅ የሚችል የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ በአግባቡ መጠቀም አለብን።

መ. አንድ የሚያንጠባጥብ የውኃ ቧንቧ ለተለያዩ በሽታ አምጪ ተሃዋስያን መራባት ምክንያት ይሆናል።

## ተግባር 2

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በተስማሚው ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

ሀ. ውኃ የሀይድሮጂንና የኦክስጂን ________ ነው።

ለ. ከፈሳሽነት ወደእንፋሎትነት የተለወጠ ውኃ በአየር ውስጥ ወደ ________ ይቀየራል።

ሐ. ከዝናብና ከወንዝ የሚገኝ የደፈረሰ ውኃ በመጀመሪያ የሚጣራው በ ________ አማካይነት ነው።

መ. ለመጠጥነት የሚውል ውኃ ከጎጂ ተሃዋስያን እንዲፀዳ _____ ይጨመርበታል።

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

## ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በዐውድ ልዩነት የተለያየ ፍቺ እንዲኖራቸው አድርጋችሁ ቢያንስ ሁለት ሁለት ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ምሣሌ፡- አየር

- በኃይል ስለሮጡ <u>አየር</u> አጠራቸው። (ትንፋሽ)
- በኢትዮጵያ <u>አየር</u> ማረፊያ ካላቸው ከተሞች አንዱ ባሕርዳር ነው። (አውሮፕላን)

ሀ. ጉድጓድ

ለ. ባህር

ሐ. መገደብ

መ. ማጣራት

ሠ. ጠጣርነት

ረ. ብክነት

ሰ. ማዋል

ሸ. ዋልታ

ቀ. መጠቀም

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና ዝርዝር ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር

«የውኃ አጠቃቀም» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ከ2ኛውና ከ3ኛው አንቀጽ የተገነዘባችሁትን በዋናና ዝርዝር የአጻጻፍ ስልት በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ ፊደል ሳትገድፉ እንዲሁም ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በትክክል ጻፉ።

# 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የውኃ አጠቃቀም

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

በጥሩ አገላለጽ ለማንበብ የምትጠቀሙባቸው ጠቃሚ ብልሀቶች ወይም ስልቶች ምን ምን ናቸው?

### ማንበብ

#### ተግባር

«የውኃ አጠቀቀም» ከሚለው ምንባብ 3ኛውንና 4ኛውን አንቀጽ በጥሩ አገላለጽና በተሻለ ፍጥነት ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

#### ተግባር

በአካባቢያችሁ ያሉትን የውኃ አካላት በመጥቀስ ህብረተሰቡ እንዴት እየተገለገለባቸው እንደሆነ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች

**ተግባር**

ቀጥሎ በሠንጠረዡ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች አዎንታዊ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ ዓረፍተገሮች መሆናቸውን ይህን (✓) ምልክት በመጠቀም ለዩ።

| ዓረፍተነገር | | ዓይነት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዎንታዊ | አሉታዊ | መጠይቃዊ |
| ሀ | በጌጣጌጥ ንግድ ለምን ያህል ጊዜ ሠራችሁ? | | | |
| ለ | ሥራችንን በአግባቡ ለመሥራት በዕቅድ መመራት አለብን። | | | |
| ሐ | በአንድአንድ ቤተሰብ ሕፃናትን መንከባከብ አልተለመደም። | | | |
| መ | ወጣቶች ቅርሶችን የመንከባከብና የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው። | | | |
| ሠ | ሰፊ ይዘት ያለውን አንድ ጽሑፍ አሳጥሮ ለመጻፍ የሚቻለው እንዴት ነው? | | | |
| ረ | በሀገራችን የሰንደቅዓላማ ቀን በብሔራዊ ደረጃ ይከበራል። | | | |
| ሰ | በቃል ውስጥ የፊደሎች ጠብቆና ላልቶ መነበብ የፍቺ ለውጥ የሚያመጣው ለምንድን ነው? | | | |
| ሸ | ሁለት የተለያየ ፍቺ ያላቸው ቃላት በአንድ ላይ አጣምሬ አንድ ትርጉም ያለው ቃል አልመሠርትም። | | | |
| ቀ | በትኩረት በማነብበት ጊዜ ሲያወሩኝ አልወድም። | | | |
| በ | በምታነቡበት ጊዜ መንቀሳቀስ የሚገባው የትኛው የአካል ክፍላችሁ ነው? | | | |



# ማህበራዊ ግንኙነት

ምዕራፍ 6

## እርስበርስ መተዋወቅ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ይንቆረቆር-ኣል | ይንቆረቆራል |
| ለ | ዝክረ-በዓል | ዝክረበዓል |
| ሐ | እየ-ተርገፈገፍ-ኩ | እየተርገፈገፍኩ |
| መ | ሰር-ፕራይዝ | ሰርፕራይዝ |
| ሠ | እንደ-ኣል-ተሳሳት-ኩ | እንዳልተሳሳትኩ |
| ረ | ከ-ጨርቅ-ኣ-ጨርቅ | ከጨርቃጨርቅ |
| ሰ | የ-ኣል-ደወልክ-ኸው | ያልደወልከው |

## ማንበብ

## ከሞት ጋር ድርድር

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

«ከሞት ጋር ድርድር» በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«ከሞት ጋር ድርድር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የአንዱን ገጸባህርይ ንግግር ካነበባችሁ በኋላ የሌላው ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ከሞት ጋር ድርድር

ድርድሩ የሚካሄደው በተሻለ መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው። ግድግዳው በአንድ አቅጣጫ ከጥግ እስከጥግ በመጋረጃ ተከልሏል። በሌላኛው አቅጣጫ ሥዕሎች ይታያሉ። ትልቅ አልጋና የምግብ ጠረጴዛ ፊት ለፊት አለ። መጋረጃው ሲገለጥ ለስለስ ያለ ሙዚቃ ይንቆረቆራል። መላጣውና ቦርጫሙ፣ የ57 ዓመቱ ተሻለ አልጋው ላይ ተጋድሞ ጋዜጣ ያነባል። እኩለ ሌሊት አካባቢ ነው። ድንገት ኮሽታ ይሰማል። ተሻለ ከመቅፀበት ከተኛበት ተነስቶ ቁጭ አለና ጆሮውን አንቅቶ ወደመስኮቱ ተመለከተ።

ተሻለ፡- «ምንድን ነው የማየው?» (ጥቁር ኮፍያ ያደረገ አስፈሪ ፍጡር ይታያል)

ሞት፡- «አይ! አንገቴ ተሰብሮ ነበር ኮ!»

ተሻለ፡- «አንተ ማን ነህ?» (ግራ በመጋባት እያየው)

ሞት፡- «ሞት ነኝ።»

ተሻለ፡- «ማ...ን?»

ሞት፡- «ሞት ነኝ። ስማኝ ይልቅ... ትንሽ ቁጭ ልበል? አንገቴን ልሰብረው ነበር ኮ! እንደቅጠል እየተርገፈገፍኩ ነው የወረድኩት።»

ተሻለ፡- «ማነህ ግን አንተ?» (ግራ እንደተጋባ)

ሞት፡- «ሞት ነኝ አልኩህ እኮ! እስቲ ውኃ አጠጣኝ?»

ተሻለ፡- «ሞት ነኝ? ምን ማለት ነው ሞት ነኝ ማለት?»

ሞት፡- «ያምሃል እንዴ? ጥቁር ልብስና ነጭ ፊት አይታይህም?»

ተሻለ፡- «ይታየኛል።»

ሞት፦ «ቆይ ዛሬ የቅዱሳን ዝክረበዓል ነው እንዴ?»

ተሻለ፦ «ኧረ አይደለም።»

ሞት፦ «ስለዚህ ሞት ነኝ ማለት ነው። እሺ አሁንስ ውኃውን አትሰጠኝም? ለስላሳም ቢሆን ግድ የለም።»

ተሻለ፦ «እየቀለድክ ነው አይደል?»

ሞት፦ «የምን ቀልድ ነው? ዕድሜህ ሃምሳ ሰባት፣ ስምህ ተሻለ፣ የቤት ቁጥርህ አንድ መቶ አሥራ ስምንት አይደል? መቼም እንዳልተሳሳትኩ እርግጠኛ ነኝ ... የታለ ያ የመጥሪያ ወረቀት?» (ኪሱን እየዳበሰ)

ተሻለ፦ «እሺ ከእኔ ምንድን ነው የምትፈልገው?»

ሞት፦ «ምን የምፈልግ ይመስልሃል?» (በመሰልቸት ስሜት)

ተሻለ፦ «አትቀልድ ሰውዬ እኔ ፍፁም ጤናማ ሰው ነኝ።»

ሞት፦ «ምን ታደርገዋለህ እንግዲህ። በጣም ደስ የሚል ቤት አለህ። ራስህ ነህ ያበጃጀኸው?»

ተሻለ፦ «አይ! ለባለሙያ ከፍለን ነው ያሠራነው፤ ግን አግዘናታል።»

ሞት፦ «ትልልቅ ዓይኖች ያሏቸው ሕጻናት እንዴት እንደምወድ...» (ግድግዳው ላይ ያለውን ሥዕል እያየ)

ተሻለ፦ «እኔ ግን አሁን መሄድ አልፈልግም፤ ገና ነኝ።»

ሞት፦ «መሄድ አልፈልግም? በናትህ ክርክር እንዳትጀምረኝ። መውጣት መውረዱ ራሴን እንዴት እንዳዞረኝ አልነግርህም!»

ተሻለ፦ «የምን መውጣት መውረድ?»

ሞት፦ «በቃ! አሁን እሱን ተውና ይልቅ ተነሳና እንሂድ!»

ተሻለ፦ «እያነበብኩ ነበር ...»

ሞት፡- «በጣም ተመስጠህ ነበር ማለት ነው።» (ተሻለ የሚያነበውን ጋዜጣ እየተመለከተ)

ተሻለ፡- «ገና አንብቤ አልጨረስኩም።»

ሞት፡- «እንዴት ብዬ እንደምነግርህ አላውቅም፤ ጓደኛዬ አንተኮ...»

ተሻለ፡-«ቆይ ለምንድን ነው በሥነሥርዓት የበሩን ደወል ያልደወልከው? በህገወጥ መንገድ መግባቱ ለምን አስፈለገ?»

ሞት፡- «ሰርፕራይዝ ላደርግህ ፈልጌ ነዋ!»

ተሻለ፡- «ስማ ሰውዬ! በጣም መሸቶብሃል!»

ሞት፡- «ልክ ነህ። ተነስ እንሂድ?»

ተሻለ፡- «የትነው የምንሄደው?»

ሞት፡- «ወደሞት ነዋ! እዚያ ... ወንዞቹ ወተት፣ ድንጋዮቹ ዳቦ ወደሆኑበት። ታውቃለህ?»

ተሻለ፡- «እኔ ትንሽ ጊዜ መቆየት እፈልጋለሁ። አሁን ለመሄድ ዝግጁ አይደለሁም።»

ሞት፡- «በጣም አዝናለሁ። ምንም ልረዳህ አልችልም። በቃ ጊዜህ ደርሷል።»

ተሻለ፡- «እንዴት ነው ጊዜው የደረሰው? ገና አሁን አይደል ከጨርቃጨርቅ አምራች ድርጅቶች ጋር ሽርክና የገባሁት?»

ሞት፡- «አሁን ትርፍ ገንዘብ መጣ! ቀረ! ምን ለውጥ አለው ብለህ ነው?»

ተሻለ፡- «አንተን ይመስልሃል?»

ሞት፡- «አሁን እሺ ትሄዳለህ አትሄድም?»

ተሻለ፡- «በጣም አዝናለሁ፤ ሞት ለመሆንህ አምኜ ለመቀበል አቅቶኛል።» (በአትኩሮት እያየው)

ሞት፡- «ምን? ማንን ጠብቀህ ነበር ...»

ተሻለ፡- «አይ! እንደዚያ አይደለም።»

ሞት፡- «ያልጠበቅሽው ዓይነት ሞት ከሆንኩብህ ይቅርታ።»

ተሻለ፡- «ለምን እንደሆነ አላውቅም፤ ሁልጊዜ በሀሳቤ … ረጅም ሆነህ ነበር የምትታየኝ …»

ሞት፡- «ሜትር ከሰባ ነኝ። ከክብደቴ ጋር ተመጣጣኝ ነው።»

ተሻለ፡- «እኔን ትመስላለህ ልበል?»

ሞት፡- «እና ማንን ልምሰል? ያንተ ሞት ነኝኮ!»

ተሻለ፡- «እሺ በቃ ትንሽ ጊዜ ስጠኝ። የአንድ ቀን ጊዜ እፈልጋለሁ።»

ሞት፡- «እሺ እንድልህ ነው? አልችልም።»

ተሻለ፡- «አንድ ተጨማሪ ቀን። ሃያ አራት ሰዓት ብቻ!»

ሞት፡- «ምን ትሰራበታለህ? ሬዲዮ ነገ ዝናባማ ቀን እንደሚሆን ተናግሯል።»

ተሻለ፡- «ቆይ ቼዝ ትችላለህ?»

ሞት፡- «አይ! አልችልም።»

ተሻለ፡- «ፎቶ ላይ ግን ቼዝ ስትጫወት ያየሁህ መሰለኝ።

ሞት፡- «ተሳስተሀል። እኔ ቼዝ መጫወት አልችልም። ባይሆን ካርታ ጨዋታ እችላለሁ።»

ተሻለ፡- «ካርታ ትችላለህ?»

ሞት፡- «መጠየቁስ!»

ተሻለ፡- «በደንብ ትችላለህ?»

ሞት፡- «አሳምሬ!»

ተሻለ፡- «ምን ለማድረግ እንዳሰብኩ ልንገርህ …»

ሞት፡- «ከእኔ ጋር ምንም ዓይነት ድርድር ለማድረግ ግን እንዳታስብ!»

ተሻለ፡- «ካርታ እንጫወትና አንተ ካሸነፍክ ወዲያውኑ ተነስተን እንሄዳለን። እኔ ካሸነፍኩ ግን ትንሽ ጊዜ ትሰጠኛለህ። የአንድ ቀን ጊዜ።»

ሞት፡- «እስኪ አሁን በየትኛው ጊዜ ነው ካርታ የምንጫወተው?»

ተሻለ፡- «ግድ የለህም። በደንብ የምትችል ከሆነ እንጫወት?»

ሞት፡- «ግን በአንድ ጨዋታ ...»

ተሻለ፡- «ለግማሽ ሰዓት ያህል እንጫወት። ፈታ በል።»

ሞት፡- «ግድ የለህም ይቅርብኝ።»

ተሻለ፡- «ይሄው ካርታው ... ለምን አንጫወትም?»

ሞት፡- «እሺ ይሁን ... ትንሽ እንጫወትና ... ለነገሩ እኔንም ዘና ያደርገኛል።»

ተሻለ፡- «በል ሳብ ...» (እየሳበ እያለ በእጁ ያሉትን ካርታዎች እያየ)

ሞት፡- «ተሳሳትሁ! አይ ...» (ከዚህ ቀጥሎ ብዙ ካርታ ያነሳሉ፤ ይጥላሉ)

ተሻለ፡- «አዎ! በቃ ... ተሸንፈሃል።»

ሞት፡- «አይ! ያችን ዘጠኝ ቁጥር መጣል አልነበረብኝም።» (ካርታዎችን ተስፋ በመቁረጥ እየተመለከተ)

ተሻለ፡- «በቃ ነገ እንገናኝ!»

ሞት፡- «ነገ እንገናኝ! የምርህን ነበር እንዴ?»

ተሻለ፡- «ተስማምተን እኮ ነበር የተጫወትነው»

ሞት፡- «አዎ! ግን ... ሃያ አራት ሰዓት የት እቆያለሁ?»

(ከአዲስ አድማስ ድረገጽ። ሚያዝያ 26/2006። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

> **ማስታወሻ**
>
> ገፀባህርያት፦ በልቦለድ ወይም በተውኔት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ባለታሪኮች ናቸው።
>
> መቼት፦ በልቦለድ ወይም በተውኔት ጽሑፍ ውስጥ ታሪኩ የሚፈጸምበት ሥፍራና ጊዜ ነው።
>
> ግጭት፦ በልቦለድ ወይም በተውኔት ውስጥ ያሉ ገፀባህርያት በታሪኩ ሂደት ከሌሎች ገፀባህርያት ወይም ከተፈጥሮ ጋር የሚፈጥሩት ፍትጊያ ነው።
>
> ጭብጥ፦ በልቦለድ ወይም በተውኔት ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው ፍሬ ነገር ማለት ነው።

### ተግባር 1

ምንባቡን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በትክክል አሟሉ።

| መቼት | ገፀባህርያት | የክርክር ዕድገት ከየት ወደየት | የግጭቱ ማዕከላዊ ነጥብ | የተደረሰበት ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

### ተግባር 2

«ከሞት ጋር ድርድር» በሚል ርዕስ የቀረበውን የምንባብ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ላልተውና ጠብቀው የሚነበቡ ፊደላት ያሏቸው ቃላት ፍቺ

### ተግባር

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በፊደላት ጠብቆና ላልቶ መነበብ ምክንያት ያላቸውን የፍቺ ልዩነት ዓረፍተነገር በመሥራት አሳዩ።

ምሣሌ፦ አለ ⟶ ተናገረ («ለ» ሲላላ) ልጁ ወደትምህርትቤት አልሄድም <u>አለ</u>።

አለ——> ተገኘ፣ ኖረ፣ («ለ» ሲጠብቅ) ሰውዬው እቤት <u>አለ</u>።

ሀ ድርድሩ
መ ፈታ
ሰ. ያሏቸው
በ. ያለውን
ለ. መላ
ሠ. ልብስ
ሸ. ሰባ
ሐ. ያነባል
ረ. አግዘናል
ቀ. ልረዳህ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምልልስ የተዋቀረ ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

«ከሞት ጋር ድርድር» የሚለውን ምንባብ ምሳሌ በማድረግ መምህራችሁ በሚጀምሩላችሁ መነሻ ሀሳብ ተጠቅማችሁ የገፀባህርያት ምልልስ ያለበት አንድ ገጽ ጽሑፍ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

#### ተግባር

ቀጥሎ የገፀባህርያትን ምልልስ የያዘ ጽሑፍ ቀርቦላችኋል። በጽሑፉ ውስጥ የተጓደሉ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታ በመጠቀም በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

**አበራና** ቀለሙ የትምህርት ቤት ጓደኛሞች ናቸው። አንድ ቀን በጧት ወደትምህርትቤት ሲሄዱ ተገናኙ።

**አበራ** እንደምን አደርክ ቀለሙ?

**ቀለሙ** ደህና፣ ደህና፣ አንተስ እንዴት ነህ?

**አበራ** በጣም ደህና ነኝ ቀለሙ። ትናንት የሂሣብ መምህራችን የሰጡንን የቤትሥራ ሠራህ?

**ቀለሙ** አዎ ሠርቻለሁ። ነገርግን ሁለተኛውን ጥያቄ በትክክል የሠራሁት አልመሰለኝም።

**አበራ** እሺ! አስቸገረህ ማለት ነው? መምህራችንም፣ ሁለተኛው ጥያቄ ጠጠር ይልባችኋል ብለው ነግረውን ነበር'ኮ።

**ቀለሙ** አሀ! ብለውን ነበር እንዴ?

አበራ አዎ ብለውን ነበር። እኔ በትክክል ስለሠራሁት አስረዳሃለሁ። (በጥሩ ሁኔታ ያስረዳዋል)

ቀለሙ አመሰግናለሁ አበራ።

አበራ በል ወደክፍላችን እንግባ (እጅ ለእጅ ተያይዘው ይገባሉ)

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ከሞት ጋር ድርድር

**ቅድመንባብ**

**ተግባር**

«ከሞት ጋር ድርድር» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሷቸውን ምልልሶች የገጸባህርያቱን ድምፀት አስመስላችሁ ተናገሩ።

**ማንበብ**

**ተግባር**

«ከሞት ጋር ድርድር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## ማዳመጥ

### «የስኬታማ ሰዎች የልምድ ልውውጥ»

**ቅድመማዳመጥ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ**

**ተግባር**

ለሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. የልምድ ልውውጥ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ከሥዕሉ የተረዳችሁትን ተናገሩ።




## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

መምህራችሁ «የስኬታማ ሰዎች የልምድ ልውውጥ» በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ያነቡላችኋል፤ እናንተ ደግሞ በሰዎች መካከል ያለውን የሀሳብ ልውውጥ በመረዳት አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስማቸውን ለውጤታማነት ያበቁት ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከልድያና ከስማቸው ልምዱን በተገቢ ሁኔታ ያካፈለ ማን ይመስላችኋል? ለምን?

ሐ. ካዳመጣችሁት ነገር ምን ትምህርት አገኛችሁ?

መ. ሊድያ የቀድሞ ሥራዋን ማስታወስ የማትፈልገው ለምንድን ነው?

## ሰዋስው

### ድርብ ዓረፍተነገርን መመሥረት

ማስታወሻ

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በአያያዦች አማካይነት በማጣመር ሌሎች ድርብ ዓረፍተነገሮችን መመሥረት ይቻላል።

ምሣሌ፡-

የሂሣብ ትምህርት እወዳለሁ። (ነጠላ ዓረፍተነገር)

ጥሩ ውጤት አላመጣሁም። (ነጠላ ዓርፍተነገር)

የሂሣብ ትምህርት እወዳለሁ፤ ይሁን እንጂ ጥሩ ውጤት አላመጣሁም።

በምሣሌው መሠረት «ይሁን እንጂ» የሚለው አያያዥ ሁለቱን ነጠላ ዓረፍተነገሮች በማያያዝ ሌላ ድርብ ዓርፍተነገር ለመመስረት አስችሏል።

## ተግባር

ቀጥሎ በሠንጠረዡ ግራና ቀኝ የቀረቡትን ነጠላ ዓረፍተነገሮች ተገቢውን አያያዥ በመጠቀም ድርብ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

| ነጠላ ዓረፍተነገር | አያያዥ | ነጠላ ዓረፍተነገር |
|---|---|---|
| 1. ቦርሳዬን አስቀመጥኩ። | ይሁን እንጂ | ሀ. ብዙ ማዳመጥ እችላለሁ። |
| 2. ቁርስ አልበላሁም። | እና | ለ. እኔን አታገኘኝም። |
| 3. ሩቅ ቦታ ሄጃለሁ። | ስለዚህ | ሐ. እሱ አይወደኝም። |
| 4. ብዙ መናገር አልወድም። | ግን | መ. የርሃብ ስሜት አልተሰማኝም። |
| 5. በሥራ ቦታ አልነበርኩም። | ነገርግን | ሠ. ምን እንደሰራህ ሪፖርቱ ደርሶኛል። |
| 6. ታታሪነቴን አልጠላውም። | እንጂ | ረ. እንደሥራዬ ውጤታማ አይደለሁም። |
| 7. ወንድሜን እወደዋለሁ። | | ሰ. ኳስ መጫወት ጀመርኩ። |
| 8. የክፍል ጓደኞቼን እወዳቸዋለሁ። | | ሸ. በየቀኑ ባያቸው ደስ ይለኛል። |

# ማንበብ

## በላ ልበልሃ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሄ የሚያገኙት እንዴት ነው?


ለ. በሥዕሉና «በላ ልበልሃ» በሚለው ርዕስ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«በላ ልበልሃ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የሚፈጠረውን ስሜትና የአካል እንቅስቃሴ በአዕምሯችሁ ምሥል እየፈጠራችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

# በላ ልበልሃ



በኢትዮጵያ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ከመቋቋማቸው በፊት ዳኝነት ከሚሰጥባቸው ሥርዓቶች አንዱ ባህላዊ የሙግት ሥርዓት ነበር። ባህላዊ ሙግት በተረትና ምሣሌ እንዲሁም በግጥም ይካሄድ ነበር። የሀገር ሽማግሌዎችና ዳኞች፣ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በሰዎች መካከል የሚፈጠሩትን የእርስበርስ ግጭቶች ከሚፈቱባቸው ዘዴዎች አንዱ ይህ የሙግት ሥርዓት ነበር።

አንድ ወቅት አንድ በሬ የጠፋበት አርሶአደር በፍለጋ ረጅም ጊዜ ቢያሳልፍም የጠፋበትን በሬ ማግኘት አልቻለም። በሁኔታው ቢበሳጭም ጉዳዩን ዝም ብሎ አልተወውም። ከረጅም የፍለጋ ጊዜ በኋላ ጥቃቅን ፍንጮችን ማግኘት ጀመረ። ያገኛቸው ፍንጮች ጣቱን ከሰፈሩ ኗሪዎች መካከል ወደአንድ ሰው እንዲቀሥር አደረጉት። እናም ሰውዬውን ሊሞግተው አደባባይ አቆመው። ሙግቱም እንደሚከተለው ነበር።

ከሳሽ፦ ያጤ ሥርዓቱን የመሠረቱን፣
አልናገርም ሀሰት ሀሰቱን፣
ሁሌ እናገራለሁ እውነት እውነቱን።
መጣሁ እንደውኃ ስፈስ፣
እንደ.ጋግ ስነፍስ፣
በቅሎዬ ሲጋሪ፣
ሚስቴ ነጭ ጋጋሪ።

ለወታደር የለው ምሣ፣
ለቀበሮ የላት ገሣ።
በሬዬ ጠፍቶ ከደጋ፣
ስከተል መጣሁ በደም ፍለጋ፣
ብደርስ በፍለጋ ከደጅህ፣
ሙዳ ሥጋ ይዟል ልጅህ፣
ስለዚህ በሬዬን ትከፍላለህ በግድህ!

በማለት የጠነከረ የመከራከሪያ ሀሳብ ሰጠ። ከዚያም ታዳሚዎችና ፍርድ ሰጪዎች የተከሳሹን መልስ ለመስማት አቆበቆቡ።

ተከሳሽ፦ ፍየል መንታ ትወልዳለች፣
አንዱን ለመጣፍ አንዱን ለወናፍ ፣
መጣፉ እኔ ወናፍ አንተ፣
እንደውኃ ብትፈስ በቦይ ትመለስ፣
እንደ.ጋግ ብትነፍስ አጭዶ ለፈረስ ፣
ሚስትህ ነጭ ብትጋግር አንድ እንግዳ አታሳድር፣
በቅሎህ ብትሰግር እመሸበት ታድር።

እንዴት ለወታደር የለውም ምሣ፣
ራት ጋግሮ ለራት ለምሣ፣
እንዴት ለቀበሮ የላት ገሣ፣
ትገባለች አርባ ክንድ ምሣ።

በሬህ ቢጠፋ ከደጋ፣
አንተም ብትመጣ በደም ፍለጋ፣
ከደጄ ቢገኝ ሙዳ ሥጋ።

ከቤቴ በላይ አለ ተራራ፣
መዘዋዋሪያው የጅብ ያሞራ።
ከቤቴ በላይ ዛፍ አለ፣
ከዛፉም በታች መንገድ አለ፣
መንገዱም ላይ ጅብ ይሄዳል፣
በዛፉም ላይ አሞራ ያርፋል።
አሞራና ጅብ ሲጣለፉ፣
ሙዳ ሥጋ በተፉ።
ነፍስ ያላወቀ ልጅ ቢያነሳ፣
አያስከፍለኝም ነገርህን አንሳ!

በማለት ተከሳሽ የጠነከረ ምላሽ ይሰጣል። ከዚያም ተሟጋቾቹ በግል ሲከራከሩ፣ ከየአካባቢ የታደሙ ሰዎች በክርክሩ መሀል «እውነት ነው!» በደንብ አድርገህ ንገረው!ይገባዋል!» በማለት ደጋፊ ሀሳብ ይሰጣሉ፤ አጋርነታቸውንም ይገልጻሉ። ከዚህ በኋላ ክርክሩን ራሳቸው ስላጠዙት ፍርድ ሰጭ ዳኞች

«ስጋ ስጋን በልተሻል
ሙግትሽ ግን ያዋጣሻል።»

በማለት ተከሳሹን ከቀረበበት ክስ ነፃ በማድረግ ፍርድ ሰጥተው አሰናበቱት።

(ሽበሺ ለማ። 1985። *ተጠየቅ*። ገጽ 107-108 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የ «በላ ልበልሃ» ምንባብን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ያለውን ሠንጠረዥ በተገቢ ፍሬ ነገሮች አሟሉ።

**መቼት**

- ቦታው፦ በአንድ የገጠር አካባቢ
- ጊዜው፦

**ዋና ገፀባህርያት**

**ግጭት**

**መዋቅር**

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| | |

**መፍትሄው ምን ሆነ?**

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «በላ ልበልሃ» በሚለው ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

1. ከሳሽ፣ «መጣሁ እንደውኃ ስፈስ፣
   እንደጋገር ስነፈስ፣» ሲል ከሳሹ ስለራሱ ምን መግለጹ ነው?
2. «እንዴት ለቀበሮ የላት ገሣ፣
   ትገባለች አርባ ክንድ ምሣ» ብሎ ተከሳሽ ሲመልስ ምን ማለቱ ነው?
3. ተከሳሽ፣ «ፍየል መንታ ትወልዳለች፣
   አንዱን ለመጣፍ አንዱን ለወናፍ፣
   መጣፉ እኔ ወናፍ አንተ» ሲል ከሳሹን ምን እያለው ነው?

# 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

ለሚከተሉት ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ምሣሌ፦ ሰጋሪ፦ በአረማመድ ጋላቢውን የማይነቀንቅ፤ የሠለጠነች በቅሎ አረማመድ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ገሣ | ሙዳ | ሥርዓት | ጋሻ | |
| ወናፍ | ሞገተ | ነፍጭ | አቆበቆቡ | አንሳ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምልልስ የተዋቀረ ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

«ደብድበኸኛል፤ አልደበደብኩህም» በሚል ርዕስ በከሳሽና በተከሳሽ ክርክር ላይ የተመሠረተ «የበላ ልበልሃ» ዓይነት ግጥም ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን የምልልስ ምንባብ አዳምጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችንና ፊደላትን በትክክል በመጠቀም ጻፉ።

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**በላ ልበልሃ**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ2ኛ ሳምንት፣ በ4ኛ ቀን «በላ ልበልሃ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ስለገፀባህርያቱ (ባለታሪኮች) መከራከሪያ ሀሳቦች የምታስታውሷቸውን ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

«በላ ልበልሃ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከሳሽና ተከሳሽ ሆናችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

### በምልልስ የተዋቀረ ንግግር

«በላ ልበልሃ» በሚለው ምንባብ መሠረት ከሳሽንና ተከሳሽን በመወከል የሚና ጨዋታ አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ድርብ ዓረፍተነገር መመሥረት

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም በምሣሌው መሠረት አምስት ድርብ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

| እና፣ ደግሞ፣ ግን፣ ነገርግን፣ እንጂ፣ ይሁንእንጂ፣ |
| --- |

ምሣሌ፡- በጧት ወደሥራ ገባሁ።

እስካሁን የሠራሁት ሥራ የለም።

በጧት ወደሥራ ልገባ እንጂ እስካሁን የሠራሁት ሥራ የለም።

# የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አጎልብተን-ኣል | አጎልብተናል |
| ለ | ተ-ወካይ-ነት-ህ | ተወካይነትህ |
| ሐ | ሀዘን-ተኛ-ው-ን | ሀዘንተኛውን |
| መ | ግንኙ-ነት-ኣችን | ግንኙነታችን |
| ሠ | ደንብ-ኣችን | ደንባችን |
| ረ | አቀርብ-ል-ሽ-ኣለሁ | አቀርብልሻለሁ |
| ሰ | አረጋዊ-ያን-ና | አረጋውያንና |

# ማንበብ

## እርስበርስ መረዳዳት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በሰዎች መካከል የሚደረገው የእርስበርስ መረዳዳት ምን ጠቀሜታ የሚያስገኝ ይመስላችኋል?

ለ. ከጓደኞቻችሁ ጋር እንዴት ትረዳዳላችሁ?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«እርስበርስ መረዳዳት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምልልሳዊ ምንባብ በቅድመንባብ ጥያቄዎች የሰጣችኋቸውን መልሶች እያረጋገጣችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### እርስበርስ መረዳዳት

ዕድር ማህበራዊና ምጣኔሀብታዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚቋቋም የመረዳጃ ማኀበር ነው። ሰዎች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በሀዘንና በሌሎች ችግሮች ጊዜ ለመረዳዳት ዕድር ይመሠርታሉ። ወይዘሮ ብርቱካንና አቶ በቀለ በአንድ አካባቢ ይኖራሉ፤ የሰፈራቸውም የዕድር አባል ናቸው። ዕለቱ እሁድ በመሆኑ ሁለቱም የዕድር ክፍያ ለመክፈል ሲሔዱ በመንገድ ላይ ተገናኝተው ስለዕድራቸው ይወያያሉ።

አቶ በቀለ፡- «ወ/ሮ ብርቱካን እንደምን አረፈድሽ? ምነው የመስቀል ወፍ ሆንሽ? አይቼሽ አላውቅም፤ ባገር አልነበርሽም?»

ወ/ሮ ብርቱካን፡- «ኧረ አለሁ። ሰሞኑን ትንሽ አሞኝ ስለነበር ከቤት ወጥቼ አላውቅም። አንተስ ደህና ነህ?»

አቶ በቀለ፡- «እኔስ ደህና ነኝ። መታመምሽን እኮ አልሰማሁም። ብሰማ ኖሮ እጠይቅሽ ነበር! ምን አሞሽ ነበር?»

ወ/ሮ ብርቱካን፡- «ያው የተለመደው ተነስቶብኝ ነው። ሥራ መሥራት ከለከለኝ ጠም አዳሪ አደረገኝ እኮ!»

አቶ በቀለ፡- «ነው እንዴ! አዲስ በሽታ መስሎኝ ነው» አይዞሽ! ሀኪም የሚያዝልሽን መድኃኒት ውሰጂ፤ ምግብም ተመገቢ።

ወ/ሮ ብርቱካን፡- «እሺ እወስዳለሁ። ብቻ እጅ አጠረኝ። እንዲያው ይሄ ዕድር ምናለ ትንሽ ገንዘብ ለሕክምና ቢያግዘኝ? ባለፈው ለተቸገሩ ብዙ ሰዎች ድጋፍ አደረገ ሲባል ሰምቻለሁ። ለእኔም ለምግብና ለሕክምና የሚሆን ትንሽ ገንዘብ ይተባበረኝ ይሆን?»

አቶ በቀለ፡- «አዎ! የተቸገሩ ሰዎችን ዕድራችን እየረዳ ነው። በቅርቡ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናትን፣ አረጋውያንና የተቸገሩ ሰዎችን ለይቶ በመመዝገብ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። አንቺም እኮ ተመዝግበሻል።»

ወ/ሮ ብርቱካን፦ «እኔስ መመዝገቤንም አላወቅሁም። እባክህ ከቻልክ በሰፈር ተወካይነትህ ኮሚቴዎችን አሳስብልኝና እኔም የተወሰነ ድጋፍ እንዳገኝ እርዳኝ።»

አቶ በቀለ፦ «እሺ! ያው ድጋፉ የሚሰጠው እንደችግሩ ክብደት ነው። የአንቺ ደግሞ የጤና ችግር ስለሆነ ድጋፉን ታገኛለሽ ብዬ እገምታለሁ። ለማንኛውም እኔም የአንቺን ጉዳይ አቀርብልሻለሁ። አይዞሽ በርታ በዪ!»

ወ/ሮ ብርቱካን፦ «ይበጅህ አቶ በቀለ! እኔማ ጧሪ ቀባሪ ልጅ የለኝ፤ አንድ ዕድሬን አምኜ አይደል የምኖር።»

አቶ በቀለ፦ «ለሁላችንም ቢሆን በችግር ጊዜ ለመረዳዳት ተስፋችን ዕድራችን እኮ ነው። በሀዘን ጊዜም ሆነ የከፋ ችግር ሲያጋጥም መረዳዳት የምንችልበት ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንባችን ላይ ሠፍሯል። ዕድር እኮ ለማህበራዊ ግንኙነታችን መሠረት በመሆኑ ለችግራችንም ጊዜ አለኝታችን ነው።»

ወ/ሮ ብርቱካን፦ «ልክ ነህ አቶ በቀለ። በዕድሩ ምክንያት ከብዙ ሰዎች ጋር ተዋውቄያለሁ። ብዙዎቹም እየረዱኝ ነው። ይህ ዕድር ባይኖር ምን ይውጠኝ ነበር?»

አቶ በቀለ፦ «ልክ ነሽ። በዕድሩ ምክንያት ጉርብትናን፣ መተባበርንና ፍቅርን አጎልብተናል። በተለይ በሀዘን ጊዜ ሀዘንተኛውን ለማፅናናት ከግል ይልቅ በጋራ መሆኑ በጣም ጥሩ ነው። ለማንኛውም አሁን እየደረስን ስለሆነ ያለሽን ችግር ለዕድሩ አባላት አንቺም እኔም እናቅርብና የሚሰጥሽን ድጋፍ በመቀበል ሕክምናሽን ትከታተያለሽ፤ አይዞሽ!»

ወ/ሮ ብርቱካን፦ «እሺ አቶ በቀለ! አመሰግናለሁ።»

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰዎች ዕድር የሚያቋቁሙት ለምንድን ነው?

ለ. ወይዘሮ ብርቱካን ከዕድሩ ዕርዳታ የሚያገኙ ይመስላችኋል? ለምን?


ሐ. የዕድር አባል መተዳደሪያ ደንብ ያወጡት ምን ሊያደርጉበት ነው?

መ. የዕድር አባላት መሆን የሚችሉት በአንድ ሠፈር የሚኖሩ ሰዎች ብቻ ናቸው? ለምን?

ሠ. በአካባቢያችሁ የተቋቋሙ ዕድሮች በምንባቡ ከተገነዘባችሁት ዕድር ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት አብራሩ።

## ተግባር 2

የአካባቢያችሁን ማኅበራዊ ግንኙነት መሠረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በትክክል አሟሉ።



# ቃላት

## ለቃላት ዐውዳዊና መዝገበ ቃላዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. የመስቀል ወፍ
ለ. ድጋፍ
ሐ. ተነስቶብኝ
መ. ምን ይውጠኝ
ሠ. ውሰጂ
ረ. እጅ አጠረኝ

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ከመዝገበቃላት በመፈለግ ጻፉ።

ሀ. ሕክምና
ለ. መሠረት
ሐ. ባልደረባ
መ. ተስፋ
ሠ. አረጋውያን
ረ. ዕድር
ሰ. ጉርብትና
ሸ. ጉዳይ

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## በምልልስ የተዋቀረ ድርሰት መጻፍ

### ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «የፈተና ሰሞን» በሚል ርዕስ በሁለት ገፀባሕርያት ምልልስ ላይ የተመሠረተ ድርሰት ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምልልስ እያዳመጣችሁ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታቸው በመጠቀም ጻፉ።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## እርስበርስ መረዳዳት

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«እርስበርስ» መረዳዳት በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሱትን ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«እርስበርስ መረዳዳት» የሚለውን ምንባብ የገፀባህርያቱን የድምፅ አወራረድ፣ የቃላት አጠቃቀምና የአካል እንቅስቃሴ ጠብቃችሁ አንብቡ።

# መናገር

### በምልልስ የተዋቀረ ንግግር

**ተግባር**

«እርስበርስ መረዳዳት» በሚል ርዕስ የቀረበውን የምልልስ ምንባብ ገፀባህርያቱን በመወከል የሚና ጨዋታ አቅርቡ።

# ሰዋስው

### ድርብ ዓረፍተነገር መመሥረት

**ተግባር**

የሚከተሉትን አያያዦች በመጠቀም ስድስት ድርብ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

| እና፣ ግን፣ እንጂ፣ ነገርግን፣ ስለዚህ፣ ይሁንእንጂ |
|---|



# ምዕራፍ 7

## ሱስ

### ማጨስና መቃም

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ማስታወቅ-ኢ-ያ-ዎች | ማስታወቂያዎች |
| ለ | ስለሚ-ያሳልፍ-ኡ-ት-ና | ስለሚያሳልፉትና |
| ሐ | ግንኙ-ነት-ኣቸው-ም | ግንኙነታቸውም |
| መ | ያባብስ-ብ-ኣቸው-ኣል | ያባብስባቸዋል |
| ሠ | በ-ተሃዋስ-ያን | በተሃዋስያን |
| ረ | ሄ-ፒ-ታ-ይ-ት-ስ | ሄፒታይትስ |

## ማንበብ

### ጫት መቃምና መዘዙ

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰዎች ጫት የሚቅሙት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ለ. ጫት መቃም ጉዳት የሚያስከትል ይመስሏችኋል? እንዴት?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ቀጥሎ «ጫት መቃምና መዘዙ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች በምክንያትና ውጤት ግንኙነት እያደራጃችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ጫት መቃምና መዘዙ

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የጫት ቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ ስለመምጣቱ በቀላሉ መገመት የሚቻል ይመስላል። በየቦታው የጫት ምርት ጨምሯል፤ የማከፋፈያና የመሸጫ ሱቆች በብዛት ተከፍተዋል፤ የጫት ማስታወቂያዎች በየቦታው ተለጥፈው ይታያሉ። እነዚህ ሁሉ ለጫት ተጠቃሚዎች ቁጥር መበራከት አመላካቾች ናቸው።

ጫት መቃም በጤና፣ በምጣኔሀብትና በማህበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። ጫት የሚቅሙ ሰዎች ለሱስ ይጋለጣሉ። ጤንነታቸው ይታወካል። የሥራ ጊዜያቸውን ጫት በመቃም ስለሚያሳልፉትና ገንዘባቸውንም ለጫት መግዣ ስለሚያውሉት ችግር ያጋጥማቸዋል። ማህበራዊ ግንኙነታቸውም የላላ ይሆናል። ጥሩ ሥነምግባር ቢኖራቸው እንኳ ማህበራዊ ተቀባይነት አይኖራቸውም፤ በዚህ የተነሳ ለብቸኝነት ይጋለጣሉ።

ጫት መቃም በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። ጫት መቃም በአዕምሮ ላይ ለአጭር ጊዜ የመነቃቃትና የደስታ ስሜቶችን ፈጥሮ እንደገና ወደድብርት፣ መረበሽና አለመረጋጋት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል። በሂደትም የሆድና የአንጀት ድርቀት ያስከትላል፤ የምግብ ፍላጎት እንዲቀንስ ያደርጋል። በተሃዋስያን ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳጣል። ለቲቢና ሄፒታይትስ ለመሳሰሉ በሽታዎች ያጋልጣል። የአፍ ጠረንን ይቀይራል፤ ጥርስን ያበላሻል። በተጨማሪም የልብ ምትንና የደም ግፊትን ይጨምራል። ሌሎችንም ተዛማጅ የጤና እክሎች ያስከትላል። የጫት መቃም መዘዝ ከራስ አልፎ ለልጅም ይተርፋል። ጫት ከሚቅሙ እናቶች የሚወለዱ ሕጻናት በቂ የጡት ወተት አያገኙም። በዚህ ምክንያት ዕድገታቸው ይቀጭጫል።

ጫት በሚቃምበት ጊዜ ከሱስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ነገሮችንም መጠቀም የተለመደ ነው። ለምሣሌ ስኳር መቃም፣ ስኳርነት ያላቸውን መጠጦች መጎንጨት፣ ሲጋራ ማጨስና ከተቃመ በኋላም አልኮል መጠጣት በዋናነት ይጠቀሳሉ። ስኳር ያለአግባብ መጠቀም ደግሞ የስኳር ሕመም ላለባቸው ሰዎች ህመማቸውን ያባብስባቸዋል። ሲጋራ ማጨስም በይበልጥ ለሳንባና ለልብ ሕመም ያጋልጣል። የአልኮል መጠጥ ጎጂ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጫት ቃሚዎችን ወደስህተት ያስገባል። ጫት ቅመው

አልኮል የሚጠጡ ሰዎች ጥንቃቄ ለጎደለው የግብረሥጋ ግንኙነት ይገፋፋሉ። ይህም ለአባላዘር በሽታዎችና ለኤች.አይ.ቪ. ያጋልጣቸዋል።

ጫት መቃም ጤናን ከመጉዳቱ በተጨማሪ ምጣኔሀብትን ያቃውሳል። የሚቅሙ ሰዎች በየዕለቱ ለጫት መግዣ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ። ከዚህም በተጨማሪ የሥራ ጊዜያቸውን በጫት መቃም ስለሚያባክኑ ገቢያቸው ይቀንሳል። በዚህ የተነሳ ቤተሰባቸውን ለመምራት ይቸገራሉ። የቤተሰብ ፍቅር ያሳጣቸዋል፤ ቀስበቀስ ቤተሰብ ወደማፍረስ ሊያመሩ ይችላሉ።

ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ይገናኛሉ። በሀዘን፣ በደስታ፣ በሥራና በተለያዩ ሁኔታዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ። ጫት የሚቅሙ ሰዎች ግን በሱስ ስለሚጠመዱ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ጫት በመቃም ነው። የሚኖራቸው የማኅበራዊ ግንኙነት ተሳትፎ አነስተኛ ይሆናል። ይህም በማኅበረሰቡ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ዝቅተኛ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ጫት መቃም ጎጂ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይ በጤና፣ በምጣኔ ሀብታዊና በማህበራዊ ሕይወት በርካታ ችግሮችን ይፈጥራል። የሥራ ባህልን ይጎዳል። ስለሆነም ሰዎች የጫት ጎጂነትን በመረዳት የራሳቸውን ግላዊ ነጻነት ለጫት ሱስ አሳልፈው ላለመስጠት መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።

(*ከአበሻ ድረገጽ። መነሻነት የተወሰደ*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

«ጫት መቃምና መዘዙ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን የሀሳብ ግንኙነት ማሳያ የቢጋር ሠንጠረዦች አሟሉ።

ሀ. ጫት መቃም → ስኳር ያለአግባብ መጠቀም → _____

ለ. ጫት መቃም → _____ → ለሳንባና ለልብ ሕመም ያጋልጣል።

ሐ. _____ → ለአልኮል መጠጥ ይዳርጋል። → _____ → ለአባላዘር በሽታዎችና ለኤች. አይ.ቪ. ያጋልጣል።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «ጫት መቃምና መዘዙ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «ጫት መቃምና መዘዙ» ከሚለው ምንባብ ከእያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ ዋና ሀሳቡን የያዘ አንድ አንድ ዓረፍተነገር ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።

ለ. «ጫት መቃምና መዘዙ» ከሚለው ምንባብ ካወጣችኋቸው ዋናዋና ሀሳቦች ውስጥ አንዱን ወስዳችሁ በምክንያትና ውጤት ስልት በራሳችሁ አገላለጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

# 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት የመዝገበቃላት ፍቺ መስጠት

## ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት ከመዝገበቃላት በመፈለግ ፍቺ ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሕይወት | መ. ሥነምግባር | ሰ. ድብርት |
| ለ. መዘዝ | ሠ. አለመረጋጋት | ሸ. ጠረን |
| ሐ. ሱስ | ረ. ድርቀት | |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ተራኪ ድርሰት መጻፍ

## ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም «ቁማር» በሚል ርዕስ አምስት አንቀጾች ያሉት ተራኪ ድርሰት ጻፉ።

## የቢጋር ሠንጠረዥ

| ርዕስ | ቁማር |
|---|---|

↓

**የአንቀጽ 1 ዋና ሀሳብ**

**የቁማር ምንነት**

መዘርዝሮች ______________________________

__________________________________________

__________________________________________።

| የአንቀጽ 2 ዋና ሀሳብ | የአንቀጽ 3 ዋና ሀሳብ |
|---|---|
| የቁማር ዓነቶች | ቁማር የሚያስከትላቸው ችግሮች |

መዘርዝሮች _________________________

_______________________________________

_______________________________________

____________________።

መዘርዝሮች ____________________

__________________________________

__________________________________

_____________።

**የአንቀጽ 4 ዋና ሃሰብ**

**መፍትሔ**

መዘርዝሮች ______________________________________________________________

_______________________________________________________።

**5. ማጠቃለያ**

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በማስተካከል ዓረፍተነገሮቹን አቃንታችሁ ጻፉ።

ምሣሌ፡- ቤተሰቦቹ አቅማቸው (የፈቀደው) እያደረጉለት ነው።

ቤተሰቦቹ አቅማቸው የፈቀደውን እያደረጉለት ነው።

ሀ. እሷ የሃያ (ዓመታት) ወጣት ናት።

ለ. ትምህርቱን በሚገባ (የማይከታተል) የፈተና ውጤቱ ሁሉ ዝቅተኛ ሆነ።

ሐ. ሰዎች በሥራና በዕውቀት ራሳቸውን ካላሻሻሉ (ኑሮ) መለወጥ አይችሉም።

መ. የጫትቤት ባለቤቶች ጫት ቃሚ (ደንበኛ) ይወዷቸዋል።

ሠ. የእሷ ከትምህርትቤት መቅረት (ጓደኞቿ) ሆነ መምህሮቿን ግራ (ማጋባት) መጣ።

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

**ጫት መቃምና መዘዙ**

## ቅድመንባብ

### ተግባር

«ጫት መቃምና መዘዙ» በሚል ርዕስ 1ኛ ሳምንት፣ 1ኛ ቀን የቀረበውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት የሚያነቡላችሁን ተጋባዥ እንግዳ በጥሞና አዳምጡ።

## ማንበብ

### ተግባር

«ጫት መቃምና መዘዙ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተጋባዥ እንግዳው እንዳነበቡት አድርጋችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

## ሲጋራ ማጨስ



### ቅድመማዳመጥ

### የተውሶ ቃላትን ማስተዋወቅ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የተውሶ ቃላት በጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ፍቻቸውን በቃላችሁ ግለጹ።

ሀ. ፒፓ
ለ. ካንሰር
ሐ. ታር
መ. ኒኮቲን
ሠ. ካርቦንሞኖኦክሳይድ

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

«ሲጋራ ማጨስ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እናንተ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ሀሳብ በመገመት አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ሥዕሉ ከምንባቡ ጋር ምን ግንኙነት ያለው ይመስላችኋል?

ለ. የትምባሆ ቅጠል ማጨስ በእነማን ተጀመረ?

ሐ. ሲጋራ ማጨስ ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚያጋልጥ እንዴት ሊታወቅ ቻለ?

መ. ሲጋራ ለማጨስ የሚያነሳሱ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ሠ. ሰዎች በሲጋራ ሱስ የሚጠመዱት ለምንድን ነው?

## ሰዋስው

### ጥገኛ መስተፃምር

ማስታወሻ

መስተፃምሮች በነጠላ ዓረፍተነገር ማሠሪያ አንቀጽ ላይ በሚያርፉበት ጊዜ ማሠሪያ አንቀጹን እንዲያሥር በማድረግ ነጠላ ዓረፍተነገሩን ወደጥገኛ ዓረፍተነገር ይለውጡታል። ጥገኛ ዓረፍተነገሩንም በሌላ ዓረፍተነገር ላይ ተጠግቶ እንዲነገር ያደርጉታል። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ፡ በ- ከ- ለ- ስለ- እንደ- ናቸው።

ምሣሌ፡- ጫት ጤናን ያውካል።

ጫት ጤናን ስለሚያውክ ...

### ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን ነጠላ ዓረፍተነገሮች ስለ- እንደ- ከ- በ- ለ- የሚሉትን መስተፃምሮች በመጠቀም ወደጥገኛ ዓረፍተነገሮች ለውጧቸው።

ሀ. ጎበዟ ልጅ አጠናች።

ለ. ረጅሙ ልጅ ሮጠ።

ሐ. ሁሉም ሰው አገሩን ወደደ።

መ. በርካታ ተማሪዎች ከሱስ ነጻ ሆኑ።

ሠ. የአካባቢው ሰዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን አጠናከሩ።

ረ. መጥፎ ሽታ ሸተተኝ።

ሰ. እህቴ ሄደችበት።

ሰ. መምህሯ ክፍል ውስጥ ገባች።

## ማንበብ

### የሱሰኝነት ተፅዕኖ

**ቅድመንባብ**

*መተንበይ*

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የሱሰኝነት ተፅዕኖ» የሚለው ርዕስ ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. ሱሰኛ መሆን ምን ምን ችግሮችን የሚያስከትል ይመስላችኋል?

**የማንበብ ሂደት**

**ተግባር**

ቀጥሎ «የሱሰኝነት ተፅዕኖ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን በማጤን ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### የሱሰኝነት ተፅዕኖ

ሱስ አንዴ ከተለመደ በኋላ በየጊዜው ውል የሚል አምሮት ወይም አምጡ አምጡ የሚያሰኝ ልማድ ነው። ሱስ ከሚያስይዙ ነገሮች መካከል ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃምና አልኮል መጠጣት ዋናዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ ነገሮች ከተለመዱ በኋላ በየጊዜው እንድንወስዳቸው የሚያስገድዱንና የሚያሰኙን ልምዶች ናቸው። በዚህም ምክንያት ሰዎችን ለሱሰኝነት ያጋልጣሉ። ሱሰኝነት ደግሞ ለጤና፣ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ለማህበራዊ ሕይወትና ለሥነልቦና ችግሮች ይዳርጋል።

#### ሲጋራ ማጨስ

ከሱስ አስያዥ ነገሮች አንዱ የሆነው ሲጋራ በውስጡ ኒኮቲን የሚባል ንጥረነገር ስለያዘ፣ የማነቃቃትና ሱስ የማስያዝ ኃይል አለው። ሲጋራ ከኒኮቲን በተጨማሪ ከ4000 በላይ ኬሚካሎች ስለሚይዝ ለጤና ጠንቅ ይሆናል። የሚያጨሱ ሰዎች የሲጋራውን ጭስ ወደሳንባቸው በሚስቡበት ጊዜ እነዚህ ኬሚካሎች ወደሰውነታቸው

ይሠራጫሉ። በዚህ ምክንያት ለሳንባ ካንሰርና ለተለያዩ በሽታዎች ይጋለጣሉ። ጥናቶች እንዳረጋገጡት ሲጋራ የሚያጨሱ ሰዎች ከማያጨሱት ሰዎች ጋር ሲነጻፀሩ በሳንባ ካንሰር የመጠቃት ዕድላቸው አሥር እጥፍ ይሆናል።

የሲጋራ ሱስ ከጤና ችግር በተጨማሪ ለምጣኔ ሀብታዊ ችግር ያጋልጣል። ሱስ ያለባቸው ሰዎች አንድ ሲጋራ ካጨሱ በኋላ ሌላ ሳያጨሱ መቆየት የሚችሉት ሁለት ሰዓት ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት የሲጋራ ሱሰኞች በተመሳሳይ ስሜት ውስጥ ለመቆየት ቶሎ ቶሎ ለማጨስ ይገደዳሉ። ይህም ለሲጋራ መግዣ ገንዘብ ስለሚያወጡ ለምጣኔሀብታዊ ችግር ያጋልጣቸዋል። ካላጨሱ የመበሳጨትና የመነጫነጭ ስሜት ስለሚፈጥርባቸው ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወን ይሳናቸዋል።

## ጫት መቃም

እንደሲጋራ ማጨስ ሁሉ ጫት መቃም ሱስ ያስይዛል። ጫት የአደንዛዥነትና ለሱስ ተገዢ የማድረግ ኃይል አለው። በዚህ ምክንያት በሱሰኞች ላይ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል። በጫት ሱስ መጠመድ የሥራ ባህልን ስለሚጎዳ ለግለሰብም ሆነ ለሀገር ዕድገት ፀር ይሆናል። የጫት ሱስ ከጥርስ ጀምሮ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ጉዳት ያስከትላል፤ የአእምሮ ሥርዓትንም ያዛባል። በተለይ ወጣቶች አፍላ ዕድሜያቸውን በትምህርትና በሥራ እንዳያሳልፉ እንቅፋት በመሆን ለቦዘኔነት፣ ለድብርትና ለብስጭት ይዳርጋቸዋል።

> **የጫት ሱስ፣ ወጣቶች አፍላ ዕድሜያቸውን በትምህርትና በሥራ እንዳያሳልፉት እንቅፋት በመሆን ለቦዘኔነት፣ ለድብርት፣ ለብስጭት ይዳርጋቸዋል።**

## አልኮል መጠጣት

የአልኮል መጠጥ ከጫትና ከሲጋራ ባልተናነሰ ሁኔታ ለሱሰኝነት ያጋልጣል። የአልኮል ሱስ ለጤና ችግሮችና ለጉስቁልና ይዳርጋል። መጠጥ ስካርን ስለሚያስከትል ለጠብና ለሌሎች አደገኛ ወንጀሎች ያጋልጣል። በስካር መንፈስ ጥፋት የሚሠሩ ሰዎች ስካሩ ካለፈላቸው በኋላ በሠሩት ሥራ ይፀፀታሉ። ይህ ደግሞ ተደጋጋሚ ብስጭት ስለሚፈጥር የጤና ችግር ያስከትላል። አንዳንድ የአልኮል ሱስ ያለባቸው ሰዎች ለሲጋራና ለጫት ሱስም የሚጋለጡበት ሁኔታ አለ። ይህ ደግሞ ችግሩን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል።


በአጠቃላይ ሱሰኝነት የጤናና የምጣኔሀብታዊ ችግር ከማስከተሉ በተጨማሪ ማህበራዊ ተቀባይነትንም ስለሚያሳጣ ለማህበራዊ ሕይወት እንቅፋት ይሆናል። ሱሰኞች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን የቆየ ግንኙነት በማቋረጥ ለብቸኝነት ይጋለጣሉ። ለከፍተኛ ሱስ ከተጋለጡ በኋላ አብዛኞቹ ከሱሱ ለመውጣት ያዳግታቸዋል። ይህ ችግር ደግሞ ሁልጊዜ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንዲያዩ ያደርጋቸዋል። ራሳቸውንም እስከማጥፋት የሚደርሱ ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ሱሰኝነት ለተለያዩ ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

(ሪፖርተር። ሰኔ 7፣ 2006። *የትምህርት ነገር።* መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ በትክክል አሟሉ።



## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ሱሰኝነት ማህበራዊ ተቀባይነትን ሊያሳጣና ለማህበራዊ ሕይወት እንቅፋት ሊሆን የሚችለው እንዴት እንደሆነ አብራሩ?

ለ. ጫት መቃም ከግለሰብ አልፎ ለሀገር ዕድገት ፀር የሚሆነው እንዴት ነው?

## 5ኛ ቀን

# ቃላት

## የቃላት አጠቃቀም

### ተግባር

በምንባቡ መሠረት ከሚከተሉት ቃላት መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ስኳር | ጠንቅ | ቦዘኔ | ተመሳሳይ | ችግር | ተገገር |
| አፍላ | አደንዛዥ | ፀፀት | ድብርት | ኒኮቲን | ግለሰብ |

ሀ. ሲጋራ በውስጡ _______ የሚባል አነቃቂ ንጥረነገር አለው።

ለ. የሲጋራ ሱስ ሰዎችን ለምጣኔሀብታዊ _______ ያጋልጣል።

ሐ. በ _______ ዕድሜ ከሱሰኝነት መራቅ ብልህነት ነው።

መ. ሰውየው _______ ተጫጭኖታል።

ሠ. አዘውትሮ _______ ዕፅ መጠቀም ተስፋቢስ ያደርጋል።

ረ. ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃምና አልኮል መጠጣት ለጤና _______ ነው።

ሰ. በሱስ ምክንያት ከሥራ ተባሮ _______ ሆኗል።

ሸ. በኋላ _______ ላይ ከመውደቅ ራስን ከሱስ ማራቅ ይሻላል።

ቀ. ሲጋራ ማጨስ፣ ጫት መቃምና አልኮል መጠጣት ለሱስ _______ ያደርጋሉ።

በ. የሲጋራና የጫት ሱሰኞች በ _______ ስሜት ውስጥ ለመቆየት ቶሎቶሎ ቅመው ያጨሳሉ።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም «አልኮል መጠጣት» በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት ሦስት አንቀጾችን ጻፉ።

| ምክንያት |
| --- |
| የአልኮል መጠጥ ሱስ |

| ውጤት |
| --- |
| ምጣኔ ሀብትን ያናጋል። |
| ለአደገኛ ወንጀሎች ያጋልጣል። |
| ለሞት ይዳርጋል። |

### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

የቃላትን ቅደምተከተል እንደገና በማዋቀር ዓረፍተነገሩን በትክክል ጻፉ።

ሀ. ያዛባል የአዕምሮ ሥርዓትን ጫት።

ለ. በግብርና ሥራ ቢሰማሩ ውጤታማ ይሆናሉ የተማሩ ሰዎች።

ሐ. የሥራ ባህልን ስለሚጎዳ ለሀገርም ሆነ ለግለሰብ ዕድገት ፀር ነው ጫት መቃም።

መ. ያጋልጣል የአልኮል መጠጥ ስካር ስለሚያስከትል ለጠብ፣ ለሥርቆትና ለሌሎች አደገኛ ወንጀሎች።

ሠ. ሁለት ሰዓት ብቻ ነው ሳያጨሱ መቆየት የሚችሉት ሱስ ያለባቸው ሰዎች።

**6ኛ ቀን**

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሱሰኝነት ተፅዕኖ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የሱሰኝነት ተጽዕኖ» ከሚለው ምንባብ የምታስታውሷቸውን ሀሳቦች ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «የሱሰኝነት ተጽዕኖ» የሚለውን ምንባብ አንብቡ።

## መናገር

### ክርክር

#### ተግባር

«ጫት መቃም ጎጂ ነው፤ ጫት መቃም ጎጂ አይደለም» በሚሉ ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች ላይ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ተከራከሩ።

## ሰዋስው

### ጥገኛ ዓረፍተነገሮችን አሟልቶ መጻፍ

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥገኛ ዓረፍተነገሮች በምሣሌው መሠረት አሟልታችሁ ጻፉ።

ምሣሌ፡- ሱሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ …

ሱሰኝነት ሰዎችን ስለሚጎዳ ከሱስ ነጻ እንሁን።

ሀ. ሰውዬው ሱሰኛ ስለሆነ

ለ. ከበደን የጫት ሱስ ከያዘው

ሐ. እነሱ የሲጋራውን ጪስ ሲስቡት

መ. እህቱ አብራው ከሄደች

ሠ. የትምባሆ ቅጠል በመላው ዓለም እንደተሠራጨ

ረ. ሲጋራ የሳንባ ካንሠር ስለሚያመጣ

# የግል ሕይወትን መምራትና ከሱሰኝነት መራቅ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ዕፅ-ኦች-ን | ዕፆችን |
| ለ | የሚ-ያነቃቃ-ኣቸው | የሚያነቃቃቸው |
| ሐ | የሚ-ያዝናና-ኣቸው-ና | የሚያዝናናቸውና |
| መ | ተቀባይ-ነት-ኣቸው-ና | ተቀባይነታቸውና |
| ሠ | ሊ-ያጋጥም-ኡ-ኣቸው | ሊያጋጥሟቸው |

## ማንበብ

### ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ለሱስ ተገዥ መሆን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ሱሰኞችን ከሱሳቸው ማላቀቅ ይቻላል? እንዴት?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ «ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን የምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማጤን ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት

ሱሰኝነት ሲጋራ በማጨስ፣ ጫት በመቃም፣ የተለያዩ አደንዛዥ ዕፆችን በመጠቀምና የአልኮል መጠጥ በመጠጣት የሚመጣ ልምድ ነው። አንዳንድ ሰዎች ሌላው ያደረገውን ሁሉ ለማድረግ በመፈለግ ለሱስ ይጋለጣሉ። በተለይም ታዳጊ ወጣቶች ሲጋራ ማጨስንና ጫት መቃምን የሥልጡንነት፣ የትልቅነት፣ የነጻነትና የአዋቂነት ምልክት ያደርጉታል። በዚህ የተነሳ ጫት መቃምና ሲጋራ ማጨስ ይጀምራሉ። ቀስበቀስም ወደሱሰኝነት ይሸጋገራሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በሱስ ውስጥ ያሉ ጓደኞቻቸውን ፍቅር ላለማጣት ሲሉ በሱስ ይጠመዳሉ። ራስን ባለማወቅና የሱሰኝነትን ጉዳት ባለመገንዘብ በችግሩ ውስጥ የሚገቡም በርካቶች ናቸው።

**የግል ሕይወትን ለመምራት ከሱሰኝነት ነጻ መሆን ያስፈልጋል።**

ለሱስ ተገዥ የሆኑ ሰዎች በርካታ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ራሳቸውን በፈለጉት መንገድ አይመሩም፤ መሪያቸው ጫት ወይም ሲጋራ ነው፤ የሚያነቃቃቸው፣ የሚያዝናናቸውና ከጭንቀት የሚያወጣቸው ጫት ወይም ሲጋራ ይመስላቸዋል። በመሆኑም ጫት መቃምንና ሲጋራ ማጨስን ስለሚያዘወትሩ የምጣኔ ሀብታዊ ቀውስ ያጋጥማቸዋል፤ ጤንነታቸው ይታወካል፤ ማህበራዊ ግንኙነታቸውም ይላላል፤ ማህበራዊ ተቀባይነታቸውን እያጡ ይሄዱና በሂደትም የግል ህይወታቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን መምራት ይሳናቸዋል።

### ከሱስ ነጻ መውጫ መንገዶች

በሱስ የተጠመዱ ሰዎች ራሳቸውን ነጻ ማውጣት ይኖርባቸዋል። ለዚህም ራስን ማወቅ፣ ጥሩ ጓደኛ መምረጥ፣ ስለቤተሰብ ማሰብና መወሰን ራስን ከሱስ ለማውጣት የሚረዱ ዋናዋና ዘዴዎች ናቸው። ራስን ለማወቅ ደግሞ ስለራስ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማንነትን መረዳትና ራስን መምራት ያስፈልጋል። ለምሣሌ፣ እኔ ማን ነኝ? ነገ መሆን የምፈልገው ምንድን ነው? ቤተሰቦቼ ከእኔ ምን ይፈልጋሉ? ምን ብሠራ ካሰብኩበት ልደርስ እችላለሁ? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ለራስ በመጠየቅ ማንነትን ማወቅ ይቻላል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ መስጠትና ሁሉንም ወደተግባር መለወጥ ራስን የማወቂያ መንገዶች ናቸው።

ከሱሰኝነት ለመራቅ ሌላው መንገድ ትክክለኛ ጓደኛ መምረጥ ነው። በተለይም የሱሰኝነት ተፅዕኖ ያለባቸው ሰዎችን ጓደኛ ማድረግ ባልተያዙ ሰዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ምክንያቱም የጓደኞቻቸውን ፍቅር ላለማጣት ወደማይፈልጉት

ነገር ሊያስገባቸው ይችላል። ለምሣሌ፣ አጫሾቹም ሆኑ ጫት ቃሚዎች ለራሳቸው የሚመቻቸው ነገር ለጓደኞቻቸውም የሚያመቻቸው መስሎ ስለሚታያቸው የማያጨሱ ወይም የማይቅሙ ጓደኞቻቸውን ወደራሳቸው ልምድ እንዲመጡላቸው ይገፋፏቸዋል። ይህ ሁኔታ ሌሎችንም ለሱስ ተገዥ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። ከዚህ ችግር ለመዳን ጓደኛን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል።

ከዚህም በተጨማሪ ከሱሰኝነት ለመራቅ ለቤተሰብ ማሰብ አንዱ መንገድ ነው። ሱሰኝነት ራስንም ሆነ ቤተሰብን ለመምራት እንቅፋት ይሆናል። ለምሣሌ የሲጋራ ሱስ ያለባቸው ሰዎች የራሳቸው ጤና ከመጎዳቱ በተጨማሪ የቤተሰቦቻቸውን ጤንነት ያውካሉ፤ ለምጣኔ ሀብታዊ ችግር ያጋልጣሉ፤ ሱሰኞች ስለቤተሰባቸው ቀርቶ ለራሳቸው ማሰብና መጨነቅ አይፈልጉም። ስለዚህ ከዚህ ችግር ሊወጡ የሚችሉት የኔ መኖር ለቤተሰቦቼ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ሲችሉ ነው። ቤተሰብን ለመምራት ከሱስ መራቅ፣ ከሱስ ለመራቅ ደግሞ ቤተሰብን ማሰብ ያስፈልጋል።

**ቤተሰብን ለመምራት ከሱስ መራቅ፣ ከሱስ ለመራቅ ደግሞ ቤተሰብን ማሰብ ያስፈልጋል።**

በሌላ በኩል የሱስ ተገዥ የሆኑ ሰዎች ከሱስ ለመላቀቅ መወሰን አለባቸው። የወሰኑትን ውሣኔ ደግሞ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ከሱሰኝነት ሲላቀቁ ጤነኛ እንደሚሆኑና ራሳቸውንም መምራት እንደሚችሉ ማመን ይኖርባቸዋል። በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ከሱስ መላቀቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ከሱስ ለመራቅና ለመላቀቅ መወሰን ያስፈልጋል።

## ከሱስ የመላቀቅ ጠቀሜታ

ራሳቸውን ከሱስ ነጻ ያደረጉ ሰዎች በጤንነታቸው፣ በምጣኔሀብታቸውና በማህበራዊ ግንኙነታቸው ላይ ችግር አይኖርባቸውም። ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን በተገቢው መምራት ይችላሉ። በሱስ ምክንያት ለሚመጡ የጤና ችግሮች አይጋለጡም። ገንዘባቸውን ለፈለጉትና ላቀዱት ነገር ማዋል ይችላሉ። ሥራቸውን በተገቢው ጊዜና በጥራት ማከናወን ይችላሉ። ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነት ይኖራቸዋል፤ በሰዎች ዘንድም ያላቸው ተቀባይነት ይጨምራል። የሚወደዱና የሚከበሩ ጠቃሚ ሰዎች ይሆናሉ።


በአጠቃላይ ሱሰኝነት በጤና፣ በምጣኔ ሀብትና በማህበራዊ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ስለዚህ ራስን በማወቅ፣ ጥሩ ጓደኛን በመምረጥና ስለቤተሰብ

በማሰብ ከሱሰኝነት መራቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሱስ ከሚያሲዙ ነገሮች በመቆጠብ የግል ሕይወትን በአግባቡ መምራት ተገቢ ነው።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ አሟሉ።




### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ለሱስ ተገዥ የሆኑ ሰዎች ምን ምን ዓይነት ችግሮች ያጋጥሟቸዋል?

ለ. በሱስ ውስጥ የገቡ ሰዎች ራሳቸውን እንዴት ነጻ ማውጣት እንደሚችሉ በተግባር አንድ ያቀረባችኋቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ።

ሐ. «ራስን ማወቅ ከሱስ ነጻ ለመሆን ይረዳል።» «ራስን ማወቅ ኤች አይ ቪን ለመከላከል ይረዳል።» በሚሉት አገላለጾች የተሰመረበትን ሐረግ በማነጻፀር አብራሩ።

መ. በሱስ የተጠመዱ ሰዎች ራሳቸውን ከሱስ ነጻ ባያደርጉ ምን ችግር ይደርስባቸዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሠ. በምንባቡ በ7ኛው አንቀጽ ራሳቸውን ከሱስ ነጻ ያደረጉ ሰዎች የሚያገኟቸውን ጠቀሜታዎች በተመለከተ መስማማት አለመስማማታችሁን በምክንያት ግለጹ።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ሐረጋትን መመሥረት

#### ተግባር

ቀጥሎ ከቀረቡት ገላጮች ተስማሚ የሆኑትን በመምረጥና ከ«ሀ»-«ሰ» ከተዘረዘሩት ቃላት ጋር በማዋቀር ሐረጎችን መሥርቱ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰፊ | ጠንካራ | ፈጣን | ቀጭን | ለጋስ | ረዥም | ጥሩ |
| ትልቅ | ሰነፍ | ፍሬያማ | አዋቂ | ደግ | ጠባብ | |

ሀ. ሰው

ለ. መንገድ

ሐ. ቤተሰብ

መ. ሀገር

ሠ. ጓደኛ

ረ. ሥራ

ሰ. ወጣት

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን «አልኮል መጠጣት» በሚል ርዕስ የጻፋችኋቸውን አንቀጾች ቀጥሎ በቀረበው የማመሳከሪያ ቅጽ መሠረት በመገምገም አስተካክላችሁ ጻፉ።

**የጽሑፍ ጥራት ማረጋገጫ ቅጽ**

- አንቀጾቹ አንድነት፣ ግጥምጥምነትና ትኩረት አላቸው?
- አንቀጾቹ በምክንያትና ውጤት ስልት የተዋቀሩ ናቸው?
- በአንቀጾቹ የሥርዓተነጥቦች አጠቃቀም ተገቢ ነው?
- አንቀጾቹ ተገቢ ማጠቃለያ/መደምደሚያ አላቸው?

### የአጻጻፍ ሥርዓት

#### ተግባር 1

በቅንፍ ውስጥ ያለውን ቃል ቅርፅ በማስተካከል ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።

ሀ. የአልኮል፣ (ጫት) የሲጋራ ሱሰኞች ማህበራዊ (ተቀባይ) ዝቅተኛ ነው።

ለ. ለሱስ ተገዥ የሆኑ (ሰው) በርካታ ችግሮች (ሊያጋጥም)።

ሐ. የግል (ሕይወት) በአግባቡ መምራት (ተገቢነት) ነው።

#### ተግባር 2

የቃላትንና የሐረጋትን ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገሮችን እንደገና ጻፉ።

ሀ. ከመጥፎ ሱስ ማውጣት አለባቸው ሰዎች ራሳቸውን።

ለ. ምጣኔ ሀብትን ከማውደም አልፎ ቤተሰብን ሊበትን ይችላል አልኮል መጠጣት፣ ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም።

ሐ. የሥራ ባህላችን ይዳከማል እየተስፋፋ ከመጣ ጫት መቃም።

## 9ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

በማንበብ ሂደት «ሐረግን በአንድ ትንፋሽ ማንበብ» ማለት ምን ማለት ነው?

### ማንበብ

#### ተግባር

«ከሱሰኝነት ነጻ መውጣት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚወስኑላችሁ ደቂቃ መሠረት አንብቡ።

# መናገር

### በማስረጃ የተደገፈ ንግግር

#### ተግባር

ሱሰኝነት ማህበራዊ ተቀባይነትን ያሳጣል ወይስ አያሳጣም? ለምን? የተለያዩ ማስረጃዎችን በመጠቀም ሀሳባችሁን በንግግር አቅርቡ።

# ሰዋስው

### ድብልቅ ዓረፍተነገር መመሥረት

#### ተግባር

ጥገኛ መስተጻምሮችን በመጠቀም ድብልቅ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሣሌ፡-

ሱሰኝነት የምጣኔ ሀብት ችግር ያመጣል።

ማኅበረሰቡ ግንዛቤ አለው።

ሱሰኝነት የምጣኔ ሀብት ችግር እንደሚያመጣ ማኅበረሰቡ ግንዛቤ አለው።

ሀ. ረጅሙ ልጅ ቦርሳውን ወሰደ።

የልጁ አባት ተቆጣ።

ለ. ሰውዬው ሆስፒታል ሄደ።

ሰውዬው ሕክምናውን አላገኘም።

ሐ. እሱ ከመጠጥ ሱስ ተላቀቀ።

እሱ የአልኮል መጠጥ አይጠጣም።

መ. የተላከለትን ደብዳቤ ተቀበለ።

የደብዳቤውን መልስ ጻፈ።

ሠ. ሰንጋው ዛሬ ጧት ታረደ።

አንድ መደብ ሥጋ ገዛሁ።

ረ. ሴትዮዋ ሌባውን ያዘችው።

ሴትዮዋ ሌባውን በአንድ ቡጢ ጣለችው።



# ምዕራፍ 8

## አርበኝነት

### የአርበኛ የሕይወት ታሪክ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ደብረ-መዊዕ | ደብረመዊዕ |
| ለ | እሰጥ-አገባ-ው | እሰጣገባው |
| ሐ | አሻራ-አቸው-ን | አሻራቸውን |
| መ | በ-ማህደረ-ማርያም | በማህደረማርያም |
| ሠ | ተልዕኮ-አቸው-ን | ተልዕኳቸውን |
| ረ | ተግባር-ኦች-አቸው-ም | ተግባሮቻቸውም |
| ሰ | ቴ-ክ-ኖ-ሎ-ጂ-ው-ን | ቴክኖሎጂውን |

## ማንበብ

### እቴጌ ጣይቱ ብጡል

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በፎቶግራፉና በምንባቡ መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?

ለ. ስለእቴጌ ጣይቱ ብጡል የምታውቁትን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«እቴጌ ጣይቱ ብጡል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ በመሆን ንዑስ ርዕስ በመከፋፈልና ድምፅ ሳታሰሙ በማንበብ የተረዳችሁትን ለጓደኛችሁ ግለፁ።

## እቴጌ ጣይቱ ብጡል



ጣይቱ ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡልና ከእናታቸው ከወይዘሮ የውብዳር ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም. በአሁኑ ደቡብ ጎንደር ዞን ደብረታቦር ከተማ ተወለዱ። አባታቸው የጎንደርና የወሎ፣ እናታቸው ደግሞ የጎጃም ተወላጅ ናቸው። አባታቸው በጦርነት በመሞታቸው በ13 ዓመታቸው ደብረታቦርን ለቀው ወደእናታቸው ትውልድ ቦታ ወደጎጃም ሄዱ። ጎንደር እያሉ፣ በማህደረማርያም፣ የጀመሩትን ትምህርታቸውን በጎጃም ደብረመዊዕ ደብር ቀጠሉበት።

### የጋብቻ ሕይወት

የአፄ ቴዎድሮስ ዘመን እንደተጋመሰ ጣይቱ የንጉሠ ነገሥቱ አዛዥ የነበሩትን አንዱን መኰንን አገቡ። የአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ሲያበቃ የቀድሞ ባላቸውን ፈተው ከአፄ ዮሐንስ የጦር አለቆች አንዱን አግብተው ለተወሰነ ጊዜ ወደትግራይ ሄደው

ተቀምጠዋል። ባለቤታቸው በአፄ ዮሐንስ ተይዘው ሲታሰሩ እንደገና ወደጎጃም ተመለሱ። ወደጎጃም እንደተመለሱም ያቋረጡትን ትምህርት ለሦስተኛ ጊዜ በመቀጠል ጽሕፈትን፣ ንባብን፣ ግዕዝንና የአማርኛ ቅኔን ተማሩ። ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በጥበብና በሕይወት ፍልስፍና የላቀ ችሎታ እንዳላቸው እየታወቀ መጣ። የጣይቱን ዝና ከሰሙት መካከል አንዱ አፄ ምኒልክ ናቸው። ንጉስ ምኒልክ በሚያዚያ ወር 1869 ዓ.ም. ወደባህር ዳር ተጉዘው በእናታቸው በወ/ሮ የውብዳር ቤት ዘመድ ወዳጅ በታደመበት ከወ/ሮ ጣይቱ ብጡል ጋር ተጫጩ። ከዚያም ሚያዝያ 25 ቀን 1875 ዓ.ም. በአንኮበር መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን በቁርባን ተጋቡ። ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም. ጣይቱ ብጡል «እቴጌ» ተብለው ተሰየሙ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስማቸው በመላው ሀገሪቱ ነገሠ።

## ፖለቲካ

እቴጌ ጣይቱ አፄ ምኒልክን ካገቡ በኋላ ያልተሰለፉበት ምጣኔሀብታዊ፣ ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ጉዳይ አልነበረም። አፄ ምኒልክ አዳዲስ ሥልጣኔዎችን ከውጪ ለማስገባት ቁርጠኛ አቋም ይዘው ሲሰሩ፣ ዋና አማካሪያቸውና አጋራቸው እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። የቴክኖሎጂ ውጤቶች ወደኢትዮጵያ ሲገቡ አፄ ምኒልክን ያበረታቱ ነበር። ሌሎች ሰዎች ቴክኖሎጂውን ከሰይጣን ሥራ ጋር እያያያዙ ሲቃወሙ በግንባር ቀደምትነት የሚደግፏቸው እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። ፖለቲካዊና ሀይማኖታዊ ክርክሮች ላይ እየተገኙ የመንግሥታቸውን አቋም ያስረዱና ይከራከሩ ነበር። አፄ ምኒልክ ወደዘመቻ ሲንቀሳቀሱ የመንግሥት ዓይንና ጆሮ ሆነው አገልግለዋል። ስያሜዋን ከመስጠት ጀምሮ የአዲስ አበባን ከተማ የመሠረቷት እቴጌ ጣይቱ ናቸው።የመጀመሪያውን ዘመናዊ ሆቴልም ከፍተዋል።እነዚህና ሌሎች ጉልህ ተግባሮቻቸው ስማቸው ዘላለማዊ ሆኖ እንዲታወስ አድርገዋቸዋል።

እቴጌ ጣይቱ በፖለቲካ ተግባራቸውም የሚታወስ ጠንካራ ታሪክ አላቸው።ጣሊያኖች በውጫሌ ውል ካሰፈሯቸው ነጥቦች መካከል አንቀጽ «17» ሥር ያለው ሀሳብ በስህተት መተርጎሙን አጥብቀው ተቃውመዋል። አንቀጽ «17»ን ጣሊያኖች ኢትዮጵያን በሚጎዳ መልኩ አዛብተው ጥቅም ላይ እንዲውል ባደረጉበት ጊዜ «ውሉን ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ» በማለት የማያወላውል አቋማቸውን አሳውቀዋል። በዚህም በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል እሰጣገባው ተካርሮ ጦርነቱ አይቀሬ ሆነ። አፄ ምኒልክ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ወደአድዋ ጦርነት ዘመቱ። እቴጌ ጣይቱም በራሳቸው የሚመራ 3000 እግረኛ ጦርና 6000 ፈረሰኛ አስከትለው ከባለቤታቸው ጎን በመሠለፍ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. አድዋ ላይ ጠላትን ድል አደረጉ።

> **እቴጌ ጣይቱ በተለያየ መልኩ አገራዊ ተልዕኳቸውን የተወጡ ጀግና ሴት ነበሩ።**

## የጦርነት ስልት

እቴጌ ጣይቱ ጦርነት ከመጀመሩ ከጥቂት ቀናት በፊት ለጦር አበጋዞች  የጦርነት ስልት አቀረቡ።ይህም የጠላት ወታደሮች ውኃ የሚጠጡበትን ምንጭ በመቆጣጠር ማጥቃት እንደሚቻል ያቀረቡት ሀሳብ ነበር። ሀሳባቸውም በአፄ ምኒልክና በሁሉም የጦር አበጋዞች ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ ጠላት ውኃ የሚጠጣበት ምንጭ በኢትዮጵያ ወታደሮች ቁጥጥር ሥር ዋለ። የጠላት ወታደሮችም እጃቸውን ከመስጠት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም።

በአጠቃላይ እቴጌ ጣይቱ በተለያየ መልኩ አገራዊ ተልዕኳቸውን የተወጡና በኢትዮጵያ ታሪክ አሻራቸውን ያሳረፉ ታላቅ ሴት ነበሩ። የኢትዮጵያን ነጻነት ባስጠበቀው የአድዋ ድል ትልቅ ሚና ከመጫወታቸው በተጨማሪ ሌሎች ማህበራዊ ተግባሮቻቸውም የሚያኮሩ ናቸው።እቴጌ ጣይቱ የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም፣ ስማቸውና ያከናወኗቸው ተግባራት ግን ከሌሎች እውቅ የኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ዘላለም ሲወሳ ይኖራል።

(ፈንታሁን እንግዳ። 2002። *ታሪካዊ መዝገበ-ሰብ ከጥንት እስከዛሬ።* ከገጽ 697-699፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ምንባቡን መሠረት በማድረግና የምልከታ ንባብን በመጠቀም የሚከተለውን የጊዜ ሰሌዳ በትክክል አሟሉ።

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ነሐሴ 12 ቀን 1832 ዓ.ም. እቴጌ ጣይቱ ከአባታቸው ከደጃዝማች ብጡልና ከእናታቸው ከወይዘሮ የውብዳር በደብረታቦር ከተማ ተወለዱ። | → | ሚያዝያ ወር 1869 ዓ.ም. | → | ሚያዝያ 25 ቀን 1875 ዓ.ም. | → | ጥቅምት 27 ቀን 1882 ዓ.ም. | → | የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. | → | የካቲት 4 ቀን 1910 ዓ.ም. |

### ተግባር 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ።

ሀ. እቴጌ ጣይቱ ትልቅ ጀብዱ በመፈፀም ድል ያደረጉበት ቦታ ምን ይባላል?

ለ. እቴጌ ጣይቱ ለጦርነት ሲዘምቱ ስንት እግረኛ ጦርና ፈረሰኞች ነበሯቸው?

ሐ. እቴጌ ጣይቱ «ውሉን ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ» ሲሉ ወስነዋል። እናንተ ብትሆኑ ሌላ ምን ዓይነት አማራጭ ትወስዱ ነበር? ለምን?

መ. እቴጌ ጣይቱ ያንን የጦርነት ስልት ባይቀይሱ ኖሮ ምን ሊፈጠር ይችል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሠ. ከምንባቡ የተማራችሁት ቁምነገር ምንድን ነው?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በቃል ክፍላቸው መመደብ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በሠንጠረዡ ከተሰጡት የቃል ክፍሎች በአንዱ መድቧቸው።

ሀ. አገቡ
ለ. ዮሐንስ
ሐ. ደብረታቦር
መ. ቅርብ
ሠ. ሆነ
ረ. ምኒልክ
ሰ. ትልቅ
ሸ. ናቸው
ቀ. አገራዊ
በ. ጎጃም


| ሥም | ግሥ | ቅፅል |
|---|---|---|
| | | |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የሕይወት ታሪክ መጻፍ

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም የ«ኮሌኔል አብዲሳ አጋ»ን የሕይወት ታሪክ በሦስት አንቀጽ ጻፉ።




## የአጻጻፍ ሥርዓት

## የሕይወት ታሪክ አጻጻፍ ቅደምተከተል

### ተግባር

የሚከተሉትን ሀሳቦች በቅደምተከተል ከመነሻ ወደመድረሻ አደራጅታችሁ ጻፉ።

ሀ. ስለአስተዳደግ ሁኔታ መጻፍ፣

ለ. የፈፀሟቸውን ጉልህ ተግባራትና ያበረከቷቸውን አስተዋፅኦዎች በቅደምተከተል መዘርዘር፣

ሐ. የባለታሪኩን ስም፣ የትውልድ ስፍራንና የትውልድ ዘመንን መጥቀስ፣

መ. ተግባራቱ ያስገኙላቸው ጥቅሞች

ሠ. የትምህርት ደረጃን መግለጽ፣

## አቀላጥፎ ማንበብ

### እቴጌ ጣይቱ ብጡል

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

ስለ «እቴጌ ጣይቱ ብጡል» በጣም የተመሰጣችሁበትን ድርጊት በቃላችሁ ግለጹ።

### ማንበብ

#### ተግባር

«እቴጌ ጣይቱ ብጡል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ እንዳነበቡት አድርጋችሁ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ /አባ መላ/



## ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

«ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ /አባ መላ/» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. በታሪክ የምታውቋቸውን አርበኞች ስም ዘርዝሩ።

ለ. ስለፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ የምታውቁትን ግለጹ።

### የማዳመጥ ሂደት

#### ተግባር

«ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ /አባ መላ/» በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ እያዳመጣችሁ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ አሟሉ።

| ሥም | ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ /አባ መላ/ |
|---|---|
| የትውልድ ዘመን | |
| ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ በማን ተማረኩ? | |
| ፊደልና ንባብ የት ተማሩ? | |
| አባ መላ የሚለውን ስም እንዴት አገኙ? | |
| የአድዋ ጦርነት መቼ ተካሄደ? | |
| በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የጦር ሚኒስትር ማነው? | |
| ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ስንት ልጅ ወለዱ? | |
| በጦር አበጋዝነትና አስተዳዳሪነት ስንት አመት ሰሩ? | |
| ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ በ1919 ዓ.ም ምን ሆኑ? | |

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

ከላይ በሠንጠረዡ ያሰፈራችኋቸውን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ስለፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ታሪክ ተናገሩ።

# ሰዋስው

## ጠቋሚ መስተኣምሮች

### ተግባር

የሚከተሉት መስተኣምሮች የዓረፍተነገሩን ባለቤት እንዲጠቁሙ አድርጋችሁ አስገቧቸው።

| እነዚያ፣ እነሱ፣ ያ፣ እሱ፣ ያቺ፣ ይህ፣ እሷ፣ ይቺ |
|---|

ምሣሌ:- ያ መጽሐፍ ጠቃሚ ነው።

ሀ. የተክሌ መማሪያ መፅሐፍ አዲስ ነው።

ለ. ልጆች ደስ የሚሉ አበቦች ገዙ።

ሐ. ሴትዮ የሳድያ እናት ትመስለኛለች።

መ. አግዳሚ ወንበር ብዙ ሰዎችን ያስቀምጣል።

ሠ. ሰዎች ልብስ ከገዙ ቆይተዋል።

ረ. ልጅ እናቷን በሥራ ታግዛለች።

## ማንበብ

### የሀገር ፍቅር

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ የቅድመንባብ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? በምንስ ይገለጻል?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«የሀገር ፍቅር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### የሀገር ፍቅር

የሀገር ፍቅር ሀገርንና ሕዝብን ሊጠቅሙ የሚችሉ ሥራዎችን በመሥራት ይገለጻል። ሰዎች በሀገር ፍቅር በመነሳሳት የሀገራቸውን ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃሉ፤ ከጠላት ይከላከላሉ። የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሀገራቸውን ሀብትና ንብረት ይንከባከባሉ፤ የሀገራቸውን ሕዝቦች ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ። የበጎ አድራጎት ተግባራትን ያከናውናሉ። ከዚህም በተጨማሪ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሰዎችን መብት ያከብራሉ፤ ድህነትንና ኋላቀርነትን ለማስወገድ ጠንክረው ይሠራሉ። ለሰንደቅዓላማና ለብሔራዊ መዝሙር ክብር ይሰጣሉ።

> **የሀገር ፍቅር ስሜት በምን ይገለጻል?**

#### የአርበኝነት ተግባር

የሀገር ፍቅር የሀገርን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅና ከወራሪ ጠላት በመከላከል ይገለጻል። የኢትዮጵያ አርበኞች የሀገራቸውን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅና ከወራሪ ኃይል ለመከላከል መስዋዕትነት ከፍለዋል። የጣሊያንን ወራሪ ኃይል ድባቅ መተዋል። ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀውን የጠላት ኃይል በሀገር ፍቅር

ስሜት ማርከዋል፤ ለሽንፈትም ዳርገውታል። የጣሊያንን ወታደር መግቢያና መውጫ አሳጥተው ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት እንዳትያዝ አድርገዋል። ይህ የጦርነት ተጋድሎ ከሀገር ፍቅር ስሜት የመነጨ ነው።

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሀገራቸውን ደህንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ የሕዝቦችን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ኢትዮጵያ በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተፈቃቅረው የሚኖሩባት ሀገር መሆኗን ቀድመው ይረዳሉ። የሕዝቦችን የየራሳቸው አኗኗር፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ኃይማኖት፣ ቋንቋና ባህል እንዳላቸው ይገነዘባሉ። በአጠቃላይ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ሕዝቦች ታሪክ ጠንቅቀው ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ። የሀገር ፍቅር ባለበት መፈቃቀርና መከባበር እንዳለ ይገነዘባሉ። የመተሳሰብና የመረዳዳትን ጠቀሜታ አውቀው ለሰላም ይታገላሉ። የሕዝቦችን ማንነት በመገንዘብ ተከባብሮ የመኖር ፍላጎታቸውን ያዳብራሉ።

> **የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ... የሕዝቦችን ታሪክ ጠንቅቀው ለማወቅ ጥረት ያደርጋሉ።**

## ድህነትንና ኋላቀርነትን ማሸነፍ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች ጠንካራ ሠራተኞች በመሆናቸው ድህነትና ኋላቀርነትን በቀላሉ በማሸነፍ ዕድገትና ብልፅግና እንዲመጣ ይጥራሉ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የተማሩ ከሆኑ ያልተማሩ ዜጎችን በተገቢው ያስተምራሉ። አርሶአደሮች ከሆኑ ከፍተኛ ምርት በማምረት ከራሳቸው አልፈው ለሀገራቸው ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ነጋዴዎች ከሆኑ በሚያገኙት ገቢ ልክ መክፈል የሚገባቸውን ግብር ይከፍላሉ። የሥራ ኃላፊዎች ከሆኑ ሕዝባቸውን በቅንነት በማገልገል ለሀገራቸው ዕድገት ጠንክረው ይሠራሉ።

## የበጎ አድራጎት ተግባር

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የበጎ አድራጎት ተግባራትን ያከናውናሉ። በተነሳሽነት ያለምንም ክፍያ ለሕዝብ አገልግሎት ይሰጣሉ። ወጣቶች ታናናሾቻቸውን ሊያስተምሩና ሊያሰለጥኑ ይችላሉ፡ አዋቂዎች የተራቆቱ አካባቢዎችን ደን በማልማት ይሸፍናሉ፤ ደም ይለግሳሉ። ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናትን ያሣድጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ ጧሪ የሌላቸውን አረጋውያን ይንከባከባሉ። እነዚህ ሁሉ የበጎ አድራጎት ተግባራት የሀገር ፍቅር መገለጫዎች ናቸው።

## የሀገር ሀብትን መንከባከብ

የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች የሕዝቦች የጋራ መገልገያ የሆኑትን ድልድዮችን፣ የኃይል ማመንጫ ተቋማትን ወዘተ. እንደዓይናቸው ብሌን ይንከባከባሉ፣ ይጠብቃሉ። እነዚህ ሀብቶች ያለአግባብ ከተበላሹ ወይም በሌባ ከተሰረቁ ተጎጂዎቹ

ሕዝቦች መሆናቸውን ስለሚገነዘቡ በጥንቃቄ በመጠበቅ ሕዝቦች በጋራ እንዲጠቀሙበት ያደርጋሉ።

ሰንደቅዓላማ የአንድ ሀገር መንግሥትና ሕዝብ ሉዓላዊነትንና ነጻነትን የሚያሣይ ምልክት በመሆኑ የሀገር ፍቅር ያላቸው ሰዎች በሚገባ ያከብሩታል። እንደሰንደቅዓላማ ሁሉ ለብሔራዊ መዝሙርም ትልቅ ክብር ይሰጣሉ። ለዚህ አብነት የሚሆኑን አትሌቶቻችን ናቸው። እነዚህ አትሌቶች በዓለም የውድድር አደባባዮች ድል ሲያደርጉ ደስታቸውን የሚገልጹት ሰንደቅዓላማችንን ከፍ አድርገው በማውለብለብ ነው። ከዚያም ብሔራዊ መዝሙራችንን በመዘመር ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር ይገልጻሉ።


**እንደሰንደቅ ዓላማ ሁሉ ለብሔራዊ መዝሙር ትልቅ ክብር ይሰጣሉ።**

(ኤፌዴሪ ትሚ። 2003። *ሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት*። ገጽ 48-57 መነሻነት የተዘጋጀ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

«የሀገር ፍቅር መገለጫዎች» የሚለውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በዙሪያው ያሉትን የቢጋር ሠንጠረዦች በምንባቡ መሠረት አሟሉ።




### ተግባር 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች የተብራራ መልስ ጻፉ።

ሀ. የሀገር ፍቅር ስሜትን ለመግለጽ ከአርበኝነት ተግባርና ከበጎ አድራጎት ተግባር የትኛው የተሻለ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. በዓለም የውድድር አደባባዮች ተሰልፈው ድል ማድረግ የተሳናቸውን አትሌቶች የሀገር ፍቅር ስሜት የላቸውም ማለት ይቻላል? ለምን?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ተጣምረው የቀረቡትን ቃላት ተናጠላዊ ፍቻቸውን ከጻፋችሁ በኋላ በምንባቡ ተጣምረው የቀረቡበትን ምክንያት ጻፉ።

ምሣሌ፦

| ቃላት | ተናጠላዊ ፍቺ | በምንባቡ ተጣምረው የቀረቡበት ምክንያት |
|---|---|---|
| ሰላምና ደህንነት | ሰላም ማለት ረብሻ፣ ሁከት ጦርነት የሌለበት ማለት ሲሆን ደህንነት ማለት ደግሞ ጤንነት ወይም በመልካም ሁኔታ ላይ መሆን ማለት ነው። | በጤንነት ወይም በመልካም ሁኔታ ለመኖር ረብሻ፣ ሁከት ጦርነት የሌለበት ሁኔታ አስፈላጊ በመሆኑ ነው። |

| ቃላት | | ተናጠላዊ ፍቺ | ምክንያት |
|---|---|---|---|
| ሀ | ድህነትና ኋላቀርነት | | |
| ለ | መፈቃቀርና መከባበር | | |
| ሐ | መተሳሰብና መረዳዳት | | |
| መ | ሀብትና ንብረት | | |
| ሠ | ዕድገትና ብልፅግና | | |
| ረ | ጠብቀውና ተንከባክበው | | |
| ሰ | መንግሥትና ሕዝብ | | |
| ሸ | ሉዓላዊነትና ነጻነት | | |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋና ሀሳብና ደጋፊ ዝርዝሮች ድርሰት መጻፍ

በሚከተለው ቢጋር ውስጥ ያሉትን ኃይለቃላት በመዘርዘር ሀሳቦች በማስፋፋት ሦስት አንቀጾችን ጻፉ።

ርዕስ
ሌባን ማጋለጥ

↓

አንቀጽ 1
በአንድ አካባቢ ሕዝቡን ያስቸገሩ ሁለት ሌቦች ነበሩ።

↓

አንቀጽ 2
የሌቦቹ ዘረፋ ያስመረረው የአካባቢው ነዋሪ ምሥጢራዊ ስብሰባ በማድረግ ሌቦቹን ለማጋለጥ ወሰነ።

↓

አንቀጽ 3
የሀገር ሽማግሌዎች የአካባቢውን ኗሪ በመጥራት ቀጣዩ ስብሰባ ተጀመረ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## በሀሳብ ቅደምተከተል ዓረፍተነገሮችን ማደራጀት

### ተግባር

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በሀሳብ ተያያዥነታቸው መሠረት በቅደምተከተል ጻፏቸው።

ሀ. ከፊታውራሪ ገበየሁ ሞት በኋላ የጦር አበጋዝነት ስልጣኑን በ1889 ዓ.ም ተረከቡ።

ለ. አፄ ምኒልክ ፊታውራሪን ገና የ18 ዓመት ወጣት ሳሉ ለእልፍኝ አለቅነት ሾሟቸው።

ሐ. ለሀገራቸው ኢትዮጵያ በርካታና አስደናቂ ስራዎችን ሰርተው በተወለዱ በ73 ዓመታቸው በ1919 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለዩ።

መ. ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከአቶ ዲነግዴ በተራና ከእናታቸው ከእመት ኢጄ አመዲና በ1844 ዓ.ም ተወለዱ።

ሠ. የማስተዳደር ጥበብን የተካኑት ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከአደዋ ድል በኋላ የፊታውራሪነት ማዕረግ አገኙ።

ረ. በ1859 ዓ.ም በተጀመረው ሸዋን አንድ አድርጎ የማስተዳደር ዘመቻ የራስ ጎበና ዳጬ ጦር ወደ ጃባትና ማጫ አውራጃ እንዲዘምት ተደረገ።

ሰ. በዚህ ስራ ላይ ውጤታማ ሆነው ስላዩዋቸው ወታደራዊ ነክ ስራዎችን ይሰጧቸው ነበር።

ሸ. ከዚህ ዘመቻ ወቅት ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ከታላቅ እህታቸው ቤት ተሸሽገው እንዳሉ ተማረኩ።

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የሀገር ፍቅር

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የሀገር ፍቅር» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሱትን ሀሳብ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«የሀገር ፍቅር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መጀመሪያ ከመምህራችሁ ጋር በመቀጠል በየግላችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

# መናገር

### በተለያየ ዐውድ መናገር

**ተግባር**

ከሚከተሉት መካከል አንዱን በመምረጥ ለክፍላችሁ ተማሪዎች በዘፈን፣ በመዝሙር ወይም በንግግር አቅርቡ።

ሀ. ስለሀገር ፍቅር የሚዘፈኑ ዘፈኖች

ለ. ስለሀገር ፍቅር የሚዘመሩ መዝሙሮች

ሐ. ስለሀገር ፍቅር የሚነገሩ ምሣሌያዊ አነጋገሮች ወይም አባባሎች

## ሰዋስው

### ስሞች እንደመሙያ ሲገቡ

### ተግባር

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በደብተራችሁ በመጻፍ እንደመሙያ የገቡትን ስሞች አስምሩባቸው።

ምሳሌ፦ እነዚያ ወጣቶች ነርሶች ናቸው።

ሀ. እኔ መምህር ነኝ።

ለ. ያ ፎቅ ነው።

ሐ. ይህ ሐይቅ ነው።

መ. እሷ ነጋዴ ነች።

ሠ. እነዚያ ተማሪዎች ናቸው።

ረ. ያቺ ልጅ ተመራማሪ ሆነች።

# የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እየ-ተንከባከብ-ኡ | እየተንከባከቡ |
| ለ | እንዲ-ገነቡ-ል-ኣቸው | እንዲገነቡላቸው |
| ሐ | የሚ-ያስፈልግ-ኣቸው-ን | የሚያስፈልጋቸውን |
| መ | ጉዳት-ኧኛ-ኦች | ጉዳተኞች |
| ሠ | የሚ-ያበረክት-ኧው | የሚያበረክተው |
| ረ | በ-ማህበረ-ሰብ-ኦች | በማህበረሰቦች |
| ሰ | ወላጅ-ኦች-ኣቸው-ን | ወላጆቻቸውን |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት አቀላጥፋችሁ አንብቧቸው።

ሀ. ያሚላሉ
ለ. ፅኑ
ሐ. ጧሪ
መ. እርስበርስ
ሠ. በማቋቋም
ረ. አርአያነት
ሰ. አስተዋጽዖ
ሸ. ግጭቶችን
ቀ. ተዓማኒነት
በ. ጥናትና ምርምር
ተ. መሠረታዊ ፍላጎት
ቸ. ተመራማሪዎች

# ማንበብ


## ማህበረሰብን ማገልገል

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

በቢጋር ሠንጠረዡ ውስጥ ባለው መነሻ ሀሳብ መሠረት በዙሪያው ያሉትን ክቦች አሟሉ።




## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ቀጥሎ «ማህበረሰብን ማገልገል» በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ጸሐፊው/ዋ ለምን ዓላማ እንደጻፈው/ችው ለማወቅ ትኩረት ሰጥታችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ማህበረሰብን ማገልገል

በኢትዮጵያ በርካታ ሰዎች ጠቃሚ ተግባራትን በማከናወን የማህበረሰብ አገልግሎት ይሰጣሉ። እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎች በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ላሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍና እንክብካቤ ያደርጋሉ። አዳዲስ አሠራሮችንና ሀሳቦችን በማመንጨት የሰዎችን የኑሮ ሁኔታ ያሻሽላሉ። በማህበረሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን በውይይት ይፈታሉ። በአካባቢያቸው የልማት ሥራዎች ላይ ንቁ ተሣታፊዎች ይሆናሉ። የተለያዩ ሥራዎችን የመምራትና የማስተባበር ኃላፊነት ሲሰጣቸው በቅንነትና በታማኝነት ለሕዝብ ጥቅም ጠንክረው ይሠራሉ።

### በጎ ተግባራትን መፈፀም

የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች በአስቸጋሪ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች በመርዳት ረገድ ጠቃሚ ሥራዎችን ይሠራሉ። ለምሣሌ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናትን በማሣደግ ማህበራዊ ችግሮችን ይፈታሉ። የሕፃናቱን መሠረታዊ ፍላጎት ያሟላሉ፤ የሕፃናት ማሣደጊያ ተቋማትን ይከፍታሉ፤

የትምህርት መሣሪያዎችን በማሟላት እንዲማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። አሣዳጊ የሌላቸውን ሕፃናት የወላጅን ያህል እየተንከባከቡ ያሣድጋሉ።

ማህበረሰብን የማገልገል ፅኑ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍ ያደርጋሉ።

ማህበረሰብን የማገልገል ፅኑ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍ ያደርጋሉ። የሥራ፣ የመማሪያና የመኖሪያ አካባቢያቸውን ምቹ የማድረግ ሥራዎችን ይሠራሉ። ጧሪ ለሌላቸው አረጋውያን የመጠለያ ተቋም ያቋቁማሉ። ቤቶቻቸውን በማደስና ጤንነታቸውን በመንከባከብ ይረዳሉ። የኤች.አይ.ቪ. ህሙማንን ይንከባከባሉ። በኢትዮጵያ እነዚህን በመሳሰሉት አርአያነት ባላቸው ተግባራቸው ከሚታወቁት መካከል አበበች ጎበና በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። ስለዚህ ማህበረሰቡን ማገልገል ከራስ ደስታ በላይ ለሀገር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም።

## ኃላፊነትን መወጣት

የተለያዩ ሥራዎችን ለመምራትና ለማስተባበር ኃላፊነት የሚሰጣቸው ሰዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ግላዊና ማህበራዊ ዕድገትን ያመጣሉ። እነዚህ ሰዎች ሥራቸውን በብቃት ስለሚወጡ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተዓማኒነት ይኖራቸዋል። በሰዎች ይወደዳሉ። በዚህም ስለሚበረታቱ የማህበረሰቡን ኑሮ ይለውጣሉ። ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የሕዝቦችን ጥቅም ያስቀድማሉ። ስለዚህ ማህበረሰብን በቅንነትና በታማኝነት ስለሚያገለግሉ የማህበረሰቡ ሕይወት ይለወጣል።

ማህበረሰብን ለማገልገል ሰዎች አዳዲስ ሀሳቦችንና አሠራሮችን ያመነጫሉ። በተለይም ልምድ ያላቸውና የተማሩ ሰዎች ጥናትና ምርምር በማድረግ የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ይሠራሉ። ዘመናዊ አሠራርን ያፈልቃሉ። ኋላቀር አሠራሮችን በመለወጥ ቀልጣፋ፣ ጊዜንና ጉልበትን ቆጣቢ የአሠራር ስልት ይፈጥራሉ። በዚህም ማህበረሰቡ ከፍተኛ ምርት እንዲያመርት ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋሉ። ይህ ተግባራቸው ብዙ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

ማህበረሰብን ለማገልገል ሰዎች አዳዲስ ሀሳቦችንና አሠራሮችን ያመነጫሉ።

ማህበረሰብን ወይም ሀገርን ለማገልገል በተለያዩ የልማት ሥራዎች የሚሳተፉ ሰዎች አሉ። ለብዙ ሰዎች በየአካባቢያቸው የጤና ተቋማት እንዲገነቡላቸው

የገንዘብና የጉልበት ድጋፍ ያደርጋሉ። በዚህም እናቶችና ሕፃናት በቅርብ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ። ሕፃናት በአካባቢያቸው ትምህርት እንዲያገኙ ትምህርትቤቶችን ለመገንባት በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ይሳተፋሉ። ማህበረሰቡ በተላላፊ በሽታዎች እንዳይጎዳ በየአካባቢው የፅዳት ሥራ እንዲከናወን ትምህርት ይሰጣሉ። መንገዶች፣ ድልድዮችና ሌሎች መሠረተልማቶች እንዲሟሉ የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ። በዚህም የሰዎችን ኑሮ ለማሻሻልና የሀገር ዕድገትን ለማምጣት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

## የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶችና የታዋቂ ሰዎች ተግባራት

የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶችና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ደግሞ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመፍታት ረገድ ጠቃሚ አገልግሎት ይሰጣሉ። የግጭቶችን መነሻዎች በአግባቡ በመረዳት በውይይት ይፈታሉ። በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ፍቅርና መረዳዳት እንዲኖር ጥረት ያደርጋሉ። የተበደሉትን ያስክሳሉ። እርስበርስ በመካሰስ ጉልበትና ጊዜ እንዳይባክን አጥብቀው ይሠራሉ። በየአጋጣሚው በሰዎች መካከል ያለውን ጠንካራ ግንኙነት የሚፈታተኑ ችግሮችን ገና ከመነሻቸው ይከላከላሉ። አድሎን፣ ሥርቆትንና ዝርፊያን እንዲሁም የተለያዩ የወንጀል ተግባራትን አጥብቀው ይዋጋሉ።

> **የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ሰዎች ትውልድን በሥነምግባርና በሞራል የማነፅ ተግባራትን ይፈፅማሉ።**

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በርካታ ሰዎች፣ የሕዝቦችን ኑሮ በማሻሻል፣ ማህበራዊ ችግሮችን በመፍታት፣ ደጋፊ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች በመርዳት ጠቃሚ ሥራ ይሠራሉ። እንዲሁም ዘመናዊ አሠራርን በማፍለቅ፣ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በማጠናከርና በልማት ሥራዎች በመሳተፍ ማህበራዊ አገልግሎት ይሠጣሉ። ሰዎች እነዚህንና መሰል በጎ ተግባራትን በማከናወን የማህበረሰብ ሕይወትን ይለውጣሉ። ይህ ደግሞ ከግለሰብ አልፎ የሀገር ዕድገትን ያፋጥናል። ስለዚህ እነዚህንና መሠል ተግባራትን በማከናወን ማህበረሰብን ማገልገል ያስፈልጋል።

(ኤፌዴሪ ትሚ። 2003። *ሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት።* ገጽ 62-67 መነሻነት የተዘጋጀ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

«ማህበረሰብን ማገልገል» የሚለውን ምንባብ ለመረዳት ያገዟችሁን ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በማዘጋጀት ርስበርሳችሁ ተጠያየቁ።

## ተግባር 2

በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የበጎ አድራጎት ሥራ መሥራት ፋይዳው ምንድን ነው?

ለ. የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ስለማህበረሰብ አገልግሎት ያለው/ያላት አመለካከት ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ተመራማሪዎች ከሚሰጡትና የሀገር ሽማግሌዎች ከሚሰጡት ማህበረሰባዊ አገልግሎት የተሻለው የትኛው ይመስላችኋል? ለምን?

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### የቃላትን ተቃራኒ ፍቺ በዓረፍተነገር መጠቀም

## ተግባር

ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒያቸውን በክፍት ቦታዎች በማስገባት ዓርፍተነገሮቹን አሟሉ።

ምሳሌ፣ አንተ ቀልጣፋ ከሆንክ የ _______ ሰዎች አሠራር ያናድድሃል።

አንተ ቀልጣፋ ከሆንክ የ አዝጋሚ ሰዎች አሠራር ያናድድሃል።

ሀ. መቼ ነው ኋላቀር አሠራርን ትተህ _______ አሠራርን የምትከተለው።

ለ. እኔ ማህበረሰባዊ አስተሳሰብን ስከተል እሱ ደግሞ _______ አስተሳሰብን ይከተላል።

ሐ. እኛ ለአካባቢ ልማት ስንነሳ፣ እነሱ ለ _______ ተነሱ።

መ. አድሏዊነት የሀገር ውድቀት ሲያስከትል _______ ግን ብልፅግናን ያመጣል።

ሠ. በኢትዮጵያ በርካታ ሰዎች ማህበረሰባዊ አገልግሎት ቢሰጡም _______ ሰዎች ደግሞ ለግል ጥቅማቸው ብቻ ይሯሯጣሉ።

ረ. የሀገር ሽማግሌዎች የወጣቶችን ሞራል ለማነፅ ሲጥሩ አንዳንዶች ግን የወጣቶችን ሞራል _______ ይጥራሉ።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የሕይወት ታሪክ መጻፍ

#### ተግባር

በ1ኛ ሳምንት 2ኛ ቀን የጻፋችኋቸውን አንቀጾች በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ለጋዜጣ ወይም ለመጽሔት ህትመት እንዲበቃ በማድረግ እንደገና ጻፉ።

- የአንቀጽ ቅርጽ የያዙ መሆናቸው፣
- ቃላት ያለምንም የፊደላት ግድፈት መጻፋቸው፣
- ሥርዓተነጥቦች በተገቢው ቦታ መግባታቸው፣
- የአንቀጹን ባህሪያት ያሟሉ መሆናቸው፣

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ዓረፍተነገሮችን በሀሳብ ቅደምተከተል ማደራጀት

#### ተግባር

በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን ዓረፍተነገሮች በሀሳብ ቅደምተከተል አደራጅታችሁ እንደገና ጻፏቸው።

ሀሳቡን በማስረጃ፣ በምሳሌዎችና በሌሎች ተጨማሪ ስልቶች አማካኝነት ማብራራት የግድ በሚሆንበት ጊዜ የአንቀጹ መጠን ይጨምራል። ስለዚህ የአንቀጹ መጠን የሚወሰነው በሚቀርበው ፍሬነገር ባህሪ ነው ማለት ነው። በተቃራኒው የሚብራራው ሀሳብ ውስን ከሆነና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ወይም ምሳሌዎችን መጨመር ካላስፈለገ መጠኑ አነስተኛ ይሆናል። አንድ አንቀጽ አንድ ሀሳብ ብቻ የሚቀርብበት የድርሰት አካል በመሆኑ መጠኑ የሚወሰነው በቀረበው ፍሬነገር ነው።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ማህበረሰብን ማገልገል

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

«ማህበረሰብን ማገልገል» ከሚለው ምንባብ የመጀመሪያ አንቀጽ የምታስታውሷቸውን ሀሳቦች ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

«ማህበረሰብን ማገልገል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚይዙላችሁ ደቂቃ መሠረት ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

#### ተግባር

ከሚከተሉት ሀሳቦች አንዱን መርጣችሁ ንግግር አቅርቡ።

ሀ. እናንተ በትምህርትቤትም ሆነ በአካባቢያችሁ ምን ምን የበጎ አድራጎት ተግባራት እንዳከናወናችሁ ዘርዝር አድርጋችሁ ተናገሩ።

ለ. በአካባቢያችሁ ያሉ ሰዎች ስለሚያከናውኗቸው የበጎ አድራጎት ተግባር ግለጹ።

## ሰዋስው

ጠቋሚ መስተኣምርና መሙያ

### ተግባር 1

የሚከተሉትን መስተኣምሮች በክፍት ቦታው ላይ በማስገባት አንቀጹን የተሟላ አድርጉ።


| |
|---|
| እነዚያ፣ እነሱ፣ እኛ፣ ያ፣ እሱ፣ ይህ፣ ይቺ፣ እሷ፣ ያቺ |

ያን ጊዜ _______ ተማሪ አላጠፋም ነበር። ሆኖም አጥፍቷል በማለት _______ ሊቀጣው ፈለገ። ስለሁኔታው ትንሽ ከተነጋገሩ በኋላ _______ ልጆች ስለልጁ ለመምህሩ የተናገሩት ስህተት እንደነበር ታወቀ። _______ ትናንት ያገኘናት ልጅም የልጁን ትክክለኛነት በሚገባ አውቃ ስለነበር _______ የተናገሩት ስህተት እንደሆነ ደግማ ለመምህሯ ገለፀች። መምህሩም _______ ዓይነት ነገር ለእናንተ ጥሩ አይደለም በማለት መከራቸው።

### ተግባር 2

ቀጥሎ ከቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በትክክል በማደራጀትና ስሞችን እንደመሙያ በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

| | | |
|---|---|---|
| ይህ<br>ያ<br>እነዚህ<br>ያቺ<br>እነሱ<br>ይቺ | ናቸው<br>ነው<br>ነች | ወጣት መምህር<br>ወንዝ<br>ተማሪዎች<br>መጻሕፍት |



# ተላላፊ በሽታዎች

# ምዕራፍ 9

## ተላላፊ በሽታ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ሊ.ያስመልስ-ኣቸው | ሊ.ያስመልሳቸው |
| ለ | ከ-ሰጠ-ኣችሁ-ኣቸው | ከሰጣችኋቸው |
| ሐ | ቦ-ቬ.-ስ | ቦቬ.ስ |
| መ | ራ-ይ-ኖ | ራይኖ |

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በፍጥነት አንብቡ።

| ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|
| ትክትክ | ተቅማጥ | የወባ ትንኝ | ራስምታት | የሕመምተኞችን |
| መጎልጎል | አባላዘር | ብርድ ብርድ | ትላትሎች | ባክቴሪያዎች |
| በሰውነታቸው | ባንቡሌ | ማንቀጥቀጥ | ጨብጥ | ልንከላከላቸው |
| እንባ ማቅረር | ከመሆናቸውም | መንገዶቻቸውን | እየተባባሰ | ልንቆጣጠራቸው |

# ማንበብ


## ተላላፊ በሽታዎች

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

«ተላላፊ በሽታዎች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ከቀደመ ዕውቀታችሁ በመነሳት የቢጋር ሠንጠረዡን አሟሉ።




### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ «ተላላፊ በሽታዎች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በቅድመንባብ ተግባራት ላይ ከሰጣችኋቸው መልሶች ጋር በማገናዘብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ተላላፊ በሽታዎች

ተላላፊ በሽታዎች ከሕመምተኞች ወደጤነኞች በተለያዩ መንገዶች የሚተላለፉ የበሽታ ዓይነቶች ናቸው። ተላላፊ በሽታዎች ከሚባሉት መካከል ኤች.አይ.ቪ./

ኤድስ፣ ቲቢ፣ ጉንፋን፣ ማጅራት ገትር፣ ትክትክ፣ ተቅማጥ፣ ወባና የአባላዘር በሽታዎች ጥቂቶቹ ናቸው።

ተላላፊ በሽታዎች መነሻቸው ቫይረስ፣ ባክቴሪያ ወይም ትላትሎች ናቸው። ለምሣሌ የማጅራት ገትር በሽታ መንስኤ ቫይረስ ወይም ባክቴሪያ ሊሆን ይችላል። የአየር ንብረቱ ሞቃታማና ነፋሻማ በሚሆንበት ወቅት በባክቴሪያ አማካይነት የማጅራት ገትር በሽታ ይከሰታል። በተለይም የካቲት፣ መጋቢትና ሚያዝያ ባክቴሪያው የሚራባባቸው አመቺ ወራት ናቸው። በሽታው የሕመምተኞችን የራስ ቅል በማቁሰል ለከፋ ችግር ይዳርጋል። ማጅራት ገትር የሚተላለፈው በትንፋሽ በመሆኑ ብዙ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ያጠቃል።

**ማጅራት ገትር የሚተላለፈው በትንፋሽ በመሆኑ ብዙ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ያጠቃል።**

እንደማጅራት ገትር ሁሉ ትክትክ በባክቴሪያ የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ሲሆን ዕድሜያቸው ከ1-5 ያሉ ሕፃናትን ያጠቃል። በሽታው በመጀመሪያ ጉንፋን ይመስልና ለተከታታይ ቀናት እየተባባሰ ይሄዳል። በሳል ጊዜም የፊት መጥቆር፣ የዓይን እንባ ማቅረር፣ እንዲሁም የምላስ መጎልጎል ምልክቶች ይታያሉ። ሕመምተኞች ስለሚስሉ በተደጋጋሚ ሊያስመልሳቸው ይችላል። በሽታው ከሰው ወደሰው በትንፋሽ አማካይነት ይተላለፋል።

ተቅማጥ በባክቴሪያ አማካይነት በተበከለ ምግብና ውኃ ይከሰታል። የተቅማጥ በሽታ በተለይ ሕፃናትን ያጠቃል። በተቅማጥ በሽታ የተያዙ ሕፃናት በሰውነታቸው ውስጥ ያለው ውኃ በተቅማጥና በትውከት ምክንያት ያልቃል። በተቅማጥ በሽታ የተያዙ ሰዎች የሆድ ቁርጠት፣ ራስምታት ወይም ትኩሳት ይኖርባቸዋል። በሽታው በንፅህና ጉድለት ምክንያት በንክኪ ሊተላለፍ ይችላል።

**ተላላፊ በሽታዎች በተለያዩ መንገዶች ከሰው ወደሰው ስለሚተላለፉ በተወሰነ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ይጎዳሉ።**

ጥንቃቄ በጎደለው የግብረሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ተላላፊ በሽታዎችም በርካታ ናቸው። ከነዚህም መካከል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፣ ጨብጥ፣ ቂጥኝ፣ ባንቡሌና የመሳሰሉት ይገኙበታል። የአባላዘር በሽታዎች የጤና ጠንቆች ከመሆናቸውም በላይ ከማህፀን ውጪ እርግዝናና፣ መሃንነትን ያስከትላሉ፤ የሆድ ዕቃ አካባቢ፣ የአዕምሮ፣ የልብና የቆዳ ህመሞችንም ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከተላላፊ በሽታ ዓይነቶች መካከል የተወሰኑትን የበሽታ ዓይነቶች፣ ምልክቶችና መተላለፊያ መንገዶች ለአብነት ከሠንጠረዡ ማየት ይቻላል።

## የተላላፊ በሽታ ዓይነቶች፣ ምልክቶችና መተላለፊያ መንገዶች

| የበሽታ ዓይነት | የበሽታው ምልክቶች | መተላለፊያ መንገዶች |
|---|---|---|
| ኤችአይ ቪ/ ኤድስ | • ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥ<br>• የክብደት መቀነስ<br>• ሣል | • ጥንቃቄ የጎደለው የግብረሥጋ ግንኙነት<br>• የደም ንክኪ |
| ቲቢ | • ከ15 ቀን በላይ የሚቆይ ሳል፣ ደም የቀላቀለ ወይም ያልቀላቀለ አክታ ወይም ደረቅ ሳል፣ | • በትንፋሽ<br>• «ማይኮ ባክቴሪየም ቦቪስ» በተባለ ባክቴሪያ በተያዙ እንስሳት ወተት |
| ጉንፋን | • ማስነጠስ፣ ሳል፣ ቀጠን ያለ ፈሳሽ ከአፍንጫ መውጣት፣ ብርድብርድ ማለት | • በንክኪ ወይም በትንፋሽ በሚተላለፍ ቫይረስ (ራይኖ) |
| ማጅራት ገትር | • ከፍተኛ ራስ ምታት፣ ትኩሣት የአንገትና የማጅራት ሕመም | • በትንፋሽ በሚተላለፍ ቫይረስና ባክቴሪያ |
| ተቅማጥ | • የማያቋርጥ ተቅማጥ፣ ትውከት፣ ትኩሳት | • በተበከለ ምግብና ውኃ<br>• በንፅህና ጉድለት ወይም በንክኪ በሚተላለፍ ባክቴሪያ |
| የአባላዘር በሽታ | • ከማህፀን ወይም ከብልት አካባቢ የቁስለትና የሕመም ስሜት | • ጥንቃቄ በጎደለው የግብረሥጋ ግንኙነት<br>• በንክኪ በሚተላለፍ ባክቴሪያ |
| ወባ | • ማንቀጥቀጥ፣ ትኩሳት፣ ቅዠት | በሴቷ የወባ ትንኝ ንክሻ |

በአጠቃላይ ተላላፊ በሽታዎች በአብዛኛው በወረርሽኝ ወይም በጥንቃቄ ጉድለት የሚከሰቱ በመሆናቸው በርካታ ሰዎችን በአጭር ጊዜ ያጠቃሉ። ስለሆነም መተላለፊያዎችን ጠንቅቀን በመገንዘብ ልንከላከላቸውና ልንቆጣጠራቸው ይገባል።

(አዲስ አድማስ ድረገጽ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ በቫይረስ ብቻ የሚመጣ በሽታ የቱ ነው?

ሀ. ቲቢ.　　ለ. ጉንፋን　　ሐ. ተቅማጥ　　መ. ወባ

2. የማንቀጥቀጥ፣ የማቃዠት፣ የማቅለሽለሽና የማስመለስ ምልክቶች የሚታዩባቸው ሰዎች በምን በሽታ የተያዙ ይመስላችኋል?

ሀ. በኤች አይ ቪ.　　ሐ. በማጅራት ገትር

ለ. በቲቢ.　　መ. በወባ

3. የ«ትክትክ» በሽታ የሚያጠቃው በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ሰዎች ነው?

ሀ. ከ6-9　　ለ. ከ1-5　　ሐ. ከ15-20　　መ. ከ10-15

4. ከሚከተሉት መካከል የተቅማጥ በሽታ መተላለፊያ መንገድ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የንፅህና ጉድለት　　ሐ. ቫይረስ

ለ. የትንኝ ንክሻ　　መ. ትንፋሽ

## ተግባር 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ጻፉ።

ሀ. የማጅራት ገትር በሽታ የትኛውን የአካል ክፍል ያጠቃል?

ለ. በባክቴሪያ አማካይነት የሚመጡ በሽታዎችን ዘርዝሩ።

ሐ. የትክትክ በሽታ ከጉንፋን በሽታ የሚለየው በምንድን ነው?

መ. በኤች.አይ.ቪ./ኤድስና በአባለዘር በሽታ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ረ. በአካባቢያችሁ በጣም ተደጋግሞ የሚከሰት ተላላፊ በሽታ ምንድን ነው? ይህን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የአካባቢያችሁ ኗሪዎች ምን ማድረግ ያለባቸው ይመስላችኋል?

# 2ኛ ቀን

## ቃላት

### በጥንድ ቃላት መካከል ያለ የፍቺ ልዩነት

#### ተግባር

ጥንድ ጥንድ ሆነው በቀረቡት ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት በዓረፍተነገር አሳዩ።

ምሣሌ፡- በሽታ ⟶ በሽተኛ

- ተላላፊ <u>በሽታ</u> በአንድ ጊዜ በርካታ ሰዎችን ሊያጠቃ ይችላል። (ሕመም)
- የቲቢ <u>በሽተኛ</u> ከ15 ቀን በላይ ደረቅ ሳል የመሳል ምልክት ይታይበታል። (ታማሚ)

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጠንቅ<br>ጠንቀኛ | ሐ. ጤና<br>ጤነኛ | ሠ. ልብ<br>ልበኛ |
| ለ. ቁስል<br>ቁስለኛ | መ. ምላስ<br>ምላሰኛ | ረ. ችግር<br>ችግረኛ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ሀሳብን በሠንጠረዥ ማስፈር

#### ተግባር 1

በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች በሠንጠረዥ ግለጹ።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ የጤና ተቋማት ውስጥ የማዋለድ አገልግሎት ይሰጣል። በዚህ መሠረት በ2003 ዓ.ም. 87,319 እናቶች ወደጤና ተቋማት ሄደው 96ቱ ሲሞቱ ሌሎቹ በሰላም ተገላገለዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0.10 ነው። እንዲሁም በ2004 ዓ.ም. ወደጤና ተቋማት ለመውለድ ከሄዱት 85,793 እናቶች መካከል 151 እናቶች በወሊድ ምክንያት ህይወታቸው አልፏል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0.13 ነው። በ2005 ዓ.ም. ደግሞ 117,174 እናቶች ወደጤና ተቋማት ለወሊድ ሄደው 117 እናቶች ህይወታቸው አልፏል። ይህም በመቶኛ 0.10 ነው።

(ምንጭ፡- አብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ 2006 ዓ.ም.። የጤና ፌስቲቫል ልዩ መጽሔት፣ ገጽ 14)

#### ተግባር 2

በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የጤና ተቋም በመሄድና የጤና ባለሙያዎችን በመጠየቅ የተላላፊ በሽታዎችን የሥርጭት መጠን የሚገልጽ በሠንጠረዥ የተደገፈ ዘገባ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ ፊደላትን ሳትገድፉና ተገቢውን ሥርዓተነጥብ በተገቢው ቦታ በመጠቀም ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ተላላፊ በሽታዎች

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

«ተላላፊ በሽታዎች» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ የምታስታውሷቸውን ቁልፍ ሀሳቦች ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

«ተላላፊ በሽታዎች» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያለውን ሥንጠረዥ ድምፅ በማሰማት በትክክል አንብቡ።

# ማዳመጥ

## የጉንፋን በሽታ

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰዎች በጉንፋን በሽታ መያዛቸውን ልናውቅ የምንችለው በምንድን ነው?

ለ. ስለቫይረስ የምታውቁትን ተናገሩ።

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

«የጉንፋን በሽታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በማዳመጥ ቀጥሎ በቀረቡት ንዑሳን ርዕሶች የተካተቱትን ዋናዋና ሀሳቦች በማስታወሻ ያዙ።

ሀ. የራይኖ ቫይረስ መለያ ባህርያት

ለ. የጉንፋን በሽታ መተላለፊያዎች

ሐ. የጉንፋን በሽታ ምልክቶች

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አንድን ሰው አንድ ጊዜ የያዘው የጉንፋን ቫይረስ መልሶ ሊይዘው የማይችለው ለምንድን ነው?

ለ. የጉንፋን በሽታ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. የጉንፋን በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

መ. ሰዎች ዕድሜያቸው እየጨመረ በሄደ ቁጥር በጉንፋን የመያዝ ዕድላቸው እየቀነሰ የሚሄደው ለምንድን ነው?

ሠ. በጉንፋን በሽታ እንዳንያዝ ምን ማድረግ ያለብን ይመስላችኋል?

# ሰዋስው

## ጊዜ

### ማስታወሻ

ጊዜ፣ አንድ ድርጊት መቼ እንደተፈጸመ ወይም መቼ እንደሚፈጸም የሚገልጽ የግስ ባህርይ ነው። ጊዜ በሶስት ይከፈላል። ክፍሎቹም የአሁን፣ የኃላፊና የትንቢት ጊዜ ይባላሉ።

- የአሁን ጊዜ የሚባለው ዓረፍተነገሩ በሚነገርበት ጊዜ የሚፈጸም ድርጊትን ይገልጻል።

ምሣሌ፣ ኤደን አሁን ደብዳቤ ትጽፋለች።

- የኃላፊ ጊዜ አንድ ድርጊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ያመለክታል።

ምሣሌ፣ አብደላ ትናንት መኪና ጠገነ።

- የትንቢት ጊዜ አንድ ድርጊት ገና ያልተፈጸመና ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ይገልጻል።

ምሣሌ፣ ህሊና ነገ አዲስአበባ ትሄዳለች።

## ተግባር

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች የአሁን ጊዜ፣ የኃላፊ ጊዜና የትንቢት ጊዜ በማለት ለዩ።

ሀ. ትናንት በሠራው መጥፎ ሥራ እጅግ አዘነ።

ለ. እነሱ ነገ ወደሀገራቸው ይሄዳሉ።

ሐ. አስቴር ትናንት እዚያ ነበረች።

መ. ነብያት አሁን መጽሐፍ ታነባለች።

ሠ. አያሌው ዛሬ ጧት መረብ ኳስ ተጫወተ።

ሰ. እኔ በኋላ እዚያ ተራራ ላይ እወጣለሁ።

ሰ. ዘምዘም አሁን ዜና ታዳምጣለች።

ሸ. ሙስጠፋ ከነገወዲያ የትምህርት መሣሪያዎችን ይገዛል።

ቀ. ያዕቆብ ትናንት ብዙ በራሪ ወረቀቶችን አነበበ።

በ. ሂኖክ አሁን ጫማ ይሰፋል።

# ማንበብ

## የቲቢ በሽታ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ካነበባችሁ በኋላ፣ ትክክል ከሆኑ «እውነት»፣ ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «ሀሰት» በማለት ምክንያት እያቀረባችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የቲቢ በሽታ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እንጂ በሌሎች ሀገሮች ጠፍቷል።

ለ. «ቲቢ» የሚለው አህፅሮተቃል «ቱበርክሎሲስ» ማለት ነው።

ሐ. ቲቢ ሳንባን እንጂ ሌሎች የአካል ክፍሎችን አያጠቃም።

መ. የቲቢ በሽታ በሕክምና ይድናል።

### የማንበብ ሂደት


**ተግባር**

«የቲቢ በሽታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በየንዑስ ርዕሶቹና በግራፉ የቀረቡትን ሀሳቦች አቀናጅታችሁ በመረዳት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የቲቢ በሽታ

### የቲቢ በሽታ ሥርጭትና ችግሮቹ

የቲቢ በሽታ የዓለም ሕዝቦች የጤና ችግር እንደሆነ የዓለም የጤና ድርጅት እ.አ.አ. በ2012 ያወጣው መረጃ ያሳያል። በየዓመቱ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በቲቢ በሽታ ይጠቃሉ። ቲቢ በገዳይነቱ ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ቀጥሎ በ2ኛ ደረጃ የሚታወቅ በሽታ ሆኗል። ኢትዮጵያም በዓለም በከፍተኛ ደረጃ በቲቢ በሽታ ከተጠቁ 22 ሀገሮች አንዷ ናት። በተጨማሪም የፀረቲቢ መድኃኒቶችን የተላመደ ቲቢ በከፍተኛ ደረጃ ከሚገኝባቸው 27 ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ እንደምትገኝ የሚጠቅሱ መረጃዎች አሉ። ለዚህ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተወሰኑ ዓመታት የነበረውን የቲቢ ሥርጭትና ክትትል የሚያሣየውን ግራፍ ማየት ይቻላል።




የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 2006 ዓ.ም በጀት አመት የዕቅድ ክንውን ሪፖርት

## የቲቢ በሽታ መነሻና መተላለፊያ መንገዶች

የቲቢ በሽታ በአብዛኛው በዓይን በማይታይ «ማይክሮባክቴርየም ቱበርክሎሲስ» በተባለ ባክቴሪያ አማካይነት ይከሰታል። የቲቢ በሽታ በአብዛኛው ሳንባን ያጠቃል። የቲቢ ሕመምተኞች ሲስሉ፣ ሲያነጥሱና ሲናገሩ የበሽታው አምጪ የሆነው ባክቴሪያ ከታማሚዎች ሳንባ ይወጣል። ከዚያ በቀጥታ በትንፋሽ ወይም በአየር አማካይነት ወደጤነኛ ሰዎች የመተንፈሻ አካል ሲገባ በሽታው ይተላለፋል። በቂ የአየር ዝውውር በሌለባቸው ክፍሎች ተፋፍጎ መኖር ለቲቢ በሽታ መስፋፋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። በተጨማሪም በሽታው «ቦቪስ» በተባለ ባክቴሪያ ከተያዙ የቤት እንስሳት የሚገኝ ወተት ሳይፈላ ከተጠጣ ወደሰዎች በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል።

## የቲቢ በሽታ ዓይነቶችና ምልክቶች

ቲቢ በአብዛኛው ሳንባን የሚያጠቃ ቢሆንም ከሳንባ ውጪም ሌሎችን የሰውነት ክፍሎች ያጠቃል። በዚህ ምክንያት በሽታው የሳንባ ቲቢና ከሳንባ ውጪ የሆነ የቲቢ በሽታ በመባል በሁለት ይከፈላል። የሳንባ ቲቢ የሚያጠቃው ሳንባን ብቻ ሲሆን የተለያዩ ምልክቶችም አሉት። የሳንባ ቲቢ ዋናው ምልክት ሁለት ሣምንታትና ከዚያ በላይ የዘለቀ ሳል ነው። ሳሉ አክታ ያለው፣ ደም የቀላቀለ ወይም ያልቀላቀለ ወይም ደረቅ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም በደረት አካባቢ የውጋት ስሜት፣ መጠነኛ ትኩሳት፣ በሌሊት ጊዜ ማላብ፣ የሰውነት ክብደት መቀነስ፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስና ድካም የበሽታው ምልክቶች ናቸው።

ከሳንባ ውጭ ያሉ የቲቢ በሽታዎች ደግሞ እንደሚጠቃው የአካል ክፍል የተለያዩ ናቸው። የአጥንትና የመገጣጠሚያ ቲቢ፣ በአንገት አካባቢ ያሉ ዕጢዎች ቲቢ፣ የአንጀት ቲቢ፣ የአንጎል ቲቢና የመሳሰሉት ከሳንባ ውጭ የሚከሰቱ የቲቢ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ የቲቢ ዓይነቶች የተለያዩ ምልክቶች አሏቸው። ለምሣሌ በአንገት አካባቢ ያሉ ዕጢዎች ቲቢ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድና የሕመም ስሜት የሌለው የዕጢ እብጠት ይፈጥራል። በሂደትም ዕጢዎቹ እርስበርስ የመያያዝና መግል መሣይ ፈሳሽ ነገር ያሣያሉ። ሌሎችም የቲቢ ዓይነቶች እንደተጠቃው የሰውነት ክፍል የተለያዩ ምልክቶች አሏቸው። ከሳንባ ቲቢ ውጭ ያሉትን የቲቢ በሽታዎች ለየት የሚያደርጋቸው እንደሳንባ ቲቢ ተላላፊ አለመሆናቸው ነው።

## የቲቢ በሽታ ሕክምና

የቲቢ ህሙማን የሚታዘዝላቸውን መድኃኒት በተገቢው መውሰድ ከቻሉ በቀላሉ ይድናሉ። ህሙማኑ እንዲወስዱ የታዘዘላቸውን መድኃኒት ሳያቋርጡ መውሰድ አለባቸው። ሕክምናው ከተቋረጠ ግን በሽታው በፊት ከነበረው በላይ ይባባሳል። በተጨማሪም የበሽታ መንስኤ የሆነው ህዋስ የፀረቲቢ መድኃኒቶችን ይለማመዳል። ከዚያም በመደበኛው የቲቢ ሕክምና ዘዴ መፈወስ የማይቻል የቲቢ ዓይነት

ይፈጥራል። ስለሆነም በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን በአግባቡ በመውሰድ ከበሽታው ሙሉ በሙሉ መዳን ያስፈልጋል።



በአጠቃላይ የቲቢ በሽታ በርካታ ሰዎችን በመጉዳት ላይ ያለ ተላላፊ በሽታ በመሆኑ ሁላችንም አስቀድመን ልንከላከለው ይገባል። የመኖሪያ ቤቶች፣ አዳራሾች፣ ቢሮዎች፣ መማሪያ ክፍሎች ወዘተ. አየር በበቂ ሁኔታ እንዲዘዋወርባቸው ማድረግ ተገቢ ነው። የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች፣ ታክሲዎች ወዘተ. በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖራቸው መስኮቶቻቸው መከፈት አለባቸው። እንዲሁም ሰዎች በሚስሉበትና በሚያነጥሱበት ጊዜ አፍና አፍንጫቸውን በመሸፈን በሽታው እንዳይስፋፋ በማድረግ መተባበር ይኖርባቸዋል። ሕክምና የጀመሩ ሰዎችም እስኪጨርሱ ድረስ ተከታትሎ ማሳከም ያስፈልጋል። በተጨማሪም የእንስሳትን ወተት አፍልቶ በመጠጣትና ጥሬ ሥጋን አብስሎ በመመገብ እንዲሁም በየጊዜው ምርመራ በማድረግ የቲቢ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ይቻላል።

(ከአዲስ አድማስ ድረገጽ። ታህሣሥ 1/2005። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ጻፉ።

1. ከቲቢ በሽታ ሙሉ በሙሉ ከተፈወሱት መካከል በመቶኛ ከፍተኛው ቁጥር የታየው በየትኛው ዓመት ነው?

   ሀ. 2003 ዓ.ም
   ሐ. 2005 ዓ.ም
   ለ. 2004 ዓ.ም
   መ. 2006 ዓ.ም

2. የቲቢ በሽታ ህክምና ከወሰዱት መካከል አነስተኛ ቁጥር የታየው በየትኛው ዓመት ነው?

   ሀ. 2003 ዓ.ም
   ሐ. 2005 ዓ.ም
   ለ. 2004 ዓ.ም
   መ. 2006 ዓ.ም

3. ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ በምርመራ የቲቢ በሽታ ከታየባቸው ብልጫ የሚያሳየው የየትኛው ዓመት ነው::

   ሀ. 2003 ዓ.ም
   ሐ. 2005 ዓ.ም
   ለ. 2004 ዓ.ም
   መ. 2006 ዓ.ም

4. ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም የቲቢ በሽታ ህክምና ወስደው የተፈወሱትን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. በመጠኑ እየተቀነሰ ሄዷል
   ለ. በመጠኑ በየአመቱ ጭማሪ አሳይቷል
   ሐ. ከነበረው ምንም ለውጥ የለውም
   መ. ከሁለተኛው ዓመት ከነበረው በሶስተኛው ዓመት ጭማሪ አሳይቷል

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የቲቢ በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ለ. የሳንባ ቲቢ ዋና ምልክት ምንድን ነው?

ሐ. የሳንባ ቲቢ በሽታ በምን በምን ይተላለፋል?

መ. የፀረ-ቲቢ መድኃኒቶችን በተላመደ ቲቢና ባልተላመደ ቲቢ መካከል ምን ልዩነት አለ?

ሠ. «የቲቢ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር ይቻላል» ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብራርታችሁ ግለጹ።

ረ. የቲቢ በሽታ ሥርጭት መጠን በግራፉ ባለው መረጃ ዓይነት የሚቀጥል ከሆነ ወደፊት ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ተግባር

ከዚህ በታች በሠንጠረዡ የተዘረዘሩትን የአካል ክፍሎች በምንባቡ መሠረት «ቲቢ የሚያጠቃቸው» ወይም «የማያጠቃቸው» በማለት በደብተራችሁ ላይ ይህን (✓) ምልክት በማድረግ መድቧቸው።

| ውጫዊና ውስጣዊ የአካል ክፍሎች | ቲቢ የሚያጠቃቸው | ቲቢ የማያጠቃቸው |
|---|---|---|
| ዓይን | | |
| ጆሮ | | |
| ሳንባ | | |
| ጉበት | | |
| አጥንት | | |
| ልብ | | |
| ኩላሊት | | |
| አንጎል | | |
| ጨጓራ | | |
| መገጣጠሚያዎች | | |
| አንጀት | | |
| የአንገት አካባቢ ዕጢዎች | | |

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## ሀሳብን በግራፍ ማስፈር

### ተግባር

በሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን የመቶኛ መረጃዎች በባር ግራፍ አሳዩ።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጤና ጥበቃ ቢሮ፣ ጥቅምት 2006 ዓ.ም. በጤና ፌስቲቫል ልዩ መጽሔት ላይ በወባ በሽታ ስለተያዙ ሰዎች ብዛት የሚገልጽ መረጃ አውጥቷል። በወጣው መረጃ መሠረት በ2002 ዓ.ም. 3,999 ሰዎች በወባ በሽታ ተይዘው በጤና ተቋማት ተኝተው ታክመዋል። ከእነዚህ መካከል 97.70 በመቶ የሚሆኑት ሲድኑ፣ 2.30 በመቶ የሚሆኑ ደግሞ ሕይወታቸው አልፏል። እንዲሁም በ2003 ዓ.ም. በወባ በሽታ ምክንያት በጤና ተቋማት ተኝተው ከታከሙት 2,914 ሰዎች መካከል 98.50 በመቶ የሚሆኑት ሲድኑ፣ 1.50 በመቶ የሚሆኑት ህይወታቸው አልፏል።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

የሚከተሉትን ሥርዓተነጥቦች በአግባቡ በመጠቀም አንቀጹን እንደገና ጻፉ።

| ! | - | « » | . | ። |
|---|---|---|---|---|

የዓለም ቲቢ ቀን በየዓመቱ የሚከበረው የተለያዩ መሪ ቃላትንና መፈክሮችን በማንገብ ነው ለምሣሌ እ.አ.አ ከ2010-2011 እንደመሪ ቃል የተመረጠው በአዲስ አስተሳሰብና ፍጥነት ቲቢን እንግታ የሚል ነው ይህ የፀረቲቢ እንቅስቃሴ ዘመናዊና ቀልጣፋ የላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች በሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸውም ይጠቁማል የዶትስና የስቶፕ የፀረቲቢ አሰጣጥ ሥልትም ቀልጣፋና ለአገልግሎት ፈላጊዎች ተደራሽ ሊሆን ይገባል።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የቲቢ በሽታ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

«የቲቢ በሽታ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሷቸውን ዋናዋና ሀሳቦች ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «የቲቢ በሽታ» በሚለው ምንባብ ውስጥ ያለውን ግራፍ አንብቡ።

# መናገር

## ቃለምልልስ ማካሄድ

#### ተግባር

በአንድ ቡድን አራት አባላት በመሆን አንዳችሁ እንደጋዜጠኛ፣ ሦስታችሁ እንደጤና ባለሙያ በመሆን ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን በተመለከተ ቃለ ምልልስ አካሂዱ።

ቃለ ምልልሱን ለማካሔድ እንደጋዜጠኛ ሆናችሁ የምትጠይቁት ለቃለመጠይቅ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ለማውጣት፣ እንደጤና ባለሙያ ሆናችሁ ምላሽ የምትሰጡት ደግሞ መልስ ለመስጠት እንዲረዳችሁ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥታችሁ ተዘጋጁ።

### የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ

- ምንነት
- የቫይረሱ ባህርይ
- በኤች አይ ቪና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት
- ከሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የሚለይበት
- የመተላለፊያ መንገዱ

- መከላከያው
- በሰዎች ላይ የሚያደርሰው ማህበራዊ፣ ምጣኔሀብታዊያዊና ሥነልቦናዊ ተፅዕኖ
- በሀገር ላይ የሚያስከትለው ማህበራዊ፣ ምጣኔሀብታዊያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ በተመለከተ።

## ሰዋስው

### የጊዜና የቦታ ተውሳከግስ

### ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረቡትን ተውሳከግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ፤ (ለአንድ ዓረፍተነገር ከአንድ በላይ ተውሳከግስ ሊኖር ይችላል።)

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ዘወትር | ነገ | እዚያ | ወዲህ | ዛሬ | ትናንት |
| ውጪ | ቅድም | በፊት | ቶሎ | ማታ | |

ሀ. የናፈቅናት እህታችን _______________ መጣች።

ለ. ጎበዙ ተማሪ ከመምህሩ _______________ መጣ።

ሐ. ታላቅ ወንድሙ _______________ አለ።

መ. ረዥሙ ልጅ _______________ ጫማ ገዛ።

ሠ. እሱ አሁን የለም፤ _______________ ነበር።

ረ. አስቴር ከክፍሉ _______________ ተቀመጠች።

ሰ. አለሙ አካባቢውን ለቆ _______________ ወደሌላ ቦታ ሄደ።

ሸ. ብዙ ጊዜ ሳይሳካለት ኖሮ _______________ ተሳካላት።

ቀ. አባትየው ሰሚ ቢያጣም _______________ ይናገራል።

በ. በቀለ _______________ ወደአዲስአበባ ይሄዳል።

### ተግባር 2

ከዚህ በታች የቀረቡትን ተውሳከግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሀ. ትናንት

ለ. ወዲያው

ሐ. ውስጥ

መ. እዚህ

# የቃላት ጥናት

## መነጠልና ማጣመር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | በ-አስ-ተማማኝ | በአስተማማኝ |
| ለ | እንደ-ኣይ-በከል-ኡ | እንዳይበከሉ |
| ሐ | እንደ-ኣይ-ራብ-ኡ-ባቸው | እንዳይራቡባቸው |
| መ | ወደ-ምንመገብ-ኧው | ወደምንመገበው |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በፍጥነት አንብቡ

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ታቆረ | መራቢያ | ማቀዝቀዣ | እስኪሞላቸው |
| ፓፓያ | አጎበር | ወረርሽኝ | ከመፀዳጃቤት |
| ማንጎ | ተከልሎ | በትንኞች | በመመርመርና |
| አቦካዶ | መከተብ | እንዲኖር | የዝንቦችንና |
| ዘይቱና | ጀርሞች | የአባለዘር | የምንመገበውን |
| እንነካ | መወሰን | በዛንዚራ | መኖሪያቤቶችና |

## ማንበብ

# ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል

## ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ

ሀ. በአካባቢያችሁ በስፋት የሚታወቁ ተላላፊ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

ለ. ከመፀዳጃ መልስ ወይም ከምግብ በፊትና በኋላ እጃችንን በሳሙናና በውኃ እንድንታጠብ የሚመከረው ለምንድን ነው?

## የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

ቀጥሎ «ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መልዕክቱን ከቀደመ ዕውቀታችሁ ጋር በማገናዘብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

# ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል

ተላላፊ በሽታዎች በግለሰብና በሀገር ላይ ከፍተኛ ችግር ስለሚፈጥሩ አስቀድሞ መከላከል ያስፈልጋል። ምግብና ውኃን በጥንቃቄ በመጠቀም፣ የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ፣ ሕፃናትን በበቂ ሁኔታ የእናት ጡት በማጥባትና ፈሳሽ ቆሻሻን በአግባቡ በማስወገድ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። እንዲሁም የግልና የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ፣ አንድ ለአንድ መወሰን፣ ደረቅ ቆሻሻን ማቃጠል ወይም መቅበር ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ያስችላሉ። በተጨማሪም በአካባቢ የዝንብና የትንኝ መራቢያ ቦታዎችን በማፅዳት፣ አጎበር በመጠቀምና በመኖሪያ አካባቢ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖር በማድረግ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። በተለይ በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል አስቀድሞ መከተብ ተገቢ ነው።

ተላላፊ በሽታዎች በተበከለ ውኃ አማካይነት ስለሚመጡ በአስተማማኝ ሁኔታ ንፅህናው ያልተጠበቀን የመጠጥ ውኃ ሁልጊዜ አፍልቶ በማቀዝቀዝ መጠጣት አስፈላጊ ነው። ውኃው ፈልቶ ከቀዘቀዘ በኋላም በንፁህ ዕቃ ከድኖ ማስቀመጥ ይገባል። ለመጠጣት ሲፈለግ ደግሞ መጠጫውን አስቀድሞ ማጠብ ያስፈልጋል።

በጥሬያቸው የሚበሉ ምግቦችን በሚገባ አጥቦ በመጠቀም ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ለምሣሌ ዘይቱና፣ ኮክ፣ እንጆሪ፣ የወይን ፍሬ፣ ተምር

የመሳሰሉትን ሳያጥቡ መመገብ አያስፈልግም። በተጨማሪም ብርቱካን፣ አቦካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓያ፣ እንዲሁም ሠላጣ፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም የመሳሰሉትን አትክልትና ፍራፍሬዎች አጥቦ መመገብ ያስፈልጋል። ሌሎች ምግቦችን ደግሞ በደንብ አብስሎ መመገብ ይገባል።

ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የበሰሉ ምግቦችን ወዲያው መመገብ ይገባል። ይህም ከበሰሉ በኋላ እንዳይበከሉ ያደርጋል። ካልተቻለም የበሰሉ ምግቦች የበሽታ አምጪ ህዋሳት እንዳይራቡባቸው በማቀዝቀዣ ውስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ቅዝቃዜ ሕዋሳት እንዳይራቡ ስለሚያደርግ በማቀዝቀዣ ውስጥ ያሉ ምግቦች አይበከሉም። ለመመገብ በሚያስፈልጉበት ጊዜ ደግሞ በሚገባ መሞቅ ይኖርባቸዋል።

**የእናት ጡት ወተት በተገቢው ያገኙ ሕፃናት በሽታን የመቋቋም አቅም አላቸው።**

የተመጣጠነ ምግብን መመገብ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ያስችላል።በተለይም ሕጻናት ከተወለዱ እስከስድስት ወር ድረስ የእናታቸውን ጡት ብቻ መጥባት አለባቸው። አንድ ዓመት እስኪሞላቸው ደግሞ ከተጨማሪ ምግብ ጋር የእናት ጡት ወተት ሊያገኙ ይገባል። በዚህ ሁኔታ የሕፃናትን በሽታ የመከላከል አቅም ማጠናከር ይቻላል። ፈሳሽና ደረቅ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ ተላላፊ በሽታዎችን ይከላከላል። ማንኛውንም ዓይነት ፈሳሽ ቆሻሻ በአግባቡ ማስወገድ ይገባል። ፈሳሽ ቆሻሻ ከፋብሪካ ወይም ከየቤቱ የሚወጣ ሊሆን ይችላል። ይህን ቆሻሻ በፈሳሽ ማዝቀጫ ጉድጓድ ማስረግና ከአካባቢ እንዲርቅ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ደረቅ ቆሻሻን በመቅበር አካባቢን ማፅዳት ከንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ይከላከላል።



ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል አንደኛው መንገድ ከተፀዳዱ በኋላ እጅን በውኃና በሳሙና ወይም በአመድ መታጠብ ነው።

ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ሌላው መንገድ ከተፀዳዱ በኋላ እጅን በውኃና በሳሙና ወይም በአመድ በደንብ መታጠብ ነው። ምክንያቱም የተላላፊ በሽታ ጀርሞች በመፀዳጃቤት ቆሻሻ ውስጥ በፍጥነት ስለሚራቡ በቀላሉ እጃችንን ሊበክሉ ይችላሉ። በተላላፊ በሽታ ተይዘን ከሆነ ደግሞ ሳንታጠብ የምንመገበውን ምግብ ወይም የሌላ ሰው እጅ እንነካ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ጀርሞቹ ወደምንመገበው ምግብ ወይም ወደነካናቸው ሰዎች ይተላለፉና ለበሽታ ያጋልጡናል። በጀርሞቹ ምክንያት በበሽታ ላለመጋለጥ ከመፀዳጃቤት መልስ በሳሙና ወይም በአመድ በደንብ መታጠብ አማራጭ የለውም። በተጨማሪም ገላን በመታጠብና ጥርስን በመቦረሽ የግል ንፅህናን መጠበቅ ያስፈልጋል።

አንድ ለአንድ መወሰን በግብረሥጋ ግንኙነት ምክንያት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል ያስችላል። ኤች.አይ.ቪ./ኤድስና የአባለዘር በሽታዎች በአብዛኛው የሚተላለፉት በግብረሥጋ ግንኙነት ነው። ስለዚህ አስቀድሞ በመመርመርና አንድ ለአንድ በመወሰን እነዚህን በሽታዎች መከላከል ይቻላል። መወሰን ካልተቻለ ደግሞ ኮንዶም በመጠቀም መከላከል ተገቢ ነው።


የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ ተላላፊ በሽታዎችን ይከላከላል። የዝንቦችንና የትንኞችን መራቢያ ማፅዳት፣ የታቆረን ውኃ ማፍሰስ፣ የመኖሪያ አካባቢን በአግባቡ ማፅዳት ተላላፊ በሽታን ለመከላከል ያስችላል። በተጨማሪም በአጎበር (በዛንዚራ) ተከልሎ መተኛት በትንኞች አማካይነት ከሚመጣ ተላላፊ በሽታ ይከላከላል። መኖሪያቤቶችና ሌሎች ክፍሎች በቂና ንፁህ የአየር ዝውውር እንዲኖራቸው በማድረግ ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ በክትባት መከላከል ለምንችላቸው በሽታዎች ቀድመን በመከተብ ከተላላፊ በሽታዎች በቀላሉ ነጻ መሆን ይቻላል።

(አዲስ አድማስ ድረገጽ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በምንባቡ መሠረት በትክክል አሟሉ።



## ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለቀረቡት ክፍት ቦታዎች ተስማሚ ቃል (ሐረግን) በመምረጥ አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| አትክልት | ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች | |
| ጀርሞች/ተሃዋስያን | በሽታ | መከላከል |

ሀ. የእናት ጡት ወተት በተገቢው የተመገቡ ሕፃናት ____________ የመቋቋም አቅም አላቸው።

ለ. ብርቱካን፣ አቦካዶ፣ ማንጎ የመሳሰሉትን ፍራፍሬዎችና ሠላጣ፣ ቲማቲም የመሳሰሉትን ____________ አጥቦ መመገብ ያስፈልጋል።

ሐ. የተላላፊ በሽታ ____________ በመፀዳጃ ቤት ቆሻሻ ውስጥ በፍጥነት ስለሚራቡ በቀላሉ እጃችንን ሊበክሉ ይችላሉ።

መ. ከፋብሪካና ከየቤቱ የሚወጡ ____________ በተገቢው መንገድ መወገድ አለባቸው።

ሠ. ተላላፊ በሽታዎች ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት አስቀድሞ ____________ ያስፈልጋል።

## 8ኛ ቀን

# ቃላት

## ቃላትን ማርባትና መመሥረት

### ተግባር

በሚከተሉት ቃላት ላይ ቅጥያዎችን በመጨመር ቃላትን በማርባትና በመመሥረት ጻፉ።

ምሳሌ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሕዝብ | ሕዝቧ<br>ሕዝባችን<br>ሕዝቡ<br>ሕዝባዊ | ዓይን | ዓይኖች<br>ዓይናችን<br>ዓይኑ/ኗ<br>ዓይናማ | እግር | እግሮች<br>እግራችን<br>እግሩ/ሯ<br>እግረኛ |

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሀገር | መ. ፍሬ | ሰ. መንገድ |
| ለ. እናት | ሠ. ብርቱካን | ሸ. ሰልፍ |
| ሐ. ጊዜ | ረ. ተራራ | ቀ. ግንብ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የሠንጠረዥ መረጃን በሀተታ መጻፍ

#### ተግባር 1

የሠንጠረዡን መረጃ መሠረት በማድረግ በሐተታ ጽሑፍ ግለጹ።

የኢትዮጵያ ፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፀረ ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎት መድሃኒት የወለዱ ከ2003 ዓ.ም - 2006 ዓ.ም

| አገልግሎት | 2003 ዓ.ም | 2004 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| በፀረ ኤች አይቪ ህምክና የተመዘገቡ | 580,919 | 602,215 | 744,330 | 805,948 |
| መድሃኒት የጀመሩ | 333,434 | 342,954 | 439,301 | 492,689 |
| መድሃኒቱን በመውሰድ ላይ ያሉ | 247,805 | 270,543 | 308,860 | 344,344 |
| መድሃኒቱን በመጠቀም ላይ ያሉ በመቶኛ | 42.65% | 44.92% | 41.49% | 42.72% |

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የ2006 በጀት ዓመት የእቅድ ክንውን ሪፖረት የተወሰደ።

#### ተግባር 2

በተግባር 1፣ በመቶኛ የቀረበውን መረጃ በመጠቀም ባር ግራፍ ሥሩ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች ፊደላትን ሳትገድፉና ሥርዓተነጥቦችን ሳታጓድሉ ጻፉ።

# 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል

## ቅድመንባብ

### ተግባር

«ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሷቸውን መከላከያ መንገዶች ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

«ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን አምስት አንቀጾች ድምፅ በማሰማት በፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### ተግባር

በ1ኛ ሳምንት በ1ኛ ቀን «ተላላፊ በሽታዎች»ና በ3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን፣ «ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል» ከሚሉት ምንባቦች ምን እንደተገነዘባችሁ በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

## ተውሳከግስ፣ መደብና ጊዜ አመልካች

### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን መደብ፣ ተውሳከግስና ጊዜ አመልካቾችን በመለየት በሚወክላቸው ቦታ የራይት (✓) ምልክት አድርጉ።

| ዓረፍተነገሮች | | መደብ | | | ተውሳከ ግስ | | | ጊዜ (የግስ ባህሪ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | የጊዜ | የቦታ | የመጠን | የአሁን | የኃላፊ | የትንቢት |
| ሀ | ትናንት የማጠቃለያ ፈተና ተፈተንኩ። | | | | | | | | | |
| ለ | ሞሚና ዛሬ ከሰዓት በኋላ የቀለም ትምህርት ውድድር ታደርጋለች። | | | | | | | | | |
| ሐ | አስቴር አሁን ከትምህርት ቤት ትመጣለች። | | | | | | | | | |
| መ | አንቺ ነገ እዚህ ግጥሞችሽን ታቀርቢያለሽ። | | | | | | | | | |
| ሠ | አስካለ ትናንት የሀበሻ ልብስ ገዛች። | | | | | | | | | |
| ረ | ዓለማየሁ አሁን ትልቅ ዓሣ ይገዛል። | | | | | | | | | |
| ሰ | አንተ አሁን የጭስ አባይ ፏፏቴን ትጎበኛለህ። | | | | | | | | | |



# ምዕራፍ 10

# ቃላዊ ግጥም

## የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እንደ-ተመሳሰሉ-አቸው | እንደተመሳሰሏቸው |
| ለ | አገልግሎት-ኤ-ማ | አገልግሎቴማ |
| ሐ | ተመልካች-ነት-ኡ | ተመልካችነቱ |
| መ | እንደ-ፍላጎት-ህ | እንደፍላጎትህ |
| ሠ | ልልቀቅ-ል-ህ | ልልቀቅልህ |
| ረ | የ-ሚ-መሣሠል-ኡ-ብ-አቸው | የሚመሣሠሉባቸው |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በፍጥነት አንብቡ።

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> | <u>ሐ</u> |
|---|---|---|
| ምህላ | ቅንብሮች | የሚገለጹበት |
| ከበኸኝ | እንጉርጉሮ | አስተርጓሪ |
| ቀረርቶ | ለመቋቋም | ያለመልማል |
| ባህርያት | ቆላ ለቆላ | የመለዋወጥ |

## ማንበብ

## የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ

ሀ. «የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም» የሚለው ርዕስ ስለምን እንደሚገልጽ ገምታችሁ ተናገሩ?

ለ. በተጻፉና ባልተጻፉ ግጥሞች መካከል ምን ዓይነት አንድነትና ልዩነት ያለ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በተጻፈና ባልተጻፈ ግጥም መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በማጤንና የግጥሞቹን ዜማ በመጠበቅ ለራሳችሁ በሚሰማ ድምጽ አንብቡ።

## የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም



ግጥም የሰው ልጆች ስሜታቸውንና ሀሳባቸውን የሚገልጹበት የሥነፅሁፍ ዘርፍ ነው። ደስታ፣ ሀዘን፣ ጥቃት፣ ብቸኝነት፣ ጀግንነት በግጥም ይገለጻል። እንጉርጉሮ፣ ጸሎት፣ ዘፈን፣ ሆታ፣ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ምህላ፣ ምርቃትና እርግማን ግጥማዊ ቅርጽ

አላቸው። መንፈሳዊ መዝሙሮችና ዓለማዊ ዘፈኖች የሙዚቃና የግጥም ቅንብሮች ናቸው።

ግጥም በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ግጥም አእምሮን ያበለፅጋል፤ መንፈስን ያለመልማል፤ ግጥም ሀዘንን ለመቋቋም ይረዳል፤ ከብስጭት ይመልሳል፤ ትዕግስትን ይቸራል። ግጥም ማግኘትንና ማጣትን፣ ክብርና ውርደትን፣ ሹመትንና ሽረትን፣ ፍቅርንና ጥላቻን ለመግለፅ ያስችላል። ሲነበብ ጣዕም አለው።

ግጥም ከአቀራረቡ አንጻር የተጻፈና ያልተጻፈ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል። የተጻፈ ግጥም በህትመት በመጽሐፍ (በወረቀት) ሰፍሮ ገጣሚ ባለቤት ያለው ሲሆን፣ በጽሑፍ ከትውልድ ወደትውልድ ይተላለፋል። ያልተጻፈ ግጥም ደግሞ በአብዛኛው ቃላዊ ሲሆን፣ በግጥም ቅርጽ የሚቀርቡትንና በቃል የሚተላለፉትን ሁሉ ያካትታል። ያልተጻፈ ግጥም ደራሲው ሕዝብ ነው። የተለየና እገሌ የሚባል ገጣሚ ወይም ደራሲ የለውም።

ሁለቱ የግጥም ዓይነቶች የሚመሳሰሉባቸው ባህርያት አሏቸው። ከእነዚህ ባህርያት መካከል ሁለቱም የሥነጽሑፍ ዘርፎች መሆናቸው፣ የሰዎችን ሀሳብና ስሜት መግለጽ መቻላቸውና በተመሳሳይ ቅርፅ መቅረባቸው ዋናዋናዎቹ ናቸው። በተመሳሳይ ቅርጽ መቅረብ ሲባል ግጥሞቹ በሐረግ፣ በስንኝ፣ በአንጓ መዋቀራቸውና የተስተካከለ ምጣኔና ያልተዛባ ምት ያላቸው መሆኑ ነው።

ምንም እንኳ እንደተመሳሰሏቸው አይብዛ እንጂ፣ መጠነኛ የሆነ ልዩነትም አላቸው። የተጻፈ ግጥም በገጣሚው/ዋ አማካይነት አንድ ጊዜ ከተጻፉ በኋላ ሳይለወጥ ይቆያል። ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፈው በጽሑፍ በመሆኑ ካልተጻፈው ግጥም ይለያል። ያልተጻፈ ግጥም ግን የሕዝብ ሀብት ነው። ቃላዊ በመሆኑ የመለዋወጥ ወይም የመሻሻል ባህርይ ይታይበታል። ግጥሙ ሲነገር ከቦታ ቦታ መጠነኛ የሆነ ልዩነት ሊኖረው ይችላል። ለትውልድ የሚተላለፈውም በቃል ነው።

የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥምን ለማወዳደርና ለማነጻጸር የሚከተሉትን ግጥሞች ለአብነት ያህል እንመልከት።

ሀ. ያልተጻፈ ግጥም

## የፉከራ ግጥም

ልከህ ስደደኝ ቆላ ለቆላ፣

ከላሹን ላምጣው ጥሬ ሲቆላ።

ከዳገት ውሎ ከዘብጥ አዳሪ፣

ሻሽ የመሰለ ድግ አስተርታሪ፣
ለናት አገሩ ተከራካሪ፣
የሰው ኮርቻ ጦም አሳዳሪ፣
ነፍስ የሚታደግ እንደፈጣሪ።

## የእርሻ ግጥም

እርሻ ያረሰና የወንዝ ዳር ዛፍ፣
ዘላለም ይኖራል አበባው ሣይረግፍ።
ያርሳል በደመና ይቆፍራል በጉም፣
ከሰው ማሣ ሂዶ እጁን አይዘረጋም።
በጎምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል፣
ቆርቆሮ ቤት ሠራ ፋኖስ የሚመስል።
በረዥም ማረሻ ካልሸጠሸጡት፣
አይሞላም ጎተራ ዝቅ ብለው ቢያዩት።

ለ. የተጻፈ ግጥም

## ፋኖስና ብርጭቆ

አንድ የፋኖስ መብራት በሥራው የኮራ፣
እንዲህ ሲል ተጣላ ከብርጭቆ ጋራ።
እኔ ነኝ መብራቱ ብርሃን የምሰጥ፣
ጨለማን አጥፍቼ የምገላልጥ።
አንተ ግን እፊቴ እንዲህ ተደንቅረህ፣
ዙሪያየን ከበኸኝ እንዲያው ተገትረህ።
አልገባኝም ከቶ የምትሠራው ሥራ፣
ብርሃኔ ሩቅ ደርሶ ደምቆ እንዳያበራ።
ተሰራጭቶ በጣም እንዳይዘረጋ፣
አንተን ፈጠረብኝ መንገድ የምትዘጋ።
እንቅፋት እየሆንክ ሥራዬን አታጥፋ፣


ገለል በል ከፊቴ ብርሃኔ ይስፋፋ።
አገልግሎቴማ ከሆነብኝ ጥፋት፣
እውነትማ ላንተ ከሆንኩህ እንቅፋት።
ልሂድልህ እሺ በል ልልቀቅልህ ፣
እንደልብህ አብራ እንደፍላጎትህ፣
ልሂድልህ ብሎ ሲለቅለት ቦታ፣
ከጎን የነፈሰ የንፋስ <u>ሽውታ</u>፣
መጣና መብራቱን አጠፋው ባንድ አፍታ።
አጭር እየሆነ ተመልካችነቱ፣
መለየት አቅቶት ጥቅሙን ከጉዳቱ።
እወቁኝ እወቁኝ እያለ ሲነሳ፣
ሰውም እንደዚሁ ያመጣል <u>አበሳ</u>።

(ከበደ ሚካኤል፣ 1999። *ታሪክና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ። ፪ኛ እትም*፣ ገጽ 40)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በተጻፈና ባልተጻፈ ግጥም መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ ከዚህ በታች የቀረበውን ቢጋር በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁ።



### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በፉከራ ግጥምና በእርሻ ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. «በእርሻ ግጥም»ና «በፋኖስና ብርጭቆ» በሚል ርዕስ በቀረበው ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. «ፋኖስና ብርጭቆ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ግጥም የተማራችሁትን ቁምነገር ግለጹ።

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሣሣይ ፍቺ ጻፉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ዘብጥ | ሐ. መታደግ | ሠ. አበሳ | ሰ. መቸር |
| ለ. ድግ | መ. መደንቀር | ረ. ምህላ | ሸ. ሽውታ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የግጥም ስንኞችን ማሟላት

### ተግባር

ቀጥሎ ለቀረቡት ስንኞች ለእያንዳንዳቸው ተስማሚ የሚሆኑ ሌሎች ስንኞችን ከራሳችሁ አፍልቃችሁ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

### ትምህርትቤቴ

ሀ. ትምህርትቤቴ ፍቅሬን ልግለጽልሽ፣

______________________________

ለ. ራዕዬን ላሣካ በትምህርት ገበታ፣

______________________________

ሐ. የሕይወቴ ለዋጭ ፍጹም መድህኒቴ፣

_______________________________

መ. መሠረት ሆነሽኝ ጠንክሬ እንድሠራ፣

_______________________________

ሠ. ታሪክን አውቄ ሕዝቦችን እንዳከብር፣

_______________________________

ረ. ፍቅርሽን መግለጫ ቃላት ቢያጥረኝም፣

_______________________________

ሰ. እጠብቅሻለሁ ኑሪልኝ እናቴ፣

_______________________________

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ተግባር

የተዘበራረቁትን ስንኞች እንደገና በማደራጀትና ሥርዓተነጥቦችን በማሟላት ግጥሙን እንደገና ጻፉ።

### ጽጌረዳና ዳመና

አንዲት ጽጌረዳ ቃልዋን አስተዛዝና

የፀሐይ ንዳድ ያጠቃት በብዙ

እንዲህ ተናገረች ለሰማይ ደመና

ጠውልጎ የሚታይ የቅጠልዋ ወዙ

እባክህ ጣልልኝ የዝናብ ጠብታ

ምንም ተስፋ የለኝ መሞቴ ነውና

ቶሎ ካላራስከኝ ጉልበቴ እንዲጠና

ድርቀት በጣም ጎድቶኝ እየኝ ስንገላታ

አዘንምልሻለሁ ጠብቂኝ እያለ

አሁን መሄዴ ነው ለትልቅ ጉዳይ

ምንም ሳይጥልላት መንገዱን ቀጠለ

ስመለስ መጥቼ ሳልፍ ባንቺ ላይ

(ከበደ ሚካኤል፣ 1999። *ታሪክና ምሣሌ ፩ኛ መጽሐፍ። ፪ኛ እትም*፣ ገጽ 33 በከፊል የተወሰደ።)

## 3ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሷቸውን ቃላዊና ጽሁፋዊ ግጥሞች ተመሣሥሎና ልዩነት ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች መምህራችሁ እንዳነበቡት አድርጋችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

# ማዳመጥ

## የተጻፈና ያልተጻፈ ግጥም

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከዚህ በፊት የምታውቁትን የፉከራ ግጥም በድምፅና በድርጊት አሳዩ።

ለ. መምህራችሁ አንድ የፉከራ ግጥም የመጀመሪያውን ስንኝ ሲያሰሟችሁ እናንተ ሁለተኛውን ስንኝ ተናገሩ።

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

መምህራችሁ የተጻፉና ያልተጻፉ ግጥሞች ሲያነቡላችሁ ተመሳስሏቸውንና ልዩነታቸውን በማወዳደርና በማነጻጸር በትኩረት አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችኋቸው ግጥሞች መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ጀግና» በሚል ርዕስ በቀረበው የተጻፈ ግጥምና «በግብርና» ቃላዊ ግጥም መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ለ. ጀግናን፣ ኀበዝ ገበሬንና ጀግንነትን ለማሞገስ ከቀረቡት ግጥሞች መካከል በጣም ያስደሰቷችሁንና የምታስታውሷቸውን ስንኞች ተናገሩ።

## ሰዋስው

## አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገሮች

### ተግባር

ከዚህ በታች የቀረቡትን አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ቀይራችሁ ጻፏቸው።

ሀ. አቶ አለሙ ቤት ሠሩ።

ለ. ቃላዊ ግጥሞችን ማዳመጥ ያስደስተኛል።

ሐ. እሱ ክፉ ሰው ነው።

መ. ልጁ እቤት አለ።

ሠ. ቀጭኗ ልጅ ኀበዝ ተማሪ ናት።

ረ. ሰውዬው ኀበዝ ተናጋሪ ነው።

ሰ. ሕፃኑ መጫወቻውን ሰበረው።

ሸ. የፉከራና የቀረርቶ ግጥሞች ቃላዊ ናቸው።

ቀ. ሙዚቃ የሰዎችን መንፈስ ያድሳል።

በ. አዛውንቱ የሄዱበት ቦታ ታውቋል።

## ማንበብ

### ቃላዊ ግጥሞች

#### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የምታውቋቸውን የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ዘርዝሩ።

ለ. የምታውቋቸው ቃላዊ ግጥሞች የሚከናወኑባቸውን አጋጣሚዎች ተናገሩ።

#### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ለራሳችሁ በሚሰማ ድምፅ በማንበብ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ተረዱ።

### ቃላዊ ግጥሞች

#### የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች

በአማርኛ የተለያዩ የቃላዊ ግጥም ዓይነቶች አሉ። የውቂያ፣ የፍቅር፣ የቀረርቶ፣ የፉከራ፣ የሥራ፣ የልጆች ጨዋታ፣ የባህል ዘፈኖችና የሙሾ ግጥሞች ወዘተ. ከቃላዊ ግጥም ዓይነቶች ይፈረጃሉ። ከነዚህ መካከል የተወሰኑትን ለአብነት ያህል እንመልከት።

#### ሀ. የውቂያ ግጥም

ይህ ቃላዊ ግጥም በሰብል ውቂያ ጊዜ አርሶአደሮች ራሳቸውንና አጋሮቻቸውን የሚያነቃቁበትና ለእንስሳት ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት የሚገልጹበት ቃላዊ ግጥም ነው። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡-

በሬ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር፣
አያ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር፣
እንዝርትም አይገኝ ከፊታይ መንደር።
አያ በሬ ሆሆ አያ ጎኔ ሆሆ፣
በሬ ሆይ አሆሆ ወዳጄ አሆሆ፣
ዳል ጋህን ዋጠው የምርት አድባሆ።
በርዬ አሽምድ ጎናቴ አሽምድ፣
ተሽከርከር እንደዓየር አድርገው አመድ።
በርዬ አንተናኔ የወረድንበቱ፣
ከካራ ይብሳል የድንጋይ ስለቱ።

## ለ. ቀረርቶና ፉከራ

ቀረርቶና ፉከራ የጀግንነት መግለጫ፣ የጠላትና የፈሪ መተንኮሻ ስልቶች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ የሚከወኑት በጦርነት ዋዜማና በጦርነት ጊዜ፣ በዐውዳመት በዓላትና በደል በዝቶ ልብ ሲሸፍት ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች በለቅሶ ጊዜም ይከወናሉ።

### ቀረርቶ

አረምን ካረሙ ከሥሩ ነቅለው ነው፣
ከቆረጡትማ ያው መተካቱ ነው።
ኧረ ጥራኝ ጫካው ኧረ ጥራኝ ዱሩ፣
ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ።
እኛን ስለከፋን ብናንጎራጉር፣
እኒህ ጥጋበኞች እንባል ጀመር።
እንኳን ምታ ብለው ልከው ሰደውት፣
በወገብ ላይ ሆኖ ያኮራል ጥይት።

### ፉከራ

ፎካሪ፦ «አካኪ ዘራፍ ...

በሮች ጥቋቁር ገበሬው ሙጫ፣

ማን ይለቀዋል እርፉ ቢንጫጫ።

ሎጋና ጎሹ የሄዱበቱ፣

ያረገርጋል የእርሻ መሬቱ።»

አጃቢ፦ «እውነት ነው!»

ፎካሪ፦ «አካኪ ዘራፍ ...

የጎበዝ በሬ ስሙ ባይከዳኝ፣

ዘሎ ቁብ አለ እንደቤት ከዳኝ።

የበሮቹ ቄስ የበሬው መምህር፣

አቆላላፊ ክምር በክምር።»

አጃቢ፦ «እርግጥ ነው!»

ፎካሪ፦ «ባምሌ በናሴ ያልተራበ ሰው፣

ሞፈር ቀንበሩን ቀሚስ ያልብሰው።»

አጃቢ፦ «እንዲያ በል!»

## ሐ. የልጆች ጨዋታ

የልጆች ጨዋታ እንደጨዋታው ዓይነት፣ እንደባህሉ፣ እንደልጆች ዕድሜ ይለያያል፤ ይከወናልም። በአብዛኛው በእንቅስቃሴ የታጀበ ነው። ለምሣሌ፣ ኧረ አምሣለ የሚለውን የልጆች ጨዋታ ግጥም ማየት ይቻላል።

### «ኧረ አምሣለ»

ኧረ አምሣለ?

ኧረ አምሣለ?

ኧረ ወዬ፣

ኧረ ወዬ፣

ኧረ እንዴነሽ?
ኧረ እንዴነሽ?

አለሁ በመከራ፣
እንባዬን ሳዘራ።

ለምን ታዘሪያለሽ?
አገዳ እየበላሽ።

አገዳም የለኝ፣
ምስኪን ደሀ ነኝ።

ምስኪን ደሀ ሆነሽ፣
ምን በልተሽ ታድሪያለሽ?

ባገኝም በልቼ፣
ባጣ ተደፍቼ።

ይድፉኝ ይደፉፉኝ፣
ጦም ማደርሽ ከፋኝ።

የደጅሽ እንኮይ፣
አልበሰለም ወይ?

ቢበስል ባይበስል፣
ትመጪ ይመስል።

መምጣቴንስ መጣሁ፣
አንድ አጫዋች አጣሁ።

(ዘሪሁን አስፋው። 1991። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።* ገጽ 57-58)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በልጆች ጨዋታ የቃላዊ ግጥም ተደጋጋሚ ስንኞችን ለይታችሁ ተናገሩ።

ለ. በልጆች ጨዋታና በቀረርቶ ግጥሞች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውንና በግጥም የሚቀርቡ የልጆች ጨዋታዎችን ስማቸውን ተናገሩ።

## ተግባር 2

ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ውስጥ ሀሳቡን አጉልቶ ለማሳየት የሚያስችለውን ቃል ወይም ሐረግ መሠረት በማድረግ መልዕክቱን በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. በርዬ አንተናኔ የወረድንበቱ፣

ከካራ ይብሳል የድንጋይ ስለቱ።

ለ. በርዬ አሸምድ ጎናቴ አሸምድ፣

ተሽከርከር እንደአየር አድርገው አመድ።

ሐ. በሬ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር፣

አያ እንዳንተ እሚዞር የሚሽከረከር፣

እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር።

መ. በሮች ጥቋቁር ገበሬው ሙጫ፣

ማን ይለቀዋል እርፉ ቢንጫጫ።

## 5ኛ ቀን

# ቃላት

## በቃላት ዓረፍተነገር መመስረት

### ተግባር

በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሀ. ክምር

ለ. ሙጫ

ሐ. ዳልጋ

መ. የሚሾር

ሠ. ያኮራል

ረ. እርፍ

ሰ. ጦም

ሸ. ሳዘራ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ግጥም መጻፍ

**ተግባር**

ከሚከተሉት ይዘቶች አንዱን ወይም የራሳችሁን ሌላ ርዕስ በመምረጥ ከአሥር ያላነሱ ስንኞች ያለው ግጥም ጻፉ።

ሀ. ትምህርት
ለ. ትምህርትቤት
ሐ. ቤተሰብ
መ. ጓደኛ

### የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

የስንኞቹን ሐረጎች ቅደምተከተል በማስተካከልና ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም የተሟላ ቃላዊ ግጥም ጻፉ።

ሀ. በሽታ የቅናት የከፋ ህመሙ
   ጨርሶ እሚያጠፋ የህሊናን ዓይኖች

ለ. በዚህ ክፉ ደዌ ሲለከፍ የሰው ልጅ
   የተጣራው ነገር ይመስለዋል ሰፈፍ።

ሐ. እያደላ ልቡም ወደክፋት ወገን
   ይመርጣል መሞትን ከማመስገን ሰውን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## ቃላዊ ግጥሞች

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን ካነበባችኋቸው ቃላዊ ግጥሞች መካከል የምታስታውሷቸውን ስንኞች በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን ከቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች መካከል የውቂያ ግጥምን በትክክለኛው ቅላፄ አንብቡ።

# መናገር

### ቀረርቶና ፉከራን መከወን

**ተግባር**

«ቃላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ የቀረቡትን የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች አንዳችሁ የቀረርቶ ግጥሞችን አንዳችሁ ደግሞ የፉከራ ግጥሞችን በትክክለኛው አከዋወን ስልት በሚና ጨዋታ አቅርቡ።

# ሰዋስው

## መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች

### ተግባር

የሚከተሉትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም ዓረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እንዴ | ለምን | ማን | መቼ | የት | ምን | ወይ |

ሀ. የዚህ ግጥም ደራሲ _________________ ነው?

ለ. የእርሻ ግጥም _________________ ይከወናል?

ሐ. ገነት ሻንጣ ገዛች _________________?

መ. ስለሥነቃል _________________ ታውቂያለሽ?

ሠ. የቀረርቶና የፉከራ ግጥም _________________ ይጠቅማል?

ረ. ልብስህን አጠብክ _________________?

ሰ. ዳዊት _________________ ሄደ?

## የቃላት ጥናት

### ቃላትን በፍጥነት ማንበብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት አቀላጥፋችሁ አንብቡ።

| ሀ | ለ | ሐ |
|---|---|---|
| ሲያባራ | ስቆርጠው | አይከለከል |
| አልቢን | አንናደድ | ካልተወራጩ |
| ጐልጐሎ | መጠምጠም | እንደጨጓራ |
| ላይለየው | እየመረረው | ቢቁለጨለጩ |
| በወንጭፍ | አይባረርም | አይሰለቸኝም |
| አርሳለሁ | አልመረርም | እንዳያምረው |

## ማንበብ

### ቃላዊ ግጥሞች

#### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛ ቀን ካነበባችኋቸው ቃላዊ ግጥሞች የምታስታውሷቸውን በቃላችሁ ተናገሩ።

#### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ «ቃላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ የቀረቡትን ግጥሞች የተገጠሙበትን ዓላማ በውል በማጤን ለራሳችሁ በሚሰማ ድምፅ አንብቡ።

## ቃላዊ ግጥሞች

ሀ. ስንዴውን ጐልጉሎ ጥሩ ምርት አገኘ፣
ጤፉንም ጐልጉሎ ጥሩ ምርት አገኘ፣
ባቄላውን ትቶ ኧረ እንዴት ተሞኘ።

ለ. ካልቢኑ ጋራ አለው መሀላ፣
ከእጁ ላይለየው ክንዱ ላይላላ።
የአልቢኔ መስላት የእህሉ ማማር፣
አይሰለቸኝም ስቆርጠው ባድር።

ሐ. ግንቦት ዘንቦ ሰኔን ሲያባራ፣
ሰርዶ አራጋፊ እንደጨጓራ።
በሬው ቀና በል ከጥጉ ድረስ፣
አርሶ የበላ አለው የደስደስ።
በሰፊ ድግር በሹል ማረሻ፣
ያደግንብሹ እንዴት ነሽ እርሻ።
ሥራ እንደኮሶ እየመረረው፣
ጠቅልሎ መጉረስ ማን አስተማረው።
በረጅም ሞፈር ካልተወራጩ፣
ሚቀመስ የለም ቢቁለጨለጩ።
ፎጣ መጠምጠም ራስ ይመልጣል፣
ሸንጥን ገትሮ ማረስ ይበልጣል።

መ. አህያ መጣች ተጭና ሻኛ፣
በልግና መኸር እጓሮ ተኛ፣
አህያ መጣች ተጭና ሞፈር፣
ቅቤ እንደጭቃ እህል እንደአፈር።

ሠ. መቅደላ አፋፉ ላይ ጨኸት በረከተ፣
የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ። (ለአጼ ቴዎድሮስ)

እንዳያምረው ውኃ ድሃ ወዳጅን፣
መተማ አፈሰሰ ዮሐንስ ደሙን። (ለአጼ ዮሐንስ)

ረ. ብነግድ አንድ ጨው፣
ባርስ አንድ ቁና፣
እንግዲህ ምንልበል እድሌ ነውና።
ኧረ ተወኝ ልቤ ተወኝ አንናደድ፣
ገብተናል ውድማ እየጠፋ መንገድ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላዊ ግጥሞቹ መሠረት በጽሑፍ መልስ ስጡ።

ሀ. ከ«ሀ» እስከ«ረ» የቀረቡት ግጥሞች እያዳንዳቸው ምን አጋጣሚዎችን መሠረት በማድረግ የተገጠሙ ይመስላችኋል?

ለ. ከ«ሀ» እስከ«ረ» የቀረቡት ግጥሞች እያንዳንዳቸው የቀረቡበትን ስሜት አብራርታችሁ ጻፉ።

ሐ. ከሚከተሉት ስንኞች የተረዳችኋቸውን ሀሳቦች በዝርው ጽሑፍ ግለጹ።

- ሥራ እንደኮሶ እየመረረው፣
  ጠቅልሎ መጉረስ ማን አስተማረው።
- አህያ መጣች ተጭና ሞፈር፣
  ቅቤ እንደጭቃ እህል እንደአፈር።

## ቃላት

### ቃላትን ከተገቢ መገለጫዎቻቸው ጋር ማዛመድ

#### ተግባር

ከሚከተሉት ቃላት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ ከ«ሀ» እስከ«ቀ» ከቀረቡት መግለጫዎች ጋር አዛምዱ።

| | | |
|---|---|---|
| አልቢን | ወንጭፍ | በልግ |
| ጐልጉሎ | ጐተራ | መኸር |
| ሰርዶ | ሞፈር | አውድማ |

ሀ. ብዙ አንጓ ያለውና መሬት ለመሬት የሚሄድ የሣር ዓይነት፣

ለ. ከጭቃ ወይም ከእንጨት፣ ከሸንበቆ፣ ከቀርከሀ ወይም ከቆርቆሮ አራት ማዕዘን ወይም ክብ ሆኖ የሚሠራና ክዳን ያለው የእህል ማስቀመጫ፣

ሐ. ለአዝመራና ለግጦሽ ሣር በቂ የሚሆን ዝናብ የሚገኝበት ወቅት (ከየካቲት እስከሚያዝያ ወር)፣

መ. የሠብል ማጨጃ መሣሪያ/ማጭድ፣

ሠ. እህል የሚወቃበት የተስተካከለና የለሰለሰ ቦታ፣

ረ. በክረምት ተዘርቶና በቅሎ የደረሰው እህል የሚታጨድበትና የሚሰበሰብበት ወቅት፣

ሰ. በዶማ ወይም በማረሻ የተነቀለን አረም አፈሩን በማራገፍ ከእርሻው ላይ የሚወገድበት ዘዴ፣

ሸ. ከጠፍር ወይም ከገመድ የሚሠራ የድንጋይ መወርወሪያ፣

ቀ. ረዘም ካለ እንጨት ተጠርቦ የሚሠራና ከቀንበር ጋር በምራን የሚያያዝ የእርሻ መሣሪያ፣

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ግጥም መጻፍ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን ድርሰት መጻፍ በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የጻፋችሁትን ግጥም፣ ለህትመት እንዲበቃ አድርጋችሁ እንደገና ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

በሚከተለው ቃላዊ ግጥም ውስጥ የግጥሙን አነባበብ የሚያዛቡ ቃላትን በማውጣትና ሥርዓተነጥቡን በማሟላት እንደገና ጻፉ።

**ቃላዊ ግጥም**

የሰው ወርቅ አያደምቅ ብለው ሲሉ ሰምቻለሁ
የዚያ የሰው ቤት የሰው ነው ሲሉ ሰምቻለሁ
የህል የእንጀራ ውኃየንም ተቀምጨዋለሁ
እንግዲህ ይበቃል እንጂ አገር ለምጃለሁ።

# 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**ቃላዊ ግጥሞች**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን «ቃላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ ከቀረቡት ግጥሞች መካከል የምታስታውሷቸውን ስንኞች በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር

በ3ኛ ሳምንት፣ በ7ኛ ቀን «ቃላዊ ግጥሞች» በሚል ከ«ሀ» እስከ«ረ» የቀረቡትን ግጥሞች ዜማቸውን/አገላለጻቸውን ጠብቃችሁ አንብቡ።

## መናገር

#### ተግባር

«ቃላዊ ግጥሞች» ከሚለው ርዕስ ሥር ከ«ሀ» እስከ«ረ» ከቀረቡት ግጥሞች አንዱን በመምረጥ አገላለጹን ጠብቃችሁ በቃላችሁ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### መጠይቃዊ ዓረፍተነገር

#### ተግባር

ማን፣ ምን፡ መቼ፣ እንዴ፣ ወይ የሚሉትን መጠይቃዊ ቃላት በመጠቀም አምስት ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

# ሙዳየ ቃላት

**ሀሳብ ማጋራት** (Think-aloud)፡- በአርዓያነት እያነበቡ እያሉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ቆም እያሉ ስለአንድ ነገር/ጉዳይ እንዴት እያሰብን እንደሆነ ለሌላ ሰው ሀሳብን ማካፈል፤

**መለየት/ማንበብ** (Decoding)፡- የተጻፉ ቃላትን (ጽሑፍን) ወደንግግር ቋንቋ ለመቀየር የፊደል ድምፅ ግንኙነትንና የቃላት ዕውቀትን መጠቀም፣

**መላልሶ ማንበብ** (Repeated reading)፡- በትክክለኛና በፍጥነት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት በግብረመልስ እየታገዙ ደጋግሞ የማንበብ ሂደት

**መልሶ ማንበብ** (Reread)፡- በማንበብ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ሀሳቡን መረዳት እስኪቻል ድረስ ወደኋላ እየተመለሱ ማንበብ፤

**መልዕክት ሰጪ ንባብ** (Prosody)፡- አንድ ጽሁፍ በትክክለኛው ወይም በተገቢው የድምፅ ቅላፄ ማንበብ፣

**መምህር መር ንባብ** (Guided Reading)፡- ለደረጃው የቀረበውን ጽሑፍ በትክክል ማንበብ እንዲቻል መምህሩን አንብበው በማሳየት ንባቡን የሚያስቀጥሉበት ሂደት፣

**መረዳት** (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

**መነጠል** (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ ቃል ወይም ሐረግ በተናጠላዊ ፊደሎች ወይም በአነስተኛ የቃል ክፍልፋዮች የመነጣጠል ሂደት

**መገመት** (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤ ስለገፀባህርያቱና ስለሴራው ድምዳሜ መስጠት፣

**የማዳመጥ ቃላት** (Listening vocabulary)፡- ሰዎች በንግግር ጊዜ አዳምጠው የሚረዷቸው ቃላት፣

**ማጠቃለል/ማሳጠር** (Summarizing)፡- የምንባብን አቢይ ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት፣

**ማጣመር** (blending)፡- በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ፊደሎች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

**ራስን የመከታተያ ስልት** (Self-checking strategy)፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት፣

**ቃላት በደቂቃ (ቃበደ)** (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል::)

**ቃላት ትንተና** (Word analysis)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ቅጥያዎች በመተንተን ለማንበብ የሚጠቀሙበት ስልት፣

**ቅጥያ** (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ::)

**ቅጽበታዊነት** (Automaticity)፡- ፊደላትን፣ ድምጾችንና ቃላትን ያለችግር፣ ሳያመነቱ፣ ሳያወላውሉ፣ በቅጽበትና በትክክል የመለየትና የማንበብ ችሎታ፣

**ቀጥተኛ ጥያቄ** (Explicit question)፡- መልሱ በቀጥታ ከምንባብ ወይም ከንግግር የሚገኝ ጥያቄ ዓይነት፣

**ቃላትን መረዳት/ማወቅ** (Word Recognition)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን ለመለየት የሚጠቀሙበት ስልት

**በማንበብ ሂደት መቆምና ማሰብ** (Stop and think)፡- በማንበብ ሂደት ምን እየተነበበ እንደሆነ ቆም ብሎ ማሰብ፣ ስለተነበበው ምንባብ ምንም ነገር ማስታወስ ካልተቻለ ወደፊት ከማንበብ ይልቅ ቆም ብሎ የተነበበውን ሀሳብ በአዕምሮ ለመረዳት መሞከር፣

**በቢጤ መማማር** (Peer tutoring)፡- ተማሪዎች ትምህርታዊ ክሂሎችን እርስበርስ የሚማማሩበት ሂደት

**የቢጋር ሠንጠረዥ** (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ ማደራጀ፣

**በትብብር መማር** (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

**ቤት መምታት** (Rhyme)፡- በተመሣሣይ ፊደሎች/ድምጾች የሚጨርሱ ቃላት /የግጥም ቤት/

**በጋራ ማንበብ** (Choral reading)፡- በርከት ያሉ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በጋራ ሆነው ድምፅ በማሰማት የሚያነቡበት ስልት፣

**ተራኪ ጽሑፍ** (Narrative text)፡- ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

**የታሪክ መዋቅር** (Story structure)፡- እንደመቼት፣ ድርጊት፣ ሁነት፣ ችግርና መፍትሄ ያሉትን አላባውያን የሚያካትት የድርሰት መዋቅር

**ትክክለኛነት** (Accuracy)፡- አንድን ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተትና ያለማወላወል የማንበብ ችሎታ፣

**ንባብን ወደፊት መቀጠል** (Read ahead)፡- አሻሚ ሀሳብ ሲያጋጥም ግልፅ እንዲሆን ወደፊት ያሉትን ዓረፍተነገሮች ማንበብ፤ የተወሰኑ ዓረፍተነገሮች ተነበው ሀሳቡ ግልፅ ካልሆነ ሌላ ስልት መፈለግ፣

**አመራማሪ ጥያቄዎች** (Implicit/inferential Questions)፡- ተማሪዎች በሚያነቡት/በሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማገናኘት መልስ የሚሰጡባቸው የአንብቦ/የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**አስረጂ ጽሑፍ** (Expository text)፡- መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

**አቀላጥፎ ማንበብ** (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በመሆን መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

**አንብቦ መረዳት** (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

**አዕምሯዊ ምሥል** (Mental picture)፡- የገፀባህርያት፣ የቦታና የሁነቶች ገለፃን በተመለከተ በአዕምሮ ምሥል እየፈጠሩ ማንበብ፣

**አዳምጦ መረዳት** (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም ጽሑፍን አዳምጦ መረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

**የአጻጻፍ ሥርዓት** (Writing convention)፡- የፊደላትን ቅርጽ፣ አሰዳደር፣ የአጻጻፍ አቅጣጫና የሥርዓተነጥብን አጠቃቀም የሚያሳይ የአጻጻፍ ሥርዓት፣

**ዋና ሀሳብ /አቢይ ሀሳብ** (Main idea)፦ ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አቢይ ወይም ዋና ሀሳብ፣

**ዐውድ** (Context)፦ ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣

**ዘውግ** (Genre)፦ በልዩ መዋቅሩ ወይም ባህሪያቱ የሚታወቅ የጽሑፍ መዋቅር፤ ምሳሌ፦ ተውኔት፣ ገላጭ ድርሰት፣ ተራኪ ድርሰት፣

**ዘዬ** (dialect)፦ በንበት/በድምጽ፣ በቃል ወይም በሰዋስው የሚከሰት አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት፣

**የጥንድ ንባብ** (partner reading)፦ በጥንድ ሆኖ ተራ በተራ የማንበብ ሂደት

**ጥያቄ መጠየቅ** (ask question)፦ ጥያቄ እየጠየቁ ማንበብ፣ ምንባቡን ለመረዳት ይጠቅማል። ለጥያቄዎች ምላሽ ማፈላለግ ያነበቡትን ለመረዳት ይረዳል፣

- ምንባቡ ስሜት ሰጥቶኛል?
- የማነበው ለምንድን ነው?
- ስለዚህ ምንባብ ምን የማውቀው ነገር አለኝ?
- ካነበብኩ በኋላ የምማረው ምንድን ነው?
- የዘለልኩት ነገር አለ?
- ምን ምን ጥያቄዎች አሉኝ?
- ስለምንባቡ ምን አስባለሁ? እስማማለሁ? ግራ ተጋብቻለሁ?
- ፍጥነቴን መቀነስ ነው ያለብኝ ወይስ መጨመር?

**የጽሑፍ መዋቅር** (text structure)፦ በጽሑፍ ውስጥ የይዘቶች አደረጃጀት

# ዋቢዎች

## ምዕራፍ 1

ሰሎሞን ይርጋ። 2000። *አዋቢዎች።* አሳታሚ፣ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር።

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። 1991። *የአማራ ክልል የቱሪስት መስህብ ሀብቶች (አጭር ቅኝት)።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት።

## ምዕራፍ 2

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ። 2002። *ሥነሕዝብና የቤተሰብ ሕይወት፣ ለሁለተኛ ደረጃ መምህራንና ወጣት ተማሪዎች የተዘጋጀ አጋዥ መጽሐፍ።*

## ምዕራፍ 3

ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት። 1995 ዓ.ም. *የኤች. አይ.ቪ./ኤድስ ትምህርት ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች።* አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።

## ምዕራፍ 4

ፍፁም ወልደማርያም። 2006። *ያልተዘመረላቸው።*

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ። 2004። *አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፤ ስምንተኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፤አርቲስቲክ አሳታሚ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ። 1989። *የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

## ምዕራፍ 5

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስአበባ፤ አልፋ አሳታሚዎች ድርጅት።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ። 2004። *አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፣ ስድስተኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

ደረጀ ገብሬ። 1996። *ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።


## ምዕራፍ 6


ሺበሺ ለማ። 1985። *ተጠየቅ፣* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሣታሚ ድርጅት።


## ምዕራፍ 7


ማረው ዓለሙ። 1998። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።


## ምዕራፍ 8


ተድላ ዘዮሐንስ። 2004። *የኢትዮጵያ ታሪክ። ኢጣሊያ በኢትዮጵያ፣ ከወልወል እስከ ጎንደር።* አዲስ አበባ፤ ማንኩሣ አሳታሚ ኃ.የተ.የግ.ማህበር።

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር። 2003። *የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ፤* 1ኛ እትም። ዱባይ፤ የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት።

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነፅሁፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ፈንታሁን እንግዳ። 2000። *ታሪካዊ መዝገበሰብዕ ከጥንት እስከዛሬ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።


## ምዕራፍ 9


የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጤና ቢሮ። 2006። *የጤና ፌስቲቫል ልዩ መጽሔት።* ጀጃው አሳታሚዎች ድርጅት።

የኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር። 2003። *የቲቢ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ መርሃ ግብር። ለዓለም ቲቢ ቀን መጋቢት 15፣ 2003።* የወጣ ልዩ ዕትም ቅጽ 3። አዲስ አበባ፤ ማስተር አሳታሚ ድርጅት።

# ምዕራፍ 10

ብርሃኑ ገበየሁ። 1999። *የአማርኛ ሥነግጥም።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ። 2005። *የግብርና ግጥማዊ ሥነቃል።* ባህር ዳር።

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ። 1997። *አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ፤ ሰባተኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።

አንተነህ አወቀ። 2001። «የአማርኛ ሥነቃል አጭር ቅኝት»። በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። *የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

አድማሱ ተስፋ። 1980። *የማርሽት።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ከበደ ሚካኤል። 1999። *ታሪክና ምሣሌ ፩ኛ መጽሐፍ።* ፪ኛ ዕትም፤ አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚና ማከፋፈያ።

ዘውዱ ምልክት። 2002። *ማ'ነው የተጣባት?* ባህር ዳር፣ አብሲኒያ ማተሚያ ድርጅት

ይርጋ ኃይሉ። 2001። *«የአማራ ባህል ገጽታዎች»። በአብክመ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ። የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።